# በአዲስ አበባ ከተማ የባህላዊ መድሃኒት አዘገጃጀት፣አሰጣጥና አጠቃቀም

ምህረት ዳኜው

በኢትዮጵያ፣ ስነጽሑፍና ፎክሎር ለኤም-ኤ-ዲግሪ
ማሟያ የቀረበ ጥናት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ-ትምህርት

ሰኔ/2000 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ከተማ ባህላዊ መድሃኒት፣አዘገጃጀት አሰጣጥና አጠቃቀም

በ

ምህረት ዳኜው

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት
የድኅረምረቃ መርሐ ግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ሥራ በአዲስ አበባ ከተማ የሚሰጠውን የባህላዊ መድሃኒት ህክምና የሚመለከት ነው ። የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች የህክምና ጥበብ መነሻ፣ የመድሃኒቶች መገኛና አዘገጃጀት እንዲሁም ታካሚን አካቶ የቀረበበት ነው። በአዲስ አበባ ከተማ ስለሚካሄደው የባህላዊ ህክምና ከዚህ ቀደም የተደረገ ጥናት የለም። የዚህ ሥራ አላማ የዘመናዊ ህክምና አገልግሎት በተሻለ ሽፋን በሚሰጥበት የአገራችን ዋና ከተማ የባህላዊ ህክምና በስፋት የሚሰጥበትን ምክንያት በመረጃ ላይ ተመስርቶ የህክምና አሰጣጡን መከታተልና ውጤታማነቱንም ከታካሚዎች ማረጋገጥ፣ በተጨማሪም እምነት በባህላዊ ህክምና ያለውን ሚና ለማሳየት ነው።

ጥናቱ የተካሄደው የባህል ሀኪሞችን፣ ታካሚዎችንና የዘመናዊ ጤና ባለሙያዎችን በቃለ መጠይቅና በባህላዊ ህክምና መስጫ ቦታዎች ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ ነው።

በከተማው እስከ ሦስት መቶ (የባህላዊ-ህክምና ባለሙያዎች የሰጡት መረጃ ነው) የሚደርሱ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች መኖራቸውንና፣ በእያንዳንዱ ሃኪም ደግሞ ቢያንስ በቀን አስር ታካሚ እንደሚገኝ የተሰበሰቡ መረጃዎች አመላክተዋል። ከአካላዊ ቁስለት ጋር የተያያዙ በሽታዎችን እንፈውሳለን ስለሚሉ፣ አብዛኛዎቹ ታካሚዎች የሰውነት ቁስል ያለባቸው ናቸው። ከመድሃኒት መሰብሰብ ጀምሮ እምነት የሃኪሞቹም ሆነ የታካሚዎቹ የፈውስ መነሻ ነው።

የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ሁሉም በቂ ችሎታ ያላቸውና ታማኝ ናቸው ባይባልም፣ ዘርፉ የሚሰጠው አገልግሎት ከፍተኛ ስለሆነ፣ በዘመናዊ የህክምና ባለሙያ ታግዞ ቢቀጥል ያለውን የጤና ችግር ለማቃለል አስተዋጽኦው የጎላ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል።

ማውጫ

ምስጋና
አጠቃሎ

1. መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

1.1 የጥናቱ ዳራ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
1.3 የጥናቱ ዓላማ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
1.4 የጥናቱ ወሰን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
1.6 የጥናቱ ዘዴና መረጃ አሰባሰብ . . . . . . . . . . . . . . . . 3
1.6.1 የአጠናን ዘዴ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
1.6.2 መረጃ አሰባሰብ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች . . . . . . . . . . . . . . . 6

2. የተዛማጅ ሥራዎችና የንድፈ-ሃሳብ ቅኝት . . . . . . . . . . . . 7
2.1 የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7
2.2 የንድፈ ሃሳብ ቅኝት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 14
2.2.1 የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች . . . . . . . . . . . . . . . 16
2.2.2 ሃይማኖትና እምነት በባህላዊ መድሃኒት ላይ . . . . . . . . . 17

3. የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች አጠቃላይ ዳራ . . . . . . . 19
3.1 የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞ ማስተዋወቂያ . . . . . . . . . . . . . . 19
3.2 የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች በአዲስ አበባ ከተማ ህክምናውን የሚሰጡበት አካባቢ . . . . . . . . . . . . . . . . 22
3.3 በባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች መካከል ያለው ግንኙነት . . . . . . .. 23
4. የባህላዊ ህክምና መድሃኒት ሃኪሞችና መድሃኒት . . . . . . . . . . . 28
4.1 የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞችና የእውቀታቸው መነሻ . . . . . . . . . . 28
4.1.1 የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ንጽጽር . . . . . . . . . . . . 31
4.1.2 የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች በአዲስ አበባ በብዛት የተገኙበት ምክንያት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 32
4.2 የባህላዊ ህክምና መድሃኒቶች መገኛና አሰባሰብ. . . . . . . . . . . . 34

4.3 የባህላዊ መድሃኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ . . . . . . . . . . . . . . 40
4.3.1 አዘገጃጀት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 40
4.3.2 አሰጣጥ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 44
4.4 የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች አዘውትረው
የሚፈውሷቸው የበሽታ አይነቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . 46
4.5 መንፈሳዊ ህክምና እና እምነት በባህላዊ ህክምና ዘርፍ. . . . . . . . 49
4.5.1 እምነት በባህላዊ ሃኪሞችና ታካሚዎች ላይ . . . . . . . . . . 51
4.6 የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች እየሰጡት ያለው አገልግሎት . . . . . 54
4.6.1 ታካሚዎች ለባህላዊ ህክምና ያላቸው አስተያየት . . . . . . . . 54

ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 58
የዋቢ ጽሑፎች ዝርዝር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 60

አባሪዎች

አባሪ -1- መረጃ አቀባይ የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች
አባሪ -2- የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች የሚያክሟቸው የበሽታ አይነቶች
አባሪ -3- መረጃ አቀባይ ታካሚዎች
አባሪ -4- ለባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎችና ለታካሚዎች
የቀረቡ ጥያቄዎች
አባሪ -5- ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች

# 1. መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ፣ በባህላዊ መድሃኒት ላይ የተካሄደው ይህ ጥናት አራት ምዕራፎች አሉት:: በመጀመሪያው ምዕራፍ አጠቃላይ የጥናቱ ማስተዋወቂያ ይገኛል:: በምዕራፍ ሁለት ተዛማጅ ሥራዎችና የንድፈ ሃሳቦች ቅኝት ሠፍሯል:: በምዕራፍ ሦስት የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች አጠቃላይ ዳራ ቀርቧል:: በምዕራፍ አራት የተገኙ መረጃዎች ተተንትነዋል::

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ፎክሎር ከሚያቅፋቸው የጥናት መስኮች መካከል አንዱ ሃገረሰባዊ ልማድ ነው:: ሃገረሰባዊ ልማድ ደግሞ ፌስቲቫልና ክብረ በዓልን፣ መዝናኛዎችን፣ ጨዋታዎችን፣ ሃገረሰባዊ መድሃኒቶችን እና ሃገረሰባዊ ሃይማኖትን ይይዛል /ፈቃደ፣ 1991፣11-14/:: የኔ ጥናት በሃገረሰባዊ መድሃኒቶች ላይ ሆኖ የሚያተኩረው በባህላዊ መድሃኒት አዘገጃጀት፣ አሰጣጥና አጠቃቀም ላይ ነው::
ባህላዊ መድሃኒትን በተመለከተ ማን እንዴትና መቼ ያዘጋጃል? ከምንና በምን ይዘጋጃል? እንዴት ጥቅም ላይ ይውላል? በዚህ ሂደት ሃይማኖት ቦታ አለው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ተሞክሯል::
http://en.wikpedia.org/wikil/Folk medicine የተባለው ድረ-ገጽ "Folk medicine" በሚለው ርዕስ ባህላዊ መድሃኒት የሚያካትታቸውን በሚከተለው ሁኔታ ገልጾታል::
"Folk medicine refers generally to healing practices traditionally used for alleviating **illness** and **injury**, or to aid in child birth. It is a category of informal knowledge, distinct from scientific medicine, as well as more formal and systematic" በባህላዊ መንገድ አገር በቀል መድሃኒቶችን በአገር በቀል እውቀት ለተለያዩ በሽታዎች መፈወሻ፣ ህብረተሰቡ እንዴት እየተጠቀመባቸው ነው? የሚሰጡት አገልግሎት ምን ያህል ነው? የሚለውን በመመርመር ወደ አንድ የለየለት አቅጣጫ ይመራል የሚል እምነት ነበረኝ:: በይበልጥም ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና እየተሰጠ በዘርፉ ጥናት አለመካሄዱ ትኩረቴን ስቦታል::

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የወጣሁበት ህብረተሰብ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ተጠቃሚ ስለነበር፣ ለዚህ ዘርፍ አገልግሎት እንግዳ አልነበርኩም:: ይህ ቀረቤታ ባለበት ሁኔታ ለክፍል ኮርስ ማሙያ፣

የባህላዊ መድሀኒት ባለሙያ በመጠየቅ የተርም ወረቀት እንድናቀርብ በኮርሱ መምህር ተጠየቅን:: የድርሻዬን የሰራሁት አዲስ አበባ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11 ነዋሪ የሆኑትንና በባህላዊ መድሃኒት ህክምና እውቅና ያላቸውን ሃኪም ማሞ ኃይሌን በመጠየቅ ነበር::

በህክምና ማዕከላቸው ተገኝቸ ምልከታ ባደረኩበት ወቅት 150 ታካሚዎች ነበሩ:: ለመድሃኒት መቀመሚያ የሰበሰቧቸውን ዕፅዋት፣ የተዘጋጁ መድሃኒቶችንና ለህክምና መመሪያ የሚገለገሉባቸውን የአገር ውስጥ የመድሃኒት መጻሕፍት ስመለከት ዘርፉ የጥናት መስክ ሊሆን እንደሚችል መነሻ ሃሳብ አገኘሁ::

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ዘመናዊ የህክምና አገልግሎት ባልነበረበት ዘመንና ዛሬም ባልተዳረሰበት አካባቢ መሰጠቱ፣ የሚያጠያይቅ አይደለም:: ዘመናዊ የህክምና ተቋማት በተሻለ ሁኔታ በሚገኙበት በአዲስ አበባ ከተማ በስፋት እየተሰጠ መሆኑ ግን ይበልጥ ትኩረትን እንዲስብ ያደርገዋል:: ስለሆነም ባህላዊ መድሃኒቶች የሚገኙበትንና የሚዘጋጁበትን እንዲሁም የሚያዘጋጁትንና የሚጠቀሙበትን በመመርመር በጽሑፍ አስፍሮ ማሳየት የጥናቱ ዋና አላማው ሲሆን፣ ዝርዝር አላማዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው::

### ዝርዝር አላማዎች

- የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች የህክምና ጥበብ መነሻንና የህክምና መድሃኒቶች አሰጣጥን ማሳየት፣
- ባህላዊ መድሃኒቶች የሚገኙበትን አካባቢና አዘገጃጀት፣ ማመልከት፣
- የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች አዘውትረው የሚፈውሷቸውን በሽታዎች በመረጃ አስደግፎ ማቅረብ፣
- ሃይማኖትና እምነት በባህላዊ መድሃኒት ላይ ያለውን ሚና ማሳየት ናቸው ::

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

በአዲስ አበባ ከተማ ያሉት የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች ቁጥራቸው በውል አይታወቅም :: የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ በአንድ ወቅት ለስብሰባ ጠርቶ 140 ሃኪሞችን እንደመዘገበ ሲገልጽ፣ የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞቹ ደግሞ ከ300 አናንስም ብለዋል :: ይህ ጥናት፣ አሉ የተባሉትን የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች አያካትትም :: በሰባት የባህላዊ

መድሃኒት ሃኪሞች ላይ ብቻ ያተኩራል ። እነዚህ ተጠኝና መረጃ አቀባዮች ናቸው ። ወደ ሃኪሞቹ ከሚመጡትና የባህላዊ ህክምና ከሚሰጥበት ቦታ በምልከታ ወቅት ካገኘኋቸው (ፈቃደኛ ከሆኑት) ታካሚዎች መካከል በሰባት ታካሚዎች ቃለ መጠይቅና በስድስት ታካሚዎች የጽሑፍ መረጃ እንድወስን ሆኗል ።

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ባህላዊ መድሃኒት ህክምና ዛሬም፣ በገጠርም ሆነ በከተማ ያለው ህብረተሰብ የጤና ችግር መፍቻ አድርጎ እየተጠቀመበት የሚገኝ የህክምና ዘርፍ ነው። ስለሆነም ሊጠና ይገባዋል። በእርግጥ ይህ ጥናት የመድሃኒቶቹን ንጥረ ነገር የሚመረምር አይደለም። ዘመናዊ የህክምና ተቋማት በሚገኙበት በአዲስ አበባ ከተማ በስፋት ባህላዊ ህክምና የሚሰጥበትን ምክንያት ለማሳየትና የህክምና ዘርፉን ለማሳደግ ከባህላዊ መድሃኒት የበሽታ መከላከያ ለማዘጋጀት መነሻ ሃሳብ ለማግኘት ጥናቱ አስፈላጊ ነው ተብሎ ይታመናል።

ባህላዊ መድሃኒት ህክምና በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠ ስለሚገኝ፣ የሚሰጠውን ጥቅምና የሚያደርሰው ጉዳትም ካለ ለመለየትና ለማጠናከርም የዘርፉ መጠናት እገዛ ያደርጋል። ቢሻሻልና ቢስፋፋ ደግሞ በአገር በቀል መድሃኒትና እውቀት ወገንና አገር ተጠቃሚ ስለሚሆኑ ይህ ጥናት መቀስቀሻ ከመሆኑም በላይ ለሌሎች አጥኚዎች በመረጃነት ሊያገለግል ይችላል።

## 1.6 የጥናቱ ዘዴና መረጃ አሰባሰብ

### 1.6.1 የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ የተካሄደው የአገር ውስጥና የውጭ አገር ተዛማጅ ሥራዎችን በማንበብ፣ ባህላዊ መድሃኒት ህክምና በሚሰጥባቸው አሥራ አንድ ቦታዎች ምልከታ በማድረግና ማስታወሻ በመያዝ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች አዘጋጅቼ፣ ለባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎችና ለታካሚዎች በማቅረብ ነው። በተጨማሪ ከኃላፊነትና ከሙያ አንጻር ጤና ጥበቃንና የአዲስ አበባ ጤና ቢሮን ጠይቄ መረጃዎች በመሰብሰብ ሙያውን ከተለያየ አቅጣጫ ለማየት ሞክሬአለው። የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ይበልጥ አገልግሎት ከሚሰጥባቸው በሽታዎች ጋር የተያያዙ የቆዳና የሥነ-ልቡና ስፔሻሊስት ዶክተሮችን ሙያዊ አስተያየትና የህክምና ሥነ ምግባር በመጨመር፣ የተገኙ መረጃዎችን በማነፃፀር፣ እንዲሁም ተዛምዶና ልዩነታቸውን ለይቶ በማሳየት ወደታሰበው ግብ ለመድረስም ሞክሬአለሁ። የጥናቱ አቀራረብ ገላጭ የጥናት ስልትን የተከተለ ይሁን እንጂ በአሃዛዊ መረጃዎች የተደገፈም ነው።

### 1.6.2 መረጃ አሰባሰብ

በቤተ መጻሕፍት የሚገኙና ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተዛማጅ የሆኑት ቀደምት የተፃፉ ሥራዎች እንዲሁም ለንድፈ ሃሳብ መሰረት የሚሆኑ መጻህፍት ተነበው ተፈላጊው መረጃ ተወስዷል:: ተጠኝ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች ባላቸው ከፍተኛ እውቅና፣ ታቃቂ ሃኪሞች የተሸሉ ናቸው በሚል በሰጡኝ መረጃ መሰረት እና ደጋግመው ባወጡዋቸው መረጃ መሰረት የተመረጡ ናቸው :: ህክምና የሚሰጡባቸው ቦታዎችም በአዲስ አበባ ከተማ በአራቱም አቅጣጫዎች የሚገኙ ሲሆኑ ከነሱም በምልከታና በቃለ መጠይቅ መረጃ ሰብስቤያለው::

ምልከታ በአካል ተገኝቶ ድርጊትን በትኩረት በመከታተል ለመገንዘብ የሚያስችል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መሆኑን አለም እሸቱ እንደሚከተለው ገልጸውታል::

> ምልከታ በአለፍ አገደም አይተን የምናልፈው ጉዳይ ሳይሆን፣ በቅድሚያ ለታቀደ መሠረታዊ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሲባል የሚከናወን ትኩረትንና ምርምርን የሚጋብዝ መረጃ የማሰባሰቢያ ስልት ነው:: በዚህ ሂደት ውስጥ በቂ ጊዜ ወስዶ መመልከት፣ የተመለከቱትንም ሳይዘገዩ ወዲያውኑ መዝግቦ ማስቀረት የተያያዙ ክንውኖች ይሆናሉ/1992፣69/::

ይህን መሠረት በማድረግም በአስራ አንድ የባህላዊ ህክምና መስጫ ቦታዎች፣ እስከ ሶስት ጊዜ በመመላለስ ምልከታ አድርጌአለሁ:: ከሃኪም ተክሌ ሃብተገብርኤል፣ ከሃኪም ሃጂ ሳኒ አሊ፣ ከሃኪም ተውሕቦ ምህረትና ከሃኪም ጥበቡ አንበርብር፣ ከሰዓት በኋላ ያለውን የህክምና አሰጣጥ ለመከታተል አንድ አንድ ቀን በህክምና መስጫ ቦታቸው ተገኝቻለሁ:: በአብዛኛው ምልከታ ያደረኩት ጧት ነው:: ታካሚዎችም በብዛት የሚመጡት ጧት ነው:: ከሁለት እስከ አምስት ሰዓት በህክምና መስጫ ቦታዎች ቆይታ አደርግ ነበር::

ምልከታ ያደረኩባቸው የባህላዊ መድሃኒት ህክምና መስጫ ቦታዎች፣ ታካሚዎችን ይመዘግባሉ:: የምዝገባም ያስከፍላሉ:: የሃኪሞች ረዳቶች ተራ ያስከብራሉ፣ መድሃኒቶችን በታዘዘው መሠረት ይሰጣሉ፣ ከዚያም የሚጠጣና የሚዋጥ ከሆነም አዘጋጅተው ያቀርባሉ:: ታካሚዎች ምርመራ ክፍል ገብተው ሲወጡ የሚታጠን፣ የሚቀባ፣የሚጠጣ በተወሰነ ጊዜ የሚዋጥ፣ ለቁስል ከሆነም የሚቀባና የሚታሰር መድሃኒት ሲሰጣቸው አይቻለሁ::

ቃለ መጠይቅ ሌላው መረጃ የሰበሰብኩበት መንገድ ነው::

ቃለ መጠይቅ ተጠያቂው ከጠያቂው ጋር በግንባር ተገናኝቶ ፣ በጽሑፍ ሳይሆን በቃል መልስ የሚሰጥበት ሂደት ነው:: ቃለ መጠይቅ በብልሃት ከተያዘና ተግባር ላይ ከዋለ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያና ማጠናቀሪያ ስልቶች በተሻለ መንገድ መረጃ ለማሰባሰብ ያስችላል:: ቃለ መጠይቅ መረጃን ከዋናው፣ ከምንጩ የመሰብሰቢያ አንዱ መንገድ በመሆኑ፣ ርቱእ የመረጃ መንጮችን በመመርኮዝ የተሻለና የበለጠ አስተማማኝነት ያለው መረጃን ሰብስቦ ለማጠናቀር ያስችላል /አለም እሸቱ1992፣65/::

በዚህ መሰረተ ሃሳብ ተመርኩዤ ከባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎችና ከታካሚዎች ጋር ቀጠሮ በመያዝ በቃለ መጠይቅ መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ:: ከጤና ጥበቃ ፣ ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ፣ የቆዳ ህክምና ስፔሻሊስት ከሆኑት ከዶ/ር ሩት ሊካሳ፣ ከስነልቦና ስፔሻሊስት ዶ/ር አታላይ ዓለም ጋር ቃለ መጠይቅ ፣ በማካሄድ መረጃዎችንም ለማጠናከር ጥረት አድርጌያለሁ::

በተዘዋወርኩባቸው የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ሲታከሙ ካገኟቸው በሽተኞች መካከል ስለ በሽታቸው እንደነገሩኝ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ኪንታሮት፣ነቀርሳና መስል ቁስል ያለባቸው ናቸው:: ለህክምና ወረፋ በመጠባበቅ ላይ እያሉ ሲነጋገሩ እንደሰማኋቸው፣ ዘመናዊ ህክምና ሞክረው ስላልዳኑ፣ የሀኪሙን የማዳን ዝና ሰምተው፣ የዳኑ ሰዎችን አይተውና ማስታወቂያ አንብበው የመጡ መሆናቸውን ተገንዝቤአለሁ::

ታካሚዎቹ በምልከታ ወቅት አነጋግሬአቸው ከአዲስ አበባ፣ከሌሎች ከተሞችና ከተለያዩ የገጠር አካባቢዎች የመጡ መሆናቸውን ገልጸውልኛል:: ፈቃደኛ የሆኑት በቃለ መጠይቅ ተካተዋል:: በማንኛውም የእድሜ ክልል የሚገኙ ወንድና ሴት የባህል ህክምናው ተጠቃሚ ናቸው:: ከህመማቸው ያገገሙ ሰዎች መጥተው ሲያመሰግኑ አይቻለሁ:: በጽሑፍ ያስፈረሟቸውን ማረጋገጫዎችም አንብቤአለሁ:: ሃኪም ተክሌ ኃብተገብርኤልና ሃኪም ሃጂ ኑሩ አደም፣ ታካሚዎች ከህክምና በፊትና በኋላ ያላቸውን ሁኔታ የሚያሳይ የፎቶግራፍ መረጃ አዘጋጅተዋል::

በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ በጽሑፍ ከባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎችና ከታካሚዎች የተገኘው ሁሉ የመጀመሪያ መረጃ ምንጭ ሆኖ ቀርቧል :: የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የህክምና አገልግሎት አሰጣጥንና አስተዳደርን በተመለከተ የሰጡት መረጃም በጥናቱ ተካቷል ::

እምነትና የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ክርስቲያንና ሙስሊም የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች /የታሰበውን ያህል ባይሆንም/ የጥናቱ አካል ሆነዋል :: ለመረጃ መሰብሰቢያ የተጠቀምኩት የፎቶ ካሜራና የድምፅ መቅረጫ ቴፕ ነው ::

## 1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች ህክምናውን ይሰጣሉ፣ ታካሚም ይታከማል እንጂ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና አገልግሎ በተመለከተ መረጃ የለም ። ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች የተጠናከረ መረጃ አለመኖር ለጥናቱ ችግር ነበር። የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ቁጥር ስለማይታወቅ በቀን የሚያክሙትን በሽተኛ ቁጥር ለማወቅም አልተቻለም ። የሚያክሙትንም ፈውስ ፈላጊ በአግባቡ መዝግበው ስለማይዙና ለመናገርም ብዙዎቹ ፈቃደኛ ስለአልሆኑ የተጨበጠ የአካሚና የታካሚ ቁጥር ማቅረብ አልተቻለም ።

ለባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች የህክምና ፈቃድ ይሰጥ የነበረው አገር አቀፉ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ማህበር ነበር (ከጤና ጥበቃ የተገኘ መረጃ) ። ከህዳር ወር 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ህጋዊ የሙያ ማህበር አይደለም በሚል ስለታገደ፣ በዚህ በኩልም መረጃዎች ዝግ ነበሩ ። በባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች መካከል የሙያ ግንኙነት ስለሌለ አንዱ ስለሌላው መረጃ አይሰጥም ።

ከምልከታ በኋላ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፃፈልኝን የትብብር ደብዳቤ ሰጥቼ ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኝነታቸውን ስጠይቃቸው፣ እጅግ የተጠራጠሩና የተለያየ ምክንያት ሰጥተው ለማናገር ያልፈለጉ አሉ ።

## 2. የተዛማጅ ሥራዎችና የንድፈ ሃሳብ ቅኝት

የተዛማጅ ሥራዎችና የንድፈ ሃሳብ ቅኝት ለማድረግ ከባህላዊ መድሃኒት ጋር ተያያዥነት ያላቸው በአገር ውስጥና በውጭ አገር ተመራማሪዎች የተሰሩ የጥናት ወረቀቶችን፣ የኮንፈረንስ ወረቀቶችን፣ የማስተርስና የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናቶችን፣ መጻሕፍትንና ሌሎች ምንጮችን ተመልክቻለሁ ::

### 2.1 የተዛማጅ ሥራዎች ቅኝት

የባህላዊ መድሃኒትን ጉዳይ የሚመለከት በአዲስ አበባ ላይ የተደረገ ጥናት አላገኘሁም :: በሌሎች አካባቢዎች የተደረጉ ጥናቶች ግን አግኝቼ ተመልክቻቸዋለሁ :: ከዚህ ቀጥሎ እነሱን ባጭር ባጭሩ እቃኛሁ :: በመጀመሪያ የምቃኘው ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶችን በቅደም ተከተል ይሆናል ::

አሰፋ ባልቻ /1992/[1] « Traditional Medicine in Wello Nature and History» በሚለው የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፋቸው የቀረበው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ታሪክ ክፍለ ትምህርት ነው:: አጥኚው እንደተነሱበት አላማ የባህል መድሃኒቱን ይበልጥ ከታሪክ አንፃር ተመልክተውታል:: ጥናቱ የተካሄደው በደሴ ከተማ ዙሪያ ነው:: አጥኚው ይበልጥ ትኩረት ያደረጉት በቁምጥና፣ በቂጥኝ፣ በጨብጥ፣ በኩፍኝ፣ በሳንባ ነቀርሳና ከመጥፎ መንፈስ ጋር በተያያዙ በሽታዎች ላይ ነው:: እነዚህንና መሰል በሽታዎችን የሚያክሙ በአካባቢው የሚገኙ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎችን በችሎታና በታማኝነት ከፍለው ተመልክተዋቸዋል ::

በእርግጠኝነት ለሚያድኗቸው በሽታዎች ብቻ በነፃና በአነስተኛ ክፍያ የሚያክሙና ሁሉንም አይነት በሽታ እናድናለን በሚል የተለያዩ መድኒቶችን እያቀያየሩ በመስጠት ገንዘብ የሚሰበስቡ መኖራቸውን ገልፀዋል :: የተለያዩ መድሃኒቶችን በመውሰድ ጉዳት የሚደርስባቸው ታካሚዎች ቢኖሩም፣ ጥናቱ የተካሄደበት ህብረተሰብ በባህላዊ መድሃኒት ላይ ከፍተኛ እምነት አለው ብለዋል::

በባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎችና በዘመናዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች መካከል ከፍተኛ እርቀት ስለአለ፣ ለጋራ አላማ ተቀራርበው ቢሰሩ የተሻለ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል፣ እንዲሁም ለባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ድጋፍ ቢደረግላቸው እነሱም፣ ያገኙትን እውቀት አፍነው ከመያዝ ቢላቀቁ ተገቢ መሆኑን አጥኚው ጠቁመዋል ::

---

[1]በሁሉም ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ የተገኘውን ዓመተ ምህረት እንዳለ ነው ያቀረብኩት

ለተወሰኑ በሽታዎች በባህላዊ ሃኪሞች የሚታዘዙትን የእፅዋት ዝርዝርና አጠቃቀም በአባሪነት አያይዘዋል ::

ሚርጊሳ ካባ /1993/ « Indigenous Medical Beliefs and Practices Among the Oromo of Illubabor » በሚል ርዕስ የፃፉት ጥናት፣ በሶሻል አንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነው :: አጥኚው ምልከታቸውን በአደረጉበት ህብረተሰብ ላይ፣ በርዕሳቸው እንደጠቀሱት እምነት ለባህላዊ መድኃኒት ከፍተኛውን ቦታ እንደሚይዝ ገልፀዋል ::

«ረቢ» በኦሮሞ እምነት «እግዚአብሔር» እንደማለት ነው :: ስለሆነም «ረቢ» የበሽታዎችን መፈወሻ መድሃኒት ይናገራል ተብሎ ይታመናል :: ይህ እምነትና አገር በቀል የህክምና ስልት ረጅም እድሜ ያለውና እንደሌላው ህብረተሰብ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ነው ብለዋል:: አጥኚው፣ በሽታዎችን ለይተው በመዘርዘር፣ የሚሰጠውንም ህክምና ጠቅሰዋል:: ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ የሚገኙት የባህል ሃኪሞች ተመሳሳይ /ተቀራራቢ/ እውቀት አላቸው ብለዋል:: «ረቢ» ገለፀልን የሚሉት የባህል ሃኪሞች፣ በጫት እየታገዙ በዱዓ ሥርዓት ከፀሎት ጋር ህክምናውን እንደሚሰጡም ገልፀዋል ::

ለበሽተኞች የሚሰጠው የእፅዋት፣ የእንስሳትና የማእድናት ውጤት፣ ዋናው የህክምና ክፍል አይደለም:: ተፈላጊው ከመድሃኒቱ ጋር የተያያዘው እምነት መሆኑም ተጠቁሟል :: ይህ ቀደም ሲልም ሆነ ዛሬ አገልግሎት እየሰጠ ያለ የህክምና ዘርፍ፣ በዘመናዊ የህክምና ስልት እየታገዘ ሊቀጥል ይገባዋል በማለት አጥኚው አስተያየት ሰጥተዋል :: ለየበሽታዎች የሚሰጡት የመድሃኒት አይነትና የአሰጣጥ ሥርዓት በአባሪነት አልተካተተም ::

አብራራው ተስፋዬ /1998/ « Traditional Medicine in an Urban Belief and Practice (The Case of Dessie Town, N. Ethiopia)" ይህ ጥናት በደሴ ከተማ የተካሄደና በሶሻል አንትሮፖሎጂ የትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ነው:: ዘመናዊ የህክምና ማዕከላት በሚገኙበት የደሴ ከተማ የባህላዊ መድሃኒት በስፋት መሰጠቱ የሥነ ልቡናና የመንፈስ ፍላጎትን ያሟላል ተብሎ በገጠሬውና በከተሜው ኗሪ በመታመኑ መሆኑን አጥኚው ይገልፃሉ :: በተለይ የዘመናዊ ህክምና መፍትሄ ያላገኙላቸው እንደ ኪንታሮት፣ ነቀርሳ፣ ችፌ፣ አውድቅ፣ ልፊ የመሳሰሉት በባህላዊ ህክምና ስለሚድኑ የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞችን ተመራጭ የሚያደርግበት ሁኔታ መኖሩም ተጠቁሟል :: ከመንፈስ ጋር የተያዙ፣ እንደ ዛር፣ጂኒ፣ ክፉ ልክፍት አይነ-ጥላ የመሳሰሉት በሽታዎች ፈውሳቸው የሚገኘው ከባህል ሃኪሞች ነው ተብሎ እንደሚታመንም አጥኚው ገልፀዋል:: የባህላዊ መድሃኒት ህክምና

አንዱ አካል የሆነው መንፈሳዊ እምነትም በደሴ ከተማ ተግባራዊ እንደሚደረግ በቅዱስ ጊዮርጊስ ፀበል ተጠምቀው የዳኑ የሙስሊም እምነት ተከታዮችን በመረጃነት በማቅረብ ነው::

የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ከዚያው ህብረተሰብ የወጡ ስለሆኑ የሚሰጡት ህክምና ይታመናል :: ታካሚው ከዘመናዊ ህክምና ያነሰ ክፍያ መጠየቁ ደግሞ ሌላው ለህክምናው ዘርፍ ተመራጭነት ምክንያት እንደሆነ አጥኚው ገልፀዋል :: የተማረውም ሆነ ያልተማረው ህብረተሰብ በሁለቱም የህክምና ተቋማት መገልገሉና ዘመናዊ ህክምና መፍትሔ ያላገኙ ላቸውን በሽታዎች በባህላዊ ሃኪሞች መዳናቸው ሲታይ፣ የባህል ህክምናው አገልግሎት ተጠናክሮ ቢቀጥል መልካም ነው ብለዋል ::

ዘሪሁን ዶዳ /2001/ « CULTURE BELIEF AND MENTAL ILLNESS AMONG THE ZAY" ጥናቱ የቀረበው፣ በሶሻል አንትሮፖሎጂ የትምህርት ክፍል ነው:: በዝዋይ ሃይቅ ደሴቶች ላይ የሚኖሩ የዛይ ህብረተሰብ ነዋሪዎችን የሚያጠቁ ዋና ዋና በሽታዎች በጥናቱ ተጠቅሰዋል :: ቦታው ለኗሪዎቹ አስቸጋሪ ለበሽታዎቹ ግን አመች መሆኑን ከገለፁ በኋላ፣ አጥኚው ትኩረት ያደረጉት በአእምሮ በሽታ ላይ ነው ::

የአእምሮ በሽታ በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ የሰይጣን ልክፍት ነው ተብሎ ይታመናል :: ይህ በክፉ መንፈስ መጣ የሚባል በሽታ በአካባቢው የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች በሁለት መንገድ ህክምና ይደረግለታል :: ቀዳሚው፣ ሰፊ ተቀባይነት ያለው የአካባቢው ህብረተሰብ አጥብቆ የሚያምንበት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቄሶችን ማፀለይና ፀበል ማስጠመቅ ነው:: ቄሶች ከሚሰጡት የፀሎት ህክምና አገልግሎት በተጨማሪ፣ በሽተኛው ስለት እንዲያስገባ፣ ሰባት ቀን ወይም ከዚያ በላይ በፀበል እንዲጠመቅ ይደርጋል:: ይህ ካልተሳካ ደግሞ በሽተኛውን ዘመናዊ ህክምና ወደሚሰጥበት አማኑኤል ሆስፒታል መላክ የመጨረሻ ምርጫ መሆኑ በጥናቱ ተጠቅሷል ::

ሁለተኛው የህክምና ዘርፍ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት መሪዎች ዘንድ የተወገዘና በሙስሊም እምነት ተከታይ ቃልቻዎች የሚሰጥ ባህላዊ ህክምና ነው:: ህክምናው የሚሰጠው በበሽተኛው ላይ አለ የሚባለው ክፉ መንፈስ በስም ተለይቶ ይታወቅና ያስወግደዋል በሚባል ተክል ጭስ ማጠን፣ ከጠነከረም በሽተኛውን በአለንጋም ሆነ በጨንገር መግረፍ ይሆናል :: እንዲሁም ክፉው መንፈስ ይወደዋል የተባለው ቀለም አይነት ተመርጦ ዶሮ፣ በግ፣ ፍየልና በሬ እንዲያርድ የሚደረግ መሆኑን በጥናታቸው አረጋግጠዋል ::

የልምድ አዋላጅ፣ ወጌሻ፣ ገራዥ፣ የመድሃኒት ዕፅ አዋቂ፣ እንዲሁም ለተለያዩ በሽታዎች አገልግሎት የሚሰጡ የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች በዝዋይ ሃይቅ ደሴቶች ላይ መኖራቸውን አጥኚው ጠቁመዋል:: ጥናታዊ ጹሁፉ የባህላዊ መድሃኒት ዝርዝር አባሪ የለውም::

አለማየሁ ዘሪሁን /2000/ «የኑዌር ማህበረሰብ የባህል መድሃኒት እውቀት አመለካከት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ» በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ ጹሑፍ ክፍል የኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር የተሰራ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ነው:: አጥኚው ያተኮሩበት የህብረተሰብ ክፍል ከአዲስ አበባ ከተማ በ889 ኪ.ሜ የራቀና ዘመናዊ ህክምና በቅርበት የማይገኝበት አካባቢ ነው:: ባህላዊ ህክምና ለኑዌሮች አማራጭ ሳይሆን ዋና የህክምና ተቋም ተደርጎ እንደሚቆጠር ተገልጿል:: በዚህ ህብረተሰብ የባህላዊ መድሃኒት ከሌላው አካባቢ የተለየ ገጽታ እንዳለውም ተጠቁሟል:: ኑዌሮች ግልፅ ከመሆናቸውም በላይ ለሚሰጡት የህክምና አገልግሎት ገንዘብ አይቀበሉም:: ዋጋቸው ህብረተሰቡን ማገልገላቸው ነው::

የባህላዊ ሃኪሞችን የህክምና አሰጣጥ፣ የመድሃኒት አዘገጃጀት፣ የታካሚ አጠቃቀም፣ የመድሃኒት ዕፅዋት አይነት ለመድሃኒት የሚውለውን የተክል ክፍል በግልፅ የማየት፣ የመመዝገብና ፎቶ የማንሳት እድል እንደገጠማቸው አጥኚው ገልጸዋል :: የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞቹን ባህሉ በአራት ምድብ የከፈላቸው ሲሆን፣ ከነዚህ የህክምና ባለሙያዎች ውጭ ህክምና የሚሰጥ አለመኖሩን በጥናታቸው አረጋግዋል:: የመጀመሪያ የባህል ህክምና የሙያ ስያሜ «ቴት ዋል» ይባላል :: ይህ የህክምና ቡድን የባህላዊ መድሃኒትን የመጠቀም ችሎታ ያለው ነው :: «ይስ» የተባለው የህክምና ቡድን የተሰበረና የወለቀ አጥንት የሚያክም ነው:: ለቁስሉ ማድረቂያ አንዳንድ ዕፅዋትን ስለሚጠቀም ከ «ቴት ዋል» ጋር የሚጋራውም አለ :: «ጋም» በዚህ ስያሜ የሚጠሩት የባህል ሃኪሞች ሴቶች ሲሆኑ፣ ከወሊድ ጋር የተያያዘ የጤና ችግሮችን የሚያክሙ ናቸው :: ህክምናው የሃገረሰብ እምነት ተፅዕኖ ያለበት ነው :: «ጎክ» እነዚህ የባህላዊ ህክምና ቡድኖች ደግሞ «መንፈሳዊ ሃኪም» በመባል የሚታወቁ ናቸው :: በሽታን የመፈወስ ጥበብ ከፈጣሪ እንዳገኙት የሚቆጥሩ፣ በእምነትና በፀሎት የሚያድኑ ናቸው:: ሃገረሰብ መንፈሳዊ እምነቶችም ኮስ፣ቤል፣ ዊው፣ እና ዴንግ የሚባሉ ናቸው :: ለእምነቶቹ መስዋዕትም ይደረግላቸዋል :: ይህ የህክምና ዘርፍ በዘር የሚወረስ መንፈሳዊ ስጦታ ተደርጎ እንደሚታመን አጥኚው ገልጸዋል ::

አራቱም የኑዌር የባህል ህክምና ቡድኖች ለሙያቸው ክፍያ ስለማይጠይቁ ነፃ አገልግሎት ሰጭ መንግስታዊ ያልሆኑ አገር በቀል የባህል ህክምና ድርጅቶች ሊባሉ ይገባል ሲሉ አጥኚው አጠቃለዋል :: ለየበሽታዎች የሚሰጡትን ዕፅዋቶች ዝርዝርና አጠቃቀማቸውን በጥናታቸው አካተዋል:: ከዚህ ቀጥየ ደግሞ ለፒኤችዲ የተደረገ ጥናትን በአጭሩ እቃኛለሁ::

ፈቃዱ ፋሲስ /2001/ « Ethiopian Tranditional Medicine Common Medicinal Plants in Persepective » በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ነው ። ጥናቱ በፋርማሲ ሙያ ዘርፍ የቀረበና ከዘመናዊ የህክምና ዘርፍ ጋር የተያያዘ የምርምር ውጤት ነው ።

የባህላዊ መድሃኒት በሰለጠነው አለም እንደ አማራጭ የህክምና አገልግሎት ሲታይ ነበር ። አሁን አሁን ግን ተፈላጊነቱ እየጨመረ ለየሃገሮቹም ከፍተኛ ገቢ ማስገኛ እየሆነ መምጣቱ በጥናታዊ ጽሑፋ ተገልጿል ። ባህላዊ መድሃኒት በአፍሪካ ከጥንት እስከ ዛሬ ዋና አገልግሎት ሰጭ ነው ። ዘመናዊ ህክምና እየተስፋፋ የመጣ ቢሆንም፣ የባህላዊ ህክምናው አብዛኛውን የአገልግሎት ድርሻ እንደሚይዝ የየሃገሮቹን ልምድ እየጠቀሱ አጥኚው አብራርተዋል ።

በኢትዮጵያ የባህላዊ መድሃኒት እንደሌላው ዓለም አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ መሆኑን የሚገልጽ የጽሑፍ መረጃ በ13ኛው እና በ14ኛው ክፍለ ዘመን መገኘቱንና ዛሬም እየሰጠ መሆኑን በአገሪቱ ያለውን የባህል መድሃኒት የህክምና አሰጣጥ ስልት በመዳሰስ በጥናታቸው አሳይተዋል።

አጥኚው በ1941 ዓ.ም የባህላዊ መድሃኒት በመንግስት እውቅና ያገኘ መሆኑን፣በደርግ ዘመንም ለባህል መድሃኒት ትኩረት ተሰጥቶት ሥርዓት ለማስያዝ ተሞክሮ እንደነበር የመኮንን ቢሻውን /1991/ ጥናት በመጥቀስ አቅርበዋል ። በወቅቱ የባህል ሃኪሞችም እንዲመዘገቡና ማህበር እንዲመሰርቱ ተደርጎ እንደነበር ገልፀዋል ። በእምነት፣ በፀበል፣ በፍል ውሃ፣ በደብተራ፣ በቃልቻ የሚካሄድ ፈውስ መኖሩንም በጥናታቸው ላይ ገልፀዋል። የተወሰኑ የባህል ህክምና መመሪያ መጻሕፍት በክርስትናውም ሆነ በእስልምናው እምነት መኖራቸውንም ጠቅሰዋል ። እንደ ዘመናዊ የህክምና ባለሙያነታቸው፣ የባህል መድሃኒቶች በአግባቡ ተጠንተውና በዘመናዊ ሥልጣኔ ታግዘው አገልግሎት የሚሰጡበት መንገድ መኖሩን የተለያዩ አገሮችን ልምድ አቅርበው ለዘርፉ ትኩረት ይሰጠውም ብለዋል ። በኢትዮጵያ በጣም የታወቁ 99 ዕፀ መድሐኒቶችና አገልግሎታቸውንም በጥናታቸው አካተዋል ።

Young Allen /1970/ « Medical Belief and Practices of Begemder Amhara » ሎስአንጀለስ ፔንሲልቪያ ዩኒቨርስቲ በአንትሮፖሎጂ ትምህርት ክፍል ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው ። ከእምነት ውጭ በቆየና ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ የአካባቢ የህክምና እውቀት፣ በአካባቢው ከሚገኙ ዕፀዋት የሚሰጥ ህክምና የመጀመሪያ ነው። ሁለተኛው ደግሞ

በኦርቶዶክስ እምነት ኃይማኖታዊ ትምህርት እውቀት የቀሰሙና ከእምነቱ ስርዓት ውጭ በደብተራ ተዘጋጅቶ በድግምት በክታብ የሚሰጥ ህክምና እንደሆነ በጽሑፉ ሰፍሯል ። የመጀመሪያው የህክምና ቡድን በተፈጥሮ ሃብቶች የሚታገዝና ህክምናውን የገቢ ምንጭ የማያደርግና ለጊዜው ህመም መፍትሄ የሚሰጥ እንደሆነ ተጠቅሷል ።

አጥኚው ይበልጥ ትኩረት የሰጡት ለ«ደብተራ» የህክምና ቡድን ነው ። ይህ የህክምና ቡድን ከቤተክርስቲያን እምነት አፈንግጦ የወጣና የድግምት ትምህርቱን በመማር /ከአገልግሎት ከጓደኛ፣ በገንዘብ. . ./ ለገቢ ምንጭ የሚጠቀምበት ነው ። የትምህርቱ መጠሪያ «አብነት» ሲባል፣ ለዚህ የሚረዳ «አውደ ነገሥት» የሚባል የምሪት መጽሐፍ መኖሩም ተገልጿል ። ታካሚ ለእለት ህመሙም ሆነ ለዘለቄታው መፍትሄ፣ ደብተራው ያዘጋጀለትን በቁመት ወይም በወገብ ዙሪያ መጠን ባለው ብራና ላይ በተለያዩ ቀለማት ያሸበረቀ ጽሑፍ ተጠቅሎ በክታብ ያሰራል ብለዋል ።

ROUNDY /1976/ « HAZARDS OF COMMUNICABLE DISEASE TRANSMISSION RESULTING FROM CULTURAL BEHAVIOR IN ETHIOPIAN RURAL HIGHLAND DWELLING POPULATION » ካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ በጂኦግራፊ የትምህርት ዘርፍ የቀረበ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጹሑፍ ነው:: የአጥኚው ትኩረት፣ ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ ያሉ ዋና ዋና በሽታዎችንና መተላለፊያ መንገዳቸውን ከመለየት ላይ ነው ። ዋና ዋና በሽታዎችንና መተላለፊያ መንገዳቸውን ጠቅሰው፣ ለአካባቢው ማኅበራዊ የጤና ቀውስ ዋናው ምክንያት እና መተላለፊያ መንገዱ የህብረተሰቡ የአኗኗር ሁኔታ፣ ግንኙነት፣ አመጋገቡ፣ የንጽህናው ይዞታና እምነቱ መሆኑን በጥናታቸው አረጋግጠዋል ። ጥናቱ የተካሄደበት ህብረተሰብ በዘመናዊ ህክምና የሚገለገል ቢሆንም ባህላዊ ህክምናውን ግን ያዘወትራል ። እንደ ግለሰቡ ምርጫና እምነት ረጅም ርቀት በመጓዝ በፀበልና በፍል-ውሃ ፈውስ ለማግኘትም ጥረት እንደሚደረግ ሁሉ ወደ ጠንቋይ መሄዱም ሌላው ምርጫ መሆኑን አጥኚው በጽሑፋቸው አስፍረዋል ። የሚከተሉት ደግሞ በተለያዩ ጉባኤዎች የቀረቡ ናቸው ።

አለማየሁ ሞገስ /1984/ «Traditional Ethiopian Medicine» ይህ ለኮንፍረንስ የቀረበ የባህላዊ መድሃኒት የጥናት ጽሑፍ ትኩረት የሰጠው፣ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትምህርት ሰልጥነው የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያ ለመሆን የሚፈልጉ ሰዎች የሚያልፉበትን መንገድ ከማሳየቱ ላይ ነው ። በ«ደብተራ» ማዕረግ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያ ለመሆን የሚፈልግ እውቀቱ ወደ አለው ሰው ሂዶ ጥብቁን ሥነ ሥርዓት ማክበርና ቃል ኪዳን መግባት እንደሚጠበቅበትና በአብዛኛው የቀደመውን ባለሙያ ረጅም ጊዜ በማገልገል የሚገኝ

የእውቀት ዘርፍ እንደሆነም በጥናቱ ላይ ተገልጿል ። ውስንም ቢሆን ከቤተሰብ እውቀት ሊወርስ እንደሚችልም ተጠቁሟል ።

መድሃኒቶቹን ለመሰብሰብ /ለማዘጋጀትም/ ከወቅት ፀደይ፣ ከወር መስከረምና ጳጉሜ፣ ከቀን ረቡዕና ዓርብ፣ ከሰዓት ንጋት አካባቢ እንደሚመረጥ ሲጠቅሱ፣ ከትልቅ ሰው ይልቅ ልጆች ሳይነጋገሩና ሳይሸኑ የሚፈለገውን የመድሃኒት ክፍል ቢሰበስቡ ፍቱን መሆኑን አጥኚው ጠቅሰዋል ። ፈውሱ ከስርዓቱ እንጂ ከመድሃኒት እንዳልሆነ በሚያሳይ ሁኔታ፤ እጅግ መንፃትና ዕፅን ማክበር ይገባል። ካልሆነ መድሃኒቱ ፈዋሽነት አይኖረውም የሚል በጥናታዊ ጽሑፉ ሰፍሯል ።

የኢትዮጵያ የባህል መድሃኒት በውጭ ዜጎች ተጽፎ የተገኘው ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሆነ «PANKHURST /1965/ « AN HISTORICAL EXAMINATION OF TRADITIONAL ETHIOPIAN MEDICINE AND SURGERY» በሚል ጥናታዊ ጽሑፋቸው ላይ ገልጸዋል። በአገር አሳሽነትና በሚሽነሪ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በጉዞና በታሪክ መጽሐፋቸው ያሰፈሩት እንጂ የኢትዮጵያ ባህላዊ መድሃኒት መረጃ ራሱን ችሎ በተጠና መልኩ የቀረበ አይደለም። በገጠመኝ እና በምልከታ ዘገባ ላይ የተመረኮዘ መሆኑን በጥናቱ ተገልጿል ።

ራሱን የቻለ የባህላዊ መድሃኒት ጥናት የሚገኘው በ20ኛ ክፍለ ዘመን ነው ። ከላይ በተጠቀሰው ጥናታዊ ጽሑፋቸው በኢትዮጵያ የሚታወቁ ዋና ዋና በሽታዎችን በማውሳት ከጥንት ጀምሮ ህብረተሰቡ የሚከላከልበትን መንገድ የሚዳስስ ነው ። ቦታውን፣ ወቅቱን፣ ዓመተ ምህረቱንና በጊዜው የነበረውን ንጉሥ እየጠቀሱ በሽታዎች በተለያየ ዘመን በህብረተሰቡ ላይ ያደረሱትን ጥፋትና ይወሰድ የነበረውን መከላከያ ገልፀዋል። በዚያ ዘመን ፈንጣጣ፣ ኮሌራ፣ /ወረርሽኝ/ ታይፈስ፣ የቁምጥና በሽታ፣ ማናንሼ /ዝሆኔ/፣ የከብቶች በሽታ /ጉመዬ/ ከተጠቀሱት በሽታዎች መካከል ይገኛሉ ።

በፍል ውሃ፣ በፀበል ከ7-14 ቀን በመጠመቅ፣ በሽተኛውን ማግለል ወይም በሽታው ከገባበት አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ መሰደድ፣ ከመከላከያ መንገዶቹ መካከል የተጠቀሱ ናቸው ። አንዳንድ የወረርሽኝ በሽታዎች በእግዚአብሔር ቅጣት የመጡ ናቸው ተብሎ ስለሚታመን የሚወሰደው የፈውስ መንገድም ከእምነቱ ጋር የተያያዘ እንደነበር አጥኚው ጠቁመዋል ። እንደየአካባቢው ሁኔታ፣ በባህላዊ መንገድ ለየበሽታዎቹ የሚወሰደው መድሃኒትም ፈጽሞ ሳይንሳዊ አይደለም ለማለት አይቻልም ብለዋል። የተቅማጥ፣ የውልቃት፣ የስብራት፣ የልዩ ልዩ በሽታዎች ህክምናና በቀዶ ጥገና አንጀት እስከ ማከም ድረስ በኢትዮጵያ የባህላዊ

ህክምና ይካሄድ እንደነበር Dr. Merab የፃፉትን መረጃ ጠቅሰው አቅርበዋል :: እ.ኤ.አ. በ1890ዎቹ የፈንጣጣ በሽታ ክትባት በባህላዊ ህክምና ይሰጥ እንደነበርም ጠቅሰዋል /1965:163/ ማር፣ ቅቤ፣ የበግ ላት፣ የተለያዩ ተክሎች ልዩ ልዩ ክፍሎቻቸው በመድሃኒት ያገለግሉ እንደነበር በጥናታቸው አውስተዋል ::

Elsabeth Dorothea /1976/ « Traditional Medicine and Magic among the Amhara of Ethiopia » ጥናቱን ያካሄዱበት ህብረተሰብ የብዙዎቹን በሽታዎች የህመም ምልክት በቀላሉ ይለያቸዋል ይላሉ:: አስከፊ የወረርሽኝ በሽታንና ሌሎችን በአንድ ወገን በሰይጣን ልክፍት ይመጣሉ የተባሉትን ደግሞ በሌላ ወገን መድበው ተመልክተዋቸዋል :: ክፉ ወረርሽኝ በሰው ልጅ ጥፋት እግዚአብሔር ለቅጣት የላከው ነው ተብሎ ይታመናል :: ከእግዚአብሔር ምህረት ለማግኘትም በቄሶች መሪነት ፀሎት ይደረጋል ብለዋል ::

በጥናቱ ስፊ ሽፋን ያገኙት ከሰይጣን ይመጣሉ ከሚባሉት ዛር፣ አይነ-ጥላ፣ ጥላ-ወጊ፣ ክፉ መንፈስና የመሳሰሉት ናቸው :: በሰይጣን ይመጣሉ ተብለው ለሚታመኑ በሽታዎች በአስማት፣ ደንቃራ በመጣል ፣ በእግዚአብሔር ስም በማጥመቅና በጠንቋይ ምሪት ፈውስ ይገኛል ተብሎ እንደሚታመን ተገልጿል :: በእግዚአብሔር ቁጣ የተላኩ ናቸው የሚባሉት በሽታዎችም ሆነ በሰይጣን በኩል ይከሰታሉ ለሚባሉት በሽታዎች ህብረተሰቡ በመአድን ውሃ፣ በፍል-ውሃና በፀሎት ፈውስ ለማግኘት እንደሚገለገል በጥናታቸው አረጋግጠዋል ::

የተጠቀሱት ጥናታዊ ሥራዎች፣ አጥኚዎቹ እንደመጡበት የትምህርት ክፍል /ከታሪክ፣ ከጂኦግራፊና ከሶሻል አንትሮፖሎጂ/ አንጻር የተመለከቱት ቢሆንም «በባህላዊ መድሃኒት ህክምና» ላይ የተካሄዱ ጥናቶች በመሆናቸው ከእኔ ሥራ ጋር ይመሳሰላሉ ::

የእኔ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ ላይ የሚያተኩር ሆኖ ባህላዊ መድሃኒቶች የሚዘጋጁበት የተፈጥሮ ሃብትና የአዘገጃጀታቸውን ሂደት ደንብና መነሻ የሚመረምር እና እምነት በባህላዊ መድሃኒት ላይ ያለውን ቦታ የተመለከተ ነው :: ዘመናዊ ህክምና በብዛትና በጥራት የሚሰጥበት የአገሪቱ ዋና ከተማ ላይ ባህላዊ መድሃኒት በስፋት የሚሰጥበትን ምክንያት ከመዳሰሱ በላይ ለህክምና አገልግሎት የሚውሉት መድሃኒቶች መገኛም ተካቷል::

## 2.2 የንድፈ ሃሳብ ቅኝት

ባህላዊ መድሃኒት አንድ አገር ወይም አንድ የተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ብቻ የሚጠቀምበት አይደለም :: ታሪክ ከሚያስታውስበት ጊዜ ጀምሮ በማንኛውም አገር አገልግሎት የሰጠ፣

ዛሬም እየሰጠ ያለ የእውቀት ዘርፍ ነው:: ለባህላዊ መድሃኒት ትኩረት ሲሰጠው የሚገባው፣ የተፈጥሮ ሃብት ያለውን ኃይል ለሰው ልጅ የተዛባ ጤና ማስተካከያ ስለሚውል ነው ::

ባህላዊ የህክምና ጥበቡ፣ እንደየአገሩ፣ የአየር ሁኔታ፣ የመሬት አቀማመጥ፣ እንደሚነሱ የበሽታ አይነቶች እንዲሁም እንደየህብረተሰቡ ባህልና እምነት መሠረት የሚለያዩ መሆኑን በመስኩ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ገልጸዋል /African Folklore: Encyclopdia: 2004:247/::

የክርስትና እምነት መሠረት የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ባህላዊ የህክምና አገልግሎት ከጥንት ጀምሮ ይሰጥ እንደነበር መረጃ ይሰጣል :: የይሁዳ ንጉስ የነበረው ሕዝቅያስ፣ ተስፋ የሚያስቆርጥ የእባጭ ህመም ያሰቃየው በነበረ ጊዜ፣ የበለስ ቅጠል ተቀጥቅጦ ከእባጩ ላይ ሲደረግለት ፈውስ አግኝቷል:: ይህም ከዕፅዋት መድሃኒት እንደሚገኝ ያረጋግጥልናል /2ኛ ነገሥት 20 ፣7/ ኢሳ. 38፣21/ ሕዝ. 47፣12/::

በ African Folklore : Encyclopedia /2004፣ 247-278/ የባህላዊ ህክምና ጥበብ፣ ባህላዊ የህክምና መገልገያዎችን በመጠቀም የተዛባው ጤና ወደ ነበረበት መመለስ ነው :: እውቀቱ ግን የተገኘው ከዘመናዊ የህክምና ጥበብ አይደለም የሚል ተጽፏል ::

የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ግንኙነትና በተፈጥሮም የመጠቀም አቅሙ የሚገለጽበት አንዱ መንገድ ባህላዊ መድሃኒት ሆኖ ቀርቧል:: በሌላም በኩል ሰው ካለው ባህላዊ ግንዛቤ ተነስቶ ከሚታይና ከማይታይ አለም ጋር ያለውን ግንኙነት ባህላዊ መድሃኒት እንደሚያሳይ እንደሚከተለው ተገልጿል ::

«Various types of traditinal medicines and related practices are appllied on the basis of folk theories about the relationship between the power of the visible and the invisible worlds as well as God, ancestors, the spitits, and human beings » /African Folklore: Encyclopedia, : 2004 :248/

ባህላዊ መድሃኒት በተለያዩ አጥኚዎች ጠቃሚነቱ ተረጋግጧል :: የሰለጠነው አለም ሳይቀር ዛሬም ይጠቀምበታል :: Watson /1988:XIV/ የባህላዊ መድሃኒት፣ ባህላዊ በሆነ መንገድ ህብረተሰቡንና ጤናን የሚታደግ፣ ዛሬም በስፋት በሰለጠነው አለም ሳይቀር አገልግሎት እየሰጠ ያለ መሆኑን ጽፏል ::

የዘመናዊ ዝንባቡዌን የባህላዊ መድሃኒት አጥንተው መጽሐፍ ያሳተሙት Chavunduk ባህላዊ ህክምና መቀጠል ይኖርበታል:: ምክንያቱም ዘመናዊ ህክምና የማይፈውሳቸውን በሽታዎች ያድናልና ብለዋል:: " Traditional medicine has also persisted because of the failure of modern medical science to get better or even good results in certain types of illness. This is particularly true in the area of chronic dysfunctions" /1994:10/.

በአገራችንም ስለ ባህላዊ መድሃኒት ያለው ግንዛቤና አጠቃቀም ተመሳሳይ ነው :: የባህል መድሃኒት በተመለከተ የተፃፉ መጻሕፍትም ተመሳሳይ ይዘት አላቸው :: በርከት ያሉ ቀደምትና የቅርብ ጊዜ መጽሐፎችን ያጣቀሰ «ጤናችን በቤታችን» የሚል የባህላዊ መድሃኒት መጽሐፍ፣ የባህላዊ መድሃኒትን በሚከተለው መልኩ ገልፆታል ::

> ባህላዊ ህክምና ብሔራዊ ቅርስና ሃብት ነው:: ባህላዊ ህክምና በአገራችን ረጅም ታሪክና አስተዋጽኦ ያለው ዘርፍ ነው:: በአገራችን ባህላዊ ህክምና ዘመናዊ ህክምና ከመጀመሩ በፊትም ሆነ ከዚያ ወዲህ በስፋት የሚሰራበትና ጉልህ ድርሻ ያለው ነው:: ዛሬም ቢሆን ለአብዛኛው ህዝብ ህክምና አገልግሎት ይሰጣል :: በተለይም በገጠሩ አካባቢ የሚሸፍነው ባህላዊ የህክምና ዘዴ ነው:: ይህን እውቀት ልናዳብረውም ልንጠብቀውም ይገባናል /በቀለች፣ 1999:1/ ::

ባህላዊ ህክምና ፍፁም ፈዋሽ ነው ባይባልም በህክምናው ዘርፍ ሰፊ ድርሻ ያለው መሆኑን ከቀረቡት መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል ::

### 2.2.1 የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች

የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች ከሚኖሩበት ህብረተሰብ እውቀቱን የቀሰሙ ናቸው :: ለሚኖሩበት ህብረተሰብም አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው:: አግልግሎቱን የሚሰጡት በአካባቢው ከሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች መድሃኒቶችን በማዘጋጀት ነው::

መንፈሳዊ ኃይል አላቸው የሚባሉትም ከአካባቢው እምነት ጋር የተያያዘ የፈውስ አገልግሎት ይሰጣሉ :: ሁለቱም የህክምና ባለሙያዎች በህብረተሰቡ ዘንድ እውቅና ያላቸው ናቸው :: ፈቃዱ ስለባህላዊ ሃኪም በስፋት ከጻፉት መካከል የሚከተለው ይገኝበታል::

> ....a person who is recognized by the community in which he lives as competent to provide health care by using vegetable, animal and mineral substances and certain

other methods based on social cultural and religous background as well as the knowledge attitudes and beliefs that are prevalent in the community regarding physical, mental and social well being and the causation of disease and disability /2001 : 2/.

ከህብረተሰቡ፣ ባህልና፣ ሃይማኖት በተገኘ እውቀት፣ ዝንባሌና እምነት መሠረት፣ መድሃኒቶችን ከእፅዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት እንዲሁም ሌሎች ስልቶች በመጠቀም ማዘጋጀትና የአካልና የአዕምሮ ጤና ጉድለትን በማከምና ለህብረተሰቡ ደህንነት ባበረከተው አስተዋፅኦ እውቅና የተሰጠው ሰው ነው፣ የባህላዊ መድሃኒት ሃኪም የሚባለው ::

የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች፣ እንደየመጡበት የእውቀት ዘርፍና እንደሚሰጡት አገልግሎት፣ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሁራን በሁለት ይከፍሏቸዋል :: ከእጽዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት ተዋጽኦ ለህሙማን መፈወሻ መድሃኒት የሚያዘጋጁትንና ወጌሻዎችን በአንድ ምድብ፣ ልዩ ተሰጥዖ አላቸው የሚባሉትን መንፈሳዊ ሃኪሞች ደግሞ በሌላ ምድብ ይፈርጇቸዋል :: (ፊቃዱ፣ 2001:2)

የመጀመሪያው ምድብ፣ የባህል ሃኪሞች እውቀቱን በሙከራ፣ ከስህተት በመማርና ለረጅም ጊዜ ምልከታ በማድረግ የሚያዳብሩ እንደሆኑ Chaunduk (1994 :10) እና Watson /1988 :10/ ገልጸዋል ::

እነዚህ ሃኪሞች በአብዛኛው በተግባር የሚለማመዱና የህክምናውን ችሎታም ቀስ በቀስ የሚያዳብሩ ናቸው :: አነስተኛም ቢሆን የጽሁፍ መመሪያ ያላቸው አሉ:: ነገር ግን ያገኙትን ባህላዊ የህክምና ጥበብ ለማንም የሚያካፍሉ አይደሉም፤ ምክንያታቸው ደግሞ ይረክሳል የሚል ነው::

### 2.2.2 ሃይማኖትና እምነት በባህላዊ መድሃኒት ላይ

ሃይማኖትና እምነት በባህላዊ መድሃኒት ላይ ትልቅ ቦታ አላቸው:: Watson /1988 :10/ እና Roundy/1976 :113/ መንፈሳዊ የባህል ህክምና ባለሙያዎች በገጠርም ሆነ በከተማ ከያዙት እምነት ጋር እንደሚያገናኙት በጥናታዊ ጽሑፋቸው ላይ አስፍረዋል :: ፈውስን የሚያካሂዱት በራሳቸው ችሎታ ተማምነው ሳይሆን ሌላ ሀይል እንደሚያደርግላቸው በማመን ነው :: ያነጋገርኳቸውም ባህላዊ ሃኪሞች የህክምና ጥበቡን ከፈጣሪ እንዳገኙት

ይናገራሉ:: ህብረተሰቡም አምኖ ወደ እነሱ ለፈውስ ይሄዳል:: ለዚህ ተጠቃሽ የሚሆነው ህብረተሰቡ፣ ስለ በሽታ ያለው አመለካከት ነው::

Ole Peter /1993:101/ እግዚአብሔር ሳያውቀው ድንገተኛ ችግርም ሆነ በሽታ በአጋጣሚ አያመጣም:: ነገር ግን እግዚአብሔር በሰው ልጅ ሲያዝን ለእርማት ወይም ለቅጣት በሽታን ሊልክ ይችላል ይባላል:: ለዚህ መሰል በሽታ ፈውስ የሚገኘው ደግሞ በእምነት ላይ በተመሰረተ ህክምና ነው:: ለዚህም ተጠቃሹ ፀበል ነው:: መፅሐፍ ቅዱስ ላይም ተጠቅሷል:: ቤተ ሳይዳ የነበረው መጠመቂያ ውሃ የእግዚአብሔር መልዓክ ሲያንቀሳቅሰው በሽተኞች እየገቡ ይፈወሱ ነበር ይላል /ዮሐ፣ 5:41/ ::

Roundy /1976:111/ የታመሙ ሰዎች ከሩቅ ቦታ ሣይቀር የማዳን ኃይል አለው ወደ ተባለ ፍል-ውሃና የማዕድን ውሃ እንደሚሰባሰቡ ገልጿል:: ይህ ደግሞ የባህላዊ መድሃኒትንና የእምነትን ግንኙነት የሚያስረዳ ነው:: ቤተክርስቲያንም የራሷን ባህላዊ መድሃኒት የምታዘጋጅበት ሁኔታ እንዳለ Ole Peter/1993:101/ ገልጿል::

በአገራችንም ሜሮን /ቅብዓ ቅዱስ/ ቤተክርስቲያን የምትሰጠው መድሃኒት ነው:: ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ማርቆስ 6 ÷13፣ ሉቃስ 10÷33-34 እና ያዕቆብ 5÷14 ላይ ያለውን መሠረት በማድረግ የሚከናወን ነው:: «ብዙ አጋንንትንም አወጡ ብዙ ድውያንንም ዘይት እየቀቡ ፈወሷቸው» /ማርቆስ 6÷13/::

ሌላው ፈውስ ማግኛ በእምነት የሚካሂድ ፀሎት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህም መረጃ አለው:: ሰዎች መፍትሄ ላጡለት የጤና ችግር ወደ ፈጣሪ በእምነት በመቅረብና በፀሎት በመለመን በተአምር የሚዳንበት እንደሆነ የሐዋርያት ሥራ 9÷36-42 ባለው ላይ ተጠቅሷል::

«ጴጥሮስም ሁሉን ካስወጣ በኋላ ተንበርክኮ ፀለየ ወደ በድንዋም መለስ ብሎ 'ጣቢታ ሆይ ተነሽ' አላት እርስዋም አይኖችዋን ገለጠች ያንጊዜም ጴጥሮስን አየችው ቀና ብላም ተቀመጠች:: እጁንም ለእርስዋ ሰጥቶ አስነሣት፣ ቅዱሳንንና ባልቴቶችንም ጠርቶ እርስዋን አድኖ ሰጣቸው» /የሐዋ 9÷40-41/:: ሙዝሊሙ ህብረተሰብ፣ ፊውስ ከፈጣሪ የሚገኝ መሆኑን ያምናል :: «ተአምራዊ ፈውስ »በሚለው ኢስላማዊ ህክምና መጽፍ ላይ የሰፈረው ለዚህ አብነት ይሆናል :: «ሙስሊም የሆነ ሰው ሁሉ ይህን የአላህ ቃል አምኖ በመቀበልና በአላህ ፈዋሽነትም በመመካት መለኮታዊና ተአምራዊ ኃይል በሆነው ተፈጥሯዊ መድሃኒት መጠቀም ብልህነት ነው» (1996፣25) የክርስትናም ሆነ የእስልምና እምነት ተከታዮች ፈውስን ከእምነት ጋር ያያይዙታል :: ሃኪምና መድሃኒት ምክንያት ነው :: ፈዋሹ ፈጣሪ፣ እንደሆነ የሚያምኑ ታካሚዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል ::

## 3. የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች አጠቃላይ ዳራ

በአዲስ አበባ የሚገኙ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ወንዶች ናቸው ። በዝቅተኛና በከፍተኛ ደረጃ ነዋሪዎች አካባቢ ህክምናው ይሰጣል ። የእርስ በርስ ግንኙነታቸውም ዝቅተኛ ነው ።

### 3.1 የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች ማስተዋወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ሁሉም ወንዶች ናቸው። እድሚያቸው በ25 እና በ91 መካከል የሚገኝ ነው። ሴት የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያ ለምን እንደሌለ ጠይቄአቸው፦ ሃኪም ተክሌ ኃ/ገብርኤል እንዲህ ብለውኛል ።

> የባህል መድሃኒት ብዙ መስዋዕት ተከፍሎበት ወደዚህ ደረጃ መጣ እንጂ በፊተኛው ጊዜ አስፈሪ ወይም አስቀያሚ ስም ስለነበረው እንኳን ሴቶቹ ወንዶችም አይፈልጉም። ይሄንን ልጄን አሁን ከኔ ጋር የሚሠራው በስንት መከራ ነው ጉትቼ እያሳመንኩ ነው ወደዚህ ያመጣሁት። ሰው ሥራ ሥር ማሽ ይሉናል፣ ቅጠል በጣሽ ይሉናል። ጠንቋይ ይሉናል፣ ሌላ ስም ስለሚሰጥ ጉጂ ባህል ነው በሚል እየተጣለ ነው፣ /ካሴት ቁጥር1፣ሚያዝያ 9/2000 /

ሃኪም እርገጤ ከበደ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና እንዲጠላ ያደረጉት ከአገር ውጭ የመጡ መነኮሳት /ተሳዓቱ ቅዱሳት/ ሃኪም እርገጤ ከበደ፣ እንደነገሩኝ፣ ከኢትዮጵያ ውጭ የመጡ ዘጠኙ መነኮሳት ነን ባዮች፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በሥልጣኔ እንዳይገፋ፣ ያለውን ጥበብ ማጥላላትና ብዙ በዓላትን በመስጠት ሥራ ማስፈታት፣ ሰውን ሁሉ ሲያል በላህ በማለት የጥበብ ሥራውን ማስተው ይገባል፣ የሚል ሃሳብ ያመነጩና በተግባርም ያዋሉ ናቸው። በአደረሱት ተጽዕኖ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና እውቀቱ ጫጫ፣ በሚስጢር እንዲያዝና ህብረተሰቡ መጥፎ ስም እንዲሰጠው መደረጉን ጠቅሰዋል።
«ይሄ ትምህርት፣ ይሄ እውቀት አባቶች አሁንም በሚስጢር ይዘው በየገዳማቱ በየቤተክርስቲያኑ በየመስጊዱ ደብቀው ለተለያዩ ሰዎች በሚስጢር ማስተላለፍ ተጀመረ። ያንን ማድረግ ምን ተባለ ሥር ያዥ ቅጠል በጣሽ ጥላ ወጊ፣ ጋኔን ሳቢ የሚል ጥላቻ በህብረተሰቡ ውስጥ አደገ።» /ካሴት ቁጥር 2፣ ሚያዚያ 10/2000 ዓ.ም/

ከዘመናዊ የህክምና ስርዓት ጋር ለመቀራረብ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ገዋን ይለብሳሉ፣ ጓንት ይጠቀማሉ፣ ማዳመጫ አላቸው እንዲሁም የሚመረምሩበትና የሚያክሙበት አልጋ ያላቸው ተመልክቻለሁ።

ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ የሆኑልኝ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ለአዘጋጀኋቸው ጥያቄዎች መልስ ሰጥተውኛል:: በምልከታዬ ወቅት ጥያቄ ለፈጠሩብኝና ከምልሳቸው በመነሳት ለጠየኩዋቸው ጥያቄዎች ትብብራቸውን አልነፈጉኝም::

በቃለ መጠይቁ፣ ጤና ጥበቃ የባህላዊ ህክምናን ዘርፍ ማጠናከርና መልክ ማስያዝ እንደሚፈልግ ተገልጸልኛል:: በሚኔስትሮች ምክር ቤት እንዲፀድቅ የወጣ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ረቂቅ ፖሊሲ 2000 ዓ.ም ደንብ ቁጥር የሌለው ከተሰጡኝ የጽሑፍ መረጃዎች አንዱ ነው::

> የባህላዊ ህክምና መድሃኒቶችን የመመዝገብ እንዲሁም የማምረት፣ የማስመጣት፣ የማከፋፈልና የማሰራጨት ፈቃድ የመስጠት ኃላፊነት የመድሃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ይሆናል:: (ረቂቅ ፖሊሲ ክፍል 6፣8) የባህል መድሃኒት በማከማቸት ፣ በማዋሃድ ፣በማደባለቅና በማዘጋጀት የተሰማራ ማንኛውም ሰው ስለ ባህላዊ መድሃኒቱ ምንጭ በቂ መረጃ ሊኖረው ይገባል:: ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍም መድሃኒቱን ማስመዝገብ ይኖርባታል:: (ረቂቅ ፖሊስ ክፍል 6፣9)

እስከ አሁን በአለው ሁኔታ በጤና ጠበቃና በባህላዊ ባለሙያዎች መካከል ያለው ግንኙነነት የላላ መሆኑን አህመድ ዘይኑ በቃለ-መጠይቁ ወቅት ገልጸልኛል:: በንጉሡና በደርግ ዘመነ መንግሥት የተደረገ መጠነኛ የማደራጀት፣ ሥርዓት የማስያዝና የባህላዊ ህክምና ዘርፍን የማሳደግ ጥረት የነበረ ቢሆንም ተከታታይ እንዳልነበር ፣ ከቃለ መጠይቁና ከተሰጡኝ የጽሁፍ መረጃዎች ለመረዳት ችያለሁ::

በንጉሱ ዘመን በ1941 ዓ.ም የባህላዊ ህክምናን የተመለከተ በነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ወጥቷል:: በደርግ ዘመን ደግሞ የማደራጀት እንቅስቃሴ ነበር::

> In 1985, a committee of experts was set up by the ministry of health to look into ways and means of strengthening traditional medicine in Ethiopia. The committee recommended that legislation be enacted for the promotion and official utilization of traditional medicine. Furthermore, it suggested that the office of traditional medicine be expanded, its budget be increased, more personal be trained at the PH.D level, and the office be expanded and restructured organizationally (Fekadu: 2001:18) .

እ.ኤ.አ በ1985 ዓ.ም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የኢትዮጵያን የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ዝርፍ ለማጠናከር የባለሙያዎች ኮሚቴ /ቡድን/ አቋቁሞ ነበር:: ለተቋቋመው ኮሚቴ የባህላዊ መድሃኒት ህክምናን እንዲያሣድግና ከዘርፉም ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል ሥራ እንዲሰራ ሥልጣን ነበረው:: እንዲሁም የባህላዊ መድሃኒት ቢሮዎች ተስፋፍተውና በጀት ተጨምሮ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ድረስ ማሰልጠን የሚያስችል መዋቅር እንዲዘረጋም ተጨማሪ ኃላፊነት ተሰጥቶትም ነበር::

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች «ፈለገ ግዮን የባህል መድሃኒት ምርምርና ህክምና ማህበር» በሚል መጠሪያ ጳጉሜ 4/1996 ዓ.ም ማህበር የመሠረቱበትን መረጃ ከጤና ጥበቃ ያገኘሁ ቢሆንም፣ ከ80% በላይ የህክምና ሽፋን ይሰጣል የሚባልለት ባህላዊ የህክምና ዘርፍ፣በጤና ጥበቃ በኩል ስለባህላዊ ሃኪሞቹ፣ስለህክምና አሰጣጡና ስለታካሚዎች የተጠናከረ መረጃ የለውም::

የባህል ህክምና ባለሙያዎች ከፍትህ ሚኒስቴር ባገኙት ፈቃድና በመሠረቱት ማህበር አማካይነት የህክምና ፈቃድ ለአባሎቻቸው ይሰጡ እንደነበር ከጤና ጥበቃ መሃመድ ዘይኑ ገልያልኛል:: ከ2000 ዓ.ም ህዳር ወር ጀምሮ ማህበሩ ታግዷል:: ከጤና ጥበቃ የአገኘሁት መረጃ እንደሚያመለክተው የባህላዊ ህክምና ፖሊሲ ወጥቶለት መስፈርት ኖሮት፣ መሥፈርቱን የሚያሟሉ ፈቃድ ከአገኙ በኋላ፣ የሙያ ማህበሩ መመስረት አለበት:: ይህን ለማድረግ ደግሞ የወጣው ረቂቅ ፖሊሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መጽደቅ ይኖርበታል የሚል ነው::

በኢትዮጵያ ከዘጠኝ ሺ በላይ አሉ የሚባሉትን የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች በአግባቡ ማደራጀትና የህክምና አሰጣጣቸውን ማስተካከል ያልተቻለው ዘመናዊ የህክምና ተቋም ባለመስፋፋቱና የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች እጥረት በመኖሩ ነው ተብሏል:: (መሃመድ ካሴት ቁጥር 5፣ሚያዝያ 22/2000 ዓ.ም)

የአዲስ አበባ ጤና ቢሮም የትብብር ደብዳቤየን ተቀብሎ በጐ ምላሽ ሰጥቶኛል:: የፋርማሲና የባህላዊ ህክምና ቡድን መሪ የሆኑት እዝራ ሙሉነህ፣ በአዲስ አበባ ጤና ቢሮና በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የባህላዊ ህክምና መድሃኒት ባለሙያዎች መካከል በተለያየ ጊዜ ለመቀራረብ የተቀናጀ ሥራ ለመሥራት ተሞክሮ አልተሳካም ብለውኛል:: የተለዋወጧቸውንም የጽሁፍ መረጃዎች[3] ሰጥተውኛል::

---

[3]የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ አዲስ አበባ ከሚገኙ የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ጋር የተለዋወጧቸው ደብዳቤዎች

ከጤና ጥበቃም ሆነ ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ያገኘሁት የቃለ መጠይቅና የጽሁፍ መረጃ የሚያመለክተው የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ሰፊ ድርሻ እንዳለው ይህ በአገራችን ብቻ ሣይሆን በህንድ በቻይና፣በጃፓን . . . የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የጐላ መሆኑንም ገልፀው፣ ፀድቆ በሚወጣው ፖሊሲና መመሪያ መሠረት በአግባቡ ተጠናክሮ ሊቀጥልና ሃገራችንም ለመድሃኒት የምታወጣውን ከፍተኛ ወጭ ሊያግዛት እንደሚችል መሀመድ ዘይኑ /ካሴት ቁጥር 5፣ ሚያዝያ 22/2000 ዓ.ም/ እዝራ ሙሉነህ / /ካሴት ቁጥር 7፣ ሚያዝያ 28/2000 ዓ.ም/ ተናግረዋል፡፡

## 3.2 የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች በአዲስ አበባ ከተማ ህክምውን የሚሰጡበት አካባቢ ፡፡

በዚህ ጥናት ለማካተት የተመረጡት የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች፣ ህክምናውን የሚሰጡበት አካባቢ ከአዲስ አበባ ከተማ አቀማመጥ ጋር የተዛመደ እንዲሆን ጥራት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም አራቱን አቅጣጫዎች የሚወክሉና በሚሰጡት የህክምና አገልግሎት እውቅና ያላቸው ቃለ መጠይቅ ተደርጐላቸዋል፡፡

በሰሜን አቅጣጫ ሃኪም ተክሌ ኃብተ ገብርኤልንና ሃኪም ሃጂ ኑሩ አደምን ምልከታና ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ችያለሁ፡፡ ሃኪም ተክሌ ህክምናውን የሚሰጡት፣ ቀጨኔ መድሃኒዓለም እጅግ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸው ሰዎች የሚገኙበትና የተጨናነቀ ሰፈር ነው፡፡ ሃኪም ሃጂ ኑሩ አደም ሽጐሌ አንበሳ ጋራዥ ፊት ለፊት ሕክምናውን የሚሰጡበት አካባቢ የተሻለ ሰፈር ነው፡፡

ደቡብ አቅጣጫ ሃኪም ማሞ ኃይሌንና ሃኪም እርገጤ ከበደን ተጠኝ አድርጌ በተለያዩ ጊዜያት ምልከታና ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ፡፡ የሃኪም ማሞ ኃይሌ የህክምና መስጫ ቦታ ሳሪስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን አጠገብ ነው፡፡ የተስተካከለ መንገድ፣ ዘመናዊ ቤቶችና ዘመናዊ አኗኗር የሚታይበት ሰፈር ነው፡፡ ሃኪም እርገጤ ከበደ ህክምናውን የሚሰጡበት ቦታ መሿለኪያ ሃዲድ ገበያ ነው፡፡ መተላለፊያ መንገድ የሌለው፣ የተያያዘ ቤት ያለበት ዘመናዊነት ቀርቶ ችግሩም መጠን የሌለበት ጉስቋላ ሰፈር ነው፡፡

በምስራቅ፣ ሃኪም መሪጌታ ተውህቦ ምህረትንና ሃኪም ፍቅረሰብ መኮነን ተጠኝ አድርጌ፣ በሁለቱም የህክምና መስጫ ቦታዎች በተደጋጋሚ ምልከታ የማድረግ እድል ሳገኝ፣ የመሪጌታ ተውህቦ ምህረት ቃለ መጠይቅ ግን አልተሣካም፡፡ ፍቅረሰብ መኮነን አክሱም

ሆቴል ጐን በትልቅ ቪላ ነው ህክምናውን የሚሰጡት:: አካባቢው የተሻለ ኑሮ ያላቸው ሰዎች የሚገኙበት ነው::

በምዕራብ አዲስ አበባ በኩል አቡበከር አህመድና ሃኪም ደጀኔ ብሩ የመረጃ ምንጭ ናቸው:: ከሃኪም አቡበከር አህመድ አየር ጤና ምልከታ በማድረግ በቃለ መጠይቅም መረጃዎችን ለማግኘት ችያለሁ:: ህክምናውን የሚሰጡት አየር ጤና ከአደባባዩ ወደ ጅማ መንገድ ሁለት ፌርማታ ርቆ ከሚገኘው ቦታ ነው:: አካባቢው ከከተማ ዳር ሆኖ ህክምና የሚሰጡበት ቤት ግን ዘመናዊ ነው:: ሃኪም ደጀኔ ብሩ ልደታ፣ ባልቻ ሆስፒታል አጠገብ ህክምናውን ይሰጣሉ:: ያሉበት ሰፈር የተጨናነቀ ነው:: ቤታቸው መካከለኛ ደረጃ ያለው ነው::

የህክምና መስጫ ቦታዎችን በመጠኑ ለማየሳት የተሞከረው የባህላዊ መድሃኒት ህክምና በማንኛውም ቦታና በየትኛውም ጊዜ የሚገኝ መሆኑን ለመጠቆም ነው:: ከዚህ የተነሳ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ተጠቃሚዎች፣ የመክፈል አቅም የሌላቸው ናቸው፣ ወይም አካባቢው የበሽታ መንስኤ ስለሆነ ነው የሚባለው ግምታዊ ማጠቃለያ በአዲስ አበባ ከተማ የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች ከሚገኙበት ስብጥር ስንነሳ አያስኬድም::

ዘመናዊ እውቀት ስለቀሰሙና ስለአልቀሰሙ ነው ማለትም አይቻልም፣ ምክንያቱም የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ሳይቀሩ በነባሩ የህክምና ስልት እንደሚገለገሉ ሁሉም የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች ገልጸውልኛል:: የባህላዊ መድሃኒት ህክምና አሰጣጥን ከገጠር ኗሪዎች ጋር ለማያያዝ ቢሞከርም ስህተት ይሆናል:: በአዲስ አበባ ከተማ እጅግ ቁጥሩ የበዛ ታካሚ አለና:: ማለት የሚቻለው ግን ነባሩ የህክምና ዘዴ ዛሬም በታላላቅ ከተሞች ውስጥ በስፋት ተግባራዊ እየሆነ መገኘቱን ነው:: በአገራችን ሥር የሰደደው ባህላዊው የህክምና ዘርፍ በህብረተሰቡ ውስጥ ስፍራ እንዳለውና ካለመሰልጠን ጋር የማያያዙ ግንዛቤ ተቀባይነት እንደሌለው ያስረዳል:: ለዚህ መረጃ ሊሆን የሚችለው ዘመናዊ ኑሮ በሚታይበት ዘመናዊ እውቀት በቀሰሙ ሰዎች በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎች የባህላዊ መድሃኒት ህክምናው በየቀኑ በእያንዳንዱ ሃኪም ከ10 እስከ 50 የሚደርሱ ሰዎች ሲታከሙ መታየታቸው ነው::

## 3.3 በባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች መካከል ያለው ግንኙነት

በ1941 ዓ.ም በወጣው የነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ መሠረት በ1985 ዓ.ም ከፍትህ ሚኒስቴር «የኢትዮጵያ የባህል መድሃኒት ጥናትና ቅመማ ህክምና ማህበር» በሚል መጠሪያ ለባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ፈቃድ ተሰጥቷቸው ነበር:: አገር አቀፍ ማህበር እንዳለ ሆኖ በአዲስ አበባ ሰባት (መሃመድ፣ ካሴት ቁጥር 5፣ ሚያዝያ 22/2000ዓ.ም) ሌሎች ማህበራት

ተመስርተውም ነበር:: በደርግ ዘመን በየክፍለ ሃገሩ በመዘዋወርም የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎችን ለማደራጀት ጥረት ተደርጎ ነበር:: ቀጥሎ የሰፈረው ደብዳቤ ይህንን ያመለክታል::

ግንቦት 17 ቀን 73 ዓ.ም

በህብረተሰባዊነት ኢትዮጵያ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት
ለጎጃም ክፍለ ሃገር
ለሚመለከተው ሁሉ
አቶ ተክሌ ሀ/ገብርኤል

ስማቸው ከላይ የተጠቀሰው ግለሰብ ለሥራ ጉዳይ ወደ ጎጃም ክፍለ ሃገር የሃገር ባህል መድሃኒት ቅመማና ባህላዊ ህክምና ድርጅት የላካቸው ስለሆነ ለሚገጥማቸው ችግር ሁሉ ሙሉ ትብብር ታደርጉላቸው ዘንድ ለሚደረግላቸው ትብብር በቅድሚያ እናመሰግናለን::

ፊርማ የማይነበብ፣ ክብ ማህተም አለበት::

ይህ ሁሉ እንቅስቃሴ ተደርጎ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች ለመሰባሰብና የጋራ እድገት ለማምጣት አለመቻላቸውን ያገኘኋቸው መረጃዎች ያረጋግጣሉ:: በማህበር ተደራጅቶ ሙያውን ከማሳደግ ይልቅ በሙያ ማኅበሩ ጥላ ስር የአባልነት መታወቂያና የህክምና ፈቃድ ከማግኘት እንዳላለፈ በወቅቱ የማህበሩ ምክትል ሊቀመንበር የነበሩት ሃኪም ተክሌ ኃብተገብርኤል ገልፀውልኛል:: (ካሴት ቁጥር 1: ሚያዝያ 9/2000 ዓ.ም)

ሃኪም ማሞ ኃይሌ፣ ጤና ጥበቃ ችሎታ ያለውንና የሌለውን ሃኪም መለየት አለበት ባይ ናቸው:: አያይዘው አገር አቀፉም ሆነ የአዲስ አበባ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ማህበራት እንዲጠናከር የበኩላቸውን ጥረት ቢያደርጉም እንዳልተሳካ ገልጸዋል:: ተደራጅተው ለመድሃኒትነት የሚጠቀሙባቸውን ዕፅዋት ለማልማት መንግስትን ለመጠየቅ ዕቅድ ይዘው ቢንቀሳቀሱም የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች እየተንሸራተቱ አስቸግረው ሳይሳካ መቅረቱን ተናግረዋል:: /ካሴት፣ ቁጥር 3: ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም/

የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ተቀራርበው ከመስራት ይልቅ መናናቅና ራስን ከፍ ማድረግ ያስቀድማሉ:: ከዚህ የተነሳ ሙያውም አላደገ፣ አገሪቱም ከዘርፉ ተጠቃሚ አልሆነችም::

ጤና ጥበቃም ሆነ መንግሥት ሙያችን እንዲጎለብት ሊያግዙ ይገባል ያሉት ደግሞ ሃጂ ኑሩ አደም ናቸው:: (ካሴት ቁጥር 4፣ ሚያዝያ 12/2000 ዓ.ም)

በቃለ መጠይቅ የጠየኳቸው የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ሁሉ ማለት ይቻላል፡ እንደ ጥንት እንደጧቱ ለየብቻ ወይም በድብቅ የሚያውቁትን መድሃኒት ለበሽተኞች እንደሚሰጡ በሚያስረዳ ሁኔታ ገልፀውልኛል::

ሃኪም እርገጡ ከበደ ግን «ሌቃ» በሚል መጠሪያ ከሌሎች የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ጋር ማህበር እንዳቋቋሙ ነግረውኛ:: ከመንግሥት ጋር በመተባበርም የባህላዊ መድሃኒት የህክምና ዘርፍ ት/ቤት የመክፈት እቅድ እንዳላቸውም ተረድቻለሁ:: /ካሴት ቁጥር 2፣ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም/ «ሌቃ» የሚል በባህላዊ መድሃት ህክምና ላይ የሚያተኩር በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ባለ 16 ገጽ ታብሎይድ[4] መጠን ያለው በሣምንት እሁድ እለት የሚወጣ ጋዜጣ አላቸው:: እሳቸውም ምክትል ዋና አዘጋጅ ናቸው::

በምልከታየ ወቅት ካስተዋልኩትና በቃለ መጠይቁ ከሰጡት ምላሽ መረዳት የቻልኩት፣ በአዲስ አበባ የሚገኙ የባህላዊ መድሃት ባለሙያዎች አብዛኛዎቹ ሚስጢር ነው «ጥበብ መርከስ የለበትም» (ፍቅረሰብ፣ ካሴት ቁጥር 8፣ ግንቦት 3/2000 ዓ.ም) የሚለው የቆየ አባባል ዛሬም በመካከላቸው ያለ መሆኑን ነው:: ጤና ጥበቃና አዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ ደግሞ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች የሚያውቋቸውን መድኒቶች በሚስጢር የሚይዙት፣ ኑሮአቸውን የሚገፉበት ስለሆነ ዋስትና ፈልገው ነው ብለዋል::

> ዕፁን እንዳለ ካሳየን ከነሙሉስሙና ከነአገልግቱ ከገለፅን እኛን ለምን ይፈልጉናል? ምክንያቱም መርማሪ ነን የሚሉት በዕፁ ይጠቀሙበታል:: ሁሉ ነገር ግልፅ ከሆነ በኋላ ደግሞ የእኛ አገልግሎት ምንድነው? ዋስትናችንስ ምንድነው? ከጥቅም ውጭ ነው የምንሆነው ፍራቻ አለብን /ሃኪም ተክሌ፣ ጦቢያ መጽሔት፣ ቅጽ 9፣ ቁጥር 3፣ 1994፣ 23/::

ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ዶ/ር አታላይ አለም የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች የሚያውቋቸውን ዕፀ መድሃኒት የሚደብቁት ከጥቅም ጋር አያይዘው ነው ይላሉ::

---

[4] ታብሎይድ መጠኑና የገጽ ብዛቱ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ የሚያንስ

በጤና ጥበቃም በኩል የባህል መድሃኒቶች ክፍል ተብሎ የተዋቀረ የምግብና የምርምር ኢንስቲትዩት ውስጥ አለ:: ስለዚህ መንግሥትም ይሄንን ነገር እንዲጣል፣ አይደለም ያለው:: እንዲያውም ክፍል አበጅቶለት ምርምሮቹ እየተካሄዱ ነው::

በተለይ ከቅጠላ ቅጠሎች የሚሰሩ መድሃኒቶችን በተመለከተ ትልቅ ገቢ የሚያስገኝ ነገር ስለሆነ ጥቅም ያለው ነገር ስለሆነ ለልጅ ልጆችን ደብቀን እናሳልፈዋለን እንጂ ከገለጥነውማ የኛ ነገር ጥቅም የሌለው ነገር ሆነ:: ተወሰደብን ከሚል አንፃር የሚደብቁ ሰዎች አሉ:: በደስታ ደግሞ ከእነዚህ ሰዎች ጋራ ምርምሩን ተባብረው የሚያካሂዱ ሰዎች አሉ:: ተቀናጅተው ቢሰሩ ለህብረተሰቡ የሚጠቅም ነገር ሊወጣ ይችላል ብዬ አስባለሁ:: /ካሴት ቁጥር 10፣ ግንቦት 29/2000 ዓ.ም/

በባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞችና በዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች መካከል እንዲሁ ሰፊ ርቀት አለ:: የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች እየሰጡት ያለው አገልግሎት ቦታ እንዳልተሰጠው፣ ያካበቱት ልምድና እውቀት እንደተናቀ ይናገራሉ:: ምንም እንኳ የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች ከእነሱ ጋር እንደሚታከሙ ቢናገሩም:: ሙያችን በጭፍኑ ትኩረት ከሚነፈገው፣ የምንሰጠውን ህክምና ባለሙያ ያረጋግጥ:: አብዛኛውን ጊዜ የምናክመው ዘመናዊ ህክምና መፈወስ ያልቻለውን በሽታ /ኪንታሮት፣ ነቀርሳ፣ ችፌ/ ነው፣ ይላሉ:: ያነጋገርኳቸው ሰባቱም የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች በሙሉ፣ ሃኪም እርገጤ ከበደ (ካሴት ቁጥር 2፣ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም) ከጤና ጥበቃ ጋር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መቀራረብ ተጀምሯል:: ቀደም ሲል ለባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ይሰጥ የነበረው ግምትና መጥፎ ስም የሚለወጥበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም:: ነገር ግን የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች አካልንና መንፈስን የሚያክሙ መሆናቸው መታወቅ አለበት ብለዋል:: ሃኪም ተክሌ ሃብተገብርኤል በበኩላቸው መንፈሳዊ ህክምና ከፍተኛ ድርሻ ቢኖረውም በዘመናዊ ህክም ግን እንደማይደገፍ ተናግረዋል:: /ካሴት ቁጥር 1፣ ሚያዝያ 9/2000 ዓ.ም/

የዘመናዊ ህክምና ባለሙያ የሆኑት ከጤና ጥበቃ ወጣት መሃመድ ዘይኑ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎችን በተመለከተ አስተያየቱን ሰጥቶኛል::

የባህል መድሃኒት አዋቂዎች የተመዘገቡበትም ሁኔታ ስለሌለ እነሱን መመዝገብ፣ ወደፊትም በዚህ በባህላዊ ህክምና ማሰልጠን እንደአሁኑ በቤተሰብ ተወርሶ የሚመጣ ብቻ ሳይሆን በባህላዊ ሃኪምነት፣ በዘመናዊ ካሪኩለም ውስጥ ተቀርጾ ገብቶ፣ በዚያ የሚሰለጥኑ ባለሙያዎች እንዲኖሩ ነው የምንፈልገው:: ህብረተሰቡን በትክክል እያገለገሉ ነው:: ያንን ከፍ አድርገን ከዘመናዊ ህክምና ጎን ህብረተሰባችን በደንብ እንዲጠቀምበት ነው የምንፈልገው:: /ካሴት ቁጥር 5፣ ሚያዝያ 22/2000 ዓ.ም/

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና እንደሚባለው የተገፋ ሳይሆን መልክ ይዞ እንዲቀጥል የሚፈለግ መሆኑን ከጤና ጥበቃው መግለጫ እንረዳለን:: ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ዕዝራ ሙሉነህ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና እንዲጠናከር የሚፈለግ መሆኑን ገልፀዋል::

> የባህል ህክምና በመንግስት የጤና ፖሊሲ፣ የመድሃኒት ፖሊሲ መበረታታት እንዳለበት በትክክል ቦታ አግኝቶ የሰፈረ ነገር ነው:: በ1970ዎቹ ውስጥ የመጀመሪያ የጤና አጠባበቅ ብሎ እንቅስቃሴ በጀመረበት ወቅት እነዚህን የባህል ሃኪሞች የማበረታታት ስትራቴጂ ነበር ሲጠቀም የነበረው:: የባህል ሃኪም ማለት ቅጠል የሚሰጡ ብቻ አይደሉም:: ሰፊ ትርጉም አለው በእኛ አገር አተረጓጎም:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መንግሥት ጊዜ ሰጥቷቸው ነው የሚገኘው:: የብዝሃ ህይወት ኢንስቲትዩት መድኒሃትነት ያላቸውን አትክልቶች ጠብቆ ማቆየት ስለሚያስፈልግ ራሱ እነሱን ለማበረታታት ሲል ቅጥር ግቢው ውስጥ ቢሮ ሰጥቶ ለተወሰኑት ደመወዝ እየከፈለ እነሱን ለማቅረብ ብዙ ሞክሯል:: /ካሴት ቁጥር 7፣ ሚያዝያ 28/2000 ዓ.ም/

በዘመናዊና በባህላዊ የህክምና ባለሙያዎች መካከል የሚታየው ክፍተት የተከሰተው ከሚሰጡት አገልግሎት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሳይሆን ተቀራርቦ ካለመወያየት የመጣ መሆኑን ከተሰጡት መረጃዎች መረዳት ይቻላል::

## 4. የባህላዊ ህክምና ሃኪሞችና መድሃኒት

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች የሚሰጡትን መድሃኒት የሚያዘጋጁት እራሳቸው ናቸው:: የመድሃኒት ምንጮቹ ደግሞ በየሃኪሞቹ የእውቀት ደረጃ የሚወሰኑ ናቸው:: ሁሉም የህክምና ጥበቡን ከአገር በቀሉ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና የቀሰሙና በአገር ውስጥ ከሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶች በባህላዊ መንገድ መድሃኒትን የሚቀምሙ ናቸው::

### 4.1 የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞችና የእውቀታቸው መነሻ

የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች በአገር ውስጥ ሲሰራበት ከነበረው ባህላዊ የህክምና አሰጣጥ የተገኙ ናቸው:: መነሻቸው ህብረተሰቡ ራሱ ፈጥሮት፣ አሳድጎትና እየተጠቀመበት ያለው አገር በቀሉ የህክምና ዘርፍ ነው:: ለዚህ የህክምና ዘርፍ ምንጭ የእምነት ተቋማት እንደሆኑ ሃኪም ፍቅረ ሰብ መኮንን «የህክምና ጥበቡ እግዚአብሔር ለሰለሞን ከሰጠው የተገኘ ነው» /ካሴት ቁጥር 8፣ ግንቦት 3/2000 ዓ.ም/ ያሉትን ለአብነት መጥቀሱ መረጃ ይሆናል:: በእስልምና እምነትም ተመሳሳይ አመለካከት እንዳለ ያነጋገርኳቸው ሙስሊም ሃኪሞች በአረብኛ የተፃፉ መጻሕፍትን በማቅረብ አሳይተውኛል::

አብደላ መሐመድ ከአረብኛ ወደ አማርኛ የመለሱት «ተአምራዊ ፈውስ» በሚል ርዕስ የተዘጋጀው «ኢስላማዊ ህክምና» መጽሐፍ ሙሉ ዝርዝሩ በባህላዊ መድሃኒት ህክምና ላይ የተመሰረተ ነው:: ይህም የባህላዊ መድሃኒት ህክምናን ከእምነት ጋር አያይዞ የመቀበሉ ሁኔታ መኖሩን ያሳያል::


> ሰዎች የትም ይኑሩ የት በሽታ ሊያጋጥማቸው ይችላል፣ ይህ ሲሆን ደግሞ፣ በደስታና በአማን መኖር አዳጋች ይሆናል:: አዛኙና ርህሩሁ ፈጣሪያችን የሰው ልጆች ለሚገጥማቸው የጤና ችግር በዙሪያቸው ከሚገኙ ዕጽዋት መፍትሔ ያፈላልጉ ዘንድ ንቃቱንና ዕውቀቱን አጎናፀፋቸው:: በዙሪያችን የምናያቸው ዕፅዋት፣ አዝርዕቶችና ፍሬዎች ለማንኛውም በሽታ አፋጣኝ ፈውስ የሚሰጡ አያሌ ምስጢሮች ይዘዋል:: የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ መሐመድ፣ «ጥቁር አዝሙድ ከሞት በስተቀር የሁሉም በሽታ መድሃኒት ነው» ሲሉ ገልፀዋል:: ከአያሌ ሰዎች ክትትል፣ ምርምርና ተሞክሮም እንደተረጋገጠው ቀይ ሽንኩርትና ነጭ ሽንኩርት እንደማርና ጥቁር አዝሙድ ሁሉ በውስጣቸው ተአምራዊ ፈውስ እንደሚያስገኙ ይታመናል /1996:5-6/::

ሰባቱም የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ትምህርታቸውን የጀመሩት ከየእምነት ተቋማቸው ነው:: የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ የሆኑት ሃኪሞች የህክምና ጥበቡን ያገኙት በገዳም ከሚኖሩ መነኮሳትና በብራና ከተፃፉ የመድሃኒት መፃሕፍት መሆኑን ሲናገሩ፣ የሙስሊም እምነት ተከታይ የሆኑት ደግሞ በቁርዓን ት/ቤት አልፈው በአረብኛ ከተፃፉ የመድሃኒት መጻሕፍት የባህላዊ መድሃኒት ህክምና እውቀቱን እንደገበዩ «ቅዱሳት መጻሕፍትን እያዩ ያክማሉ የሚለው ጥሩ ነው ብዬ እወስደዋለሁ:: የእኔ ህክምና አይነቱ ከዚህም ሊሆን ይችላል ላይሆንም ይችላል» በማለት ሃኪም አቡበከር አህመድ /ካሴት ቁጥር 6፣ ሚያዝያ 23/2000 ዓ.ም/ የገለፁልኝ ማስረጃ ይሆናል::

የእምነት ተቋማቱ ለትምህርታቸውም ሆነ ለህክምና ጥበቡ መነሻ እንደሆኑ ከቤተሰብ ወይም ከህክምና ባለሙያ ጋር በመቀራረብ የህክምና ጥበቡን እንደወረሱ የገለፁም አሉ::

> ከገዳም /ሳይኮ ገዳ/ መጀመሪያው ያስተማሩኝ መነኩሴ የመድሃኒት መጽሐፍ ነበራቸው፣ መጽሐፍም ሰጥተውኛል:: መነሻ የማደርገው ያው ነው:: ዛሬም አለኝ ተንከባክቤ ተጠንቅቄ ይዤዋለሁ:: ተስፋ የቆረጠው ካዳንኩት እደሰታለሁ ለነፍስም ይጠቅማል:: መድሃኒቶች ከስንት ጊዜ በኋላ አገልግሎት እንደማይሰጡ የሚገልፁ መጻሕፍት አሉ:: ይህንም ማወቅ ይገባል:: የመድሃኒት የጊዜ ገደብ አለው:: /ሃኪም ፍቅረሰብ መኮንን፣ ካሴት ቁጥር 8 ግንቦት 3/2000 ዓ.ም/

ሰባቱ የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች እውቀቱን መጀመሪያ ያገኙትና ያዳበሩት በአገራቸው ነው:: ሃኪም እርገጤ ከበደ በግብፅ በህንድና በቻይና፣ ሃኪም ሃጂ አቡበከር አህመድ ደግሞ በሱዳን፣ በሳውዲ አረቢያ በፓኪስታንና በኬንያ ተጨማሪ እውቀት መቅሰማቸውን ተናግረዋል:: ሃኪም ሃጂ አቡበከር አህመድ፣ ሃኪም ሃጂ ሳኒ አሊና ሃኪም ሃጂ አሊ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑት የባህዊ መድሃኒት ሃኪሞች ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ያልሆኑትን ጨምሮ «ሃጂ» የሚል የሃይማኖት ማዕረግ አላቸው:: ዘጠኝ መቶ ሃያ ዓመት (ሃጂ ኑር፣ ካሴት ቁጥር 4፣ሚያዝያ 12/2000 ዓ.ም) አላቸው የሚባሉትና የሚጠቀሙባቸው በአረብኛ የተፃፉ መጻሕፍት ተገኙ የተባሉት ከመካከለኛው ምስራቅ ነው:: በተመሳሳይ ሁኔታ ሃኪም ማሞ ኃይሌ፣ በኢብራይስጥ «ብሊት» /መድሃኒት ማለት ነው፣ እንደነገሩኝ/ የሚል ርዕስ ያለው መጽሐፍ አባ ወልደጻዲቅ የተባሉ መነኩሴ ከእየሩሳሌም አምጥተው እንደሰጧቸውና ዛሬም በብራና ከተጻፉ የመድሃኒት መጻሕፍት ጋር እንደሚጠቀሙበት ገልፀውልኛል::



920 ዓመት ዕድሜ አለው የተባለ በአረብኛ የተፃፈ የመድሃኒት መጽሐፍ

አባ ወልደፃዲቅ «ብሊት» የተባለውን የመድሃኒት መቀመሚያ መመሪያ መጽሐፍ ከእስራኤል ከማምጣታቸወ በተጨማሪ ሃኪም ማሞን መጀመሪያ የህክምና ጥበብ ያስተማሩ ናቸው::

የክርስትናም ሆነ የእስልምና እምነት መነሻ የሆነው መካከለኛው ምስራቅ ከእምነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የባህልዊ መድሃኒት ጥበብ ምንጭም መካከለኛው ምስራቅ እንደሆነ የተጠቀሰው መረጃ፣ ፍንጭ የሚሰጥ ይመስላል:: ከዚህ በላይ ለማለት ግን የመድሃኒት መጻህፍቱ የተፃፉበት ቋንቋ አውቆ ማንበብ፣ ሌሎች መረጃዎችንም ማገላበጥ ይገባል:: በአለበት ሁኔታ ግን ሃኪሞቹ የተነሱበትን እውቀት ከማሳየቱም በላይ የህክምና ጥበቡን ከሃይማኖት ጋር ለማያያዝ የሚደረገውን ጥረትም ያመለክታል::

የባህላዊ ሃኪሞች መነሻ የሚያሳየው ሌላው ገጽታ፣ የቀደሙት የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች ይጠቀሙበት የነበረውን ጥበብ ሲደግሙት መታየታቸው ነው:: የተለየ የመድሃኒት አሰባሰብ፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ አይታይም:: የነበረውን መስመር በመከተል ሃኪሞቹም ሆኑ ታካሚዎቹ በትላንቱ የህክምና ጥበብ መንገድ ይጓዛሉ:: በሙያው የተሰማሩት ሃኪም ፍቅረሰብ መኮንን ይህንኑ ያረጋግጣሉ:: «አሁን የምንገለገልባቸውን የመድሃኒት እውቀቶች ያገኘነው ከቆየ ነው:: ይህ መድሃኒት ሲወርድ  ሲዋረድ የመጣ፣ ጥቅም ላይ ይውሉ የነበሩ ናቸው:: መድሃኒቶቹ የቆዩ ናቸው፣ እኛ አዲስ የፈጠርነው አይደለም:: ህዝብ ሲገለገልበት የኖረና የተፈተነ ነው::» /ካሴት ቁጥር 8፣ ግንቦት 3/2000 ዓ.ም/

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ባህልና እምነት ተቀላቅለው ዛሬም ሲያለግሉ የምናይበት የተግባር ቦታ «ባህላዊ የህክምና አገልግሎት» መሆኑን ነው::

«ባህላዊ የህክምና ዘዴ የሰው ልጅ መመገብ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነበር» ካሴት ቁጥር 1፣ ሚያዝያ 9/2000 ዓ.ም/ እንዳሉት ሃኪም ተክሌ ሃብተገብርኤል ይህ ዘርፍ ረጅም ዘመን አገልግሎት ሲሰጥ የኖረው የመድሃኒት መቀመሚያ መጻሕፍት በሚያዙት መሰረት በተመሳሳይ መንገድ ነው ማለት ይቻላል:: ከዚህ ላይ መነሳት ያለበት ሌላው፣ ምንም ይሁን ምን በነበረና ተቀባይነት ባገኘ ሁኔታ መንዝዝ የለውጥ ጥያቄ የማስነሳት አቅሙ ደካማ መሆኑ ነው::

ዛሬ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች፣ የባህላዊ ህክምና ልማድ ወደ ባህል የቀየረላቸውን ተረክበው፣ በተለመደው ባህል ውስጥ በመኖር ለባህሉ እያስረከቡና ህብረተሰቡ በሚያምንበት መሰረት እያከሙ ይገኛሉ::

### 4.1.1 የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ንፅፅር

በባህላዊ መድሃኒት ህክምና የተሰማሩ ባለሙያዎች ስለራሳቸው፣ የሚሰጡት ብያኔ ዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ከሚሰጧቸው ብያኔ በመጠኑ የሚለይበት ሁኔታ አለ :: በእርግጥ ወጌሻነት፣ መድሃኒት ቀማሚነት አዋላጅነት የባህላዊ ህክምና ዘርፎች እንደሆኑና በእነዚህ የህክምና መስኮች የተሰማሩ ባሙያዎች ለመኖራቸው የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎችም እውቅና ይሰጣሉ :: ልዩነታቸው በመንፈሳዊ ዘርፍ የህክምና ባለሙያነት ላይ ነው ::

የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች አካልና መንፈስን የመፈወስ ነባር ሙያ አለን፣ ከዘመናዊ ህክምና ባለሙያ የሚለየን ሁለቱን አጣምረን መያዛችን ነው ሲሉ፤ ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ከጤና ጥበቃ መሃመድ ዘይኑ፣ ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ እዝራ ሙሉነህ ደግሞ መንፈሳዊ ህክምና ስለማይለካ በዚህ ዘርፍ የተሰማራ ባለሙያ እንደ ባለሙያ ተቀባይነት የለውም ይላሉ :: ሃኪም እርገጤ ከበደ ስለባህላዊ መድሃኒት ባለሙያ ችሎታ ሃሳብ ሰጥተዋል ::

> የባህላዊ ህክምናና የዘመናዊ ዶክተሮች የምንለያየው እዚህ ላይ ነው:: የባህላዊ ሃኪም ስንል አካልንና መንፈስንም ጭምር ነው የምናከመው፣ ዘመናዊ ግን አካልን ብቻ ነው የሚያክመው :: ባይገርምህ ከዛሬ 250 ዓመት በፊት በዘመናዊ የህክም ት/ቤት ውስጥ ካሪኩለም ተቀርጾለት መንፈሳዊ ህክምና / Spiritual medication/ አብሮ ይሰጥ ነበር፣ በአውሮፓ :: /ካሴት ቁጥር 2፣ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም/

ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያ፣ ስለ ባህላዊ መድሃኒት ሃኪም የተሰጠኝ የሙያ ትርጉም፣ ስለመንፈሳዊ ህክምና ጉዳይ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት አጉልቶ የሚያሳይ ነው ። ተቀባይነት ባለው የሙያ ዘርፍ የተሰማራው የባህላዊ ህክምና ባለሙያ ከጤና ጥበቃ መሃመድ ዘይኑ በሚከተለው ሁኔታ ገልጸውታል ።

> የባህል መድሃኒት አዋቂ ማለት እውቀትን ልምድንና ክህሎትን በማስተባበር ከዕፅዋት ከእንስሳት ከማዕድናትና ከእነሱ ተዋፅኦ የሆኑትን በመጠቀም አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ ነው። አሁን ባለው አካሄድ በመንፈሳዊ ተጠቅመው እናድናለን የሚሉ አሉ። ያንን ግን ሜዝር ለማድረግና ኳሊቲውን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ነው ።መንፈስ ሲባል መጥፎ መንፈስም አለ ። /ካሴት ቁጥር 5፣ ሚያዝያ 22/2000 ዓ.ም/

ከላይ ለማነፃፀር የቀረበው የተራራቀ ግንዛቤ ባለበት ሁኔት ጤና ጥበቃ የባህላዊ መድሃኒት ህክምናን በተመለከተ ረቂቅ ፖሊሲ አውጥቶ የሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲያፀድቅለትም ልኳል። በረቂቅ ፖሊሲው ላይም መንፈሳዊ ህክምና እንዳልተካተተ አረጋግጫለሁ ።

### 4.1.2 የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች በአዲስ አበባ በብዛት የተገኙበት ምክንያት

የባህል መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች በአዲስ አበባ ከተማ ከ140-300 መገኘት፣ ሁለት ምክንያቶችን የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ጠቅሷል ። ቅድሚያውን የሚይዘው ገቢን የማሣደግ ፍላጉት ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ህብረተሰቡ ስለ ባህላዊ መድሐኒት ህክምና ያለው የቆየ ልምድና እምነት መሆኑን የጤና ቢሮ ተወካይ ዕዝራ ሙሉነህ ገልፀዋል ።

> የባህል ሃኪሞች የት ነው መሆን ያለባቸው ? ዘመናዊ ህክምና ከሌለባቸው ቦታዎች ነው። እዚህ ጋ ግን አሁን ያለው ነገር ትርፍ ማግኘት ነው። የታመመ ሰው የትም ይሄዳል። ዘመናዊ መድሃኒቶች ጋ መፍትሄ ካላገኘ የባህል መድሃኒቶች ነው የሚሄደው? ፀበልም ይሁን ጥንቆላ ይሁን ሰዎች ምርጫ አለ እስካሉ ድረስ የትም ይሄዳሉ ይህንን ለገንዘብ ማግኛነት መጠቀም ወንጀል ነው ። /ካሴት ቁጥር 7፣ ሚያዝያ 28/2000 ዓ.ም/

ሁለተኛው ምክንት ሆኖ የቀረበው በአለንበት ዘመን የበሽታዎች መብዛት ህብረተሰቡ ስለ ባህላዊ መድሃኒት ህክምና ያለው የቆዬ ግንዛቤ ነው ። ለዚህም ከአስተዳደጋችን ጀምሮ የባህል መድሃኒት ህክምና እንድንቀበለው መደረጉንና በአካባቢያችን የነበሩ የባህላዊ መድሃኒት

ባለሙያዎች ዝና ተፅዕኖም በቀላሉ የሚለቅ እንዳልሆነ ባለሙያው በተጨማሪ የሰጡት ምክንያት ነው ::

የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች በተመለከተ ከጤና ጥበቃ ያገኘሁት መረጃም የአዲስ አበባ ጤና ቢሮን አቋም የሚደግፍ ነው :: በኢትዮጵያ የባህላዊ መድሃኒት ቡድን ኤክስፐርት የመሃመድ ዘይኑ ዝርዝር ማብራሪያ ደግሞ እንደሚከተለው ነው ::

> በገጠር ይኖራል ተብሎ የሚታሰበው ህዝብ 75% ነው:: ያለው መረጃ እንደሚያሳየው አብዛኛው እንደሚጠቀመው ነው፣ የባህላዊ ህክምናን :: ያ ለምንድነው ? አንደኛ ከተደራሽነት በእያንዳንዱ መንደር ነው ያሉት :: ሁለተኛ ዋጋቸው ውድ አይደለም :: ዘመናዊ ህክምና ጋ ሂደህ ረዣዥም ሰልፎችን ጠብቀህ ወይ ደግሞ ራጅ ማሽን ታዞልህ በጣም መጉላላቱን ሽሽት ነው :: ሌላው ትልቁ ግን ለዚህ ድርሻ አለው ብለን የምንለው እምነት ነው :: ያድነኛል ብሎ የማመን ነገር :: ሁላችንም ከታች እናቶቻችን ያሳደጉን አለ፤ በባህላዊ ህክምናው ላይና በሰዎቹ ላይ ያለን እምነት ትልቅ ነው :: ... የተከበሩ ትልልቅ ሰዎች ናቸው ይህንን ህክምና የሚሰጡት ለእነሱ ያላቸው ክብር ጭምር ነው ወደዚያ የሚወስዳቸው :: /ካሴት ቁጥር 5፣ ሚያዝያ 22/2000 ዓ.ም/

ከሁለቱም ዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች የምናገኘው ማብራሪያ፣ የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ወደ ከተማ የሚሰበሰቡበትን ምክንያት የሚያስገነዝብ መረጃ ነው :: እንደተባለው ገቢያቸውን አሳድገውበታል :: ምልከታ ያደረኩባቸው የባህላዊ መድሃኒት ህክምና መስጫ ቦታዎች ሁሉ ቢያንስ የካርድ አስር ብር ያስከፍላሉ :: አንድ የኪንታሮት በሽተኛ 500 ብር ተጠይቆ፣ በድህነቱ ምክንያት ለምኖ 250 ብር መክፈሉን ነግሮኛል :: በእርግጥ በነፃ የሚያክሙም አይጠፉም:: ታካሚዎች እንደመሠከሩላቸው ሃኪም ማሞ ኃይሌ አቅም የሌላቸውን በነፃ በማከም የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛሉ::

የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎቹ በከተማ የሚሰባሰቡበት ምክንያት ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ለመሆኑ ሃኪም ፍቅረሰብ መኮንን የገለፁት ሌላ ማረጋገጫ ይሆናል::

> እኔ በባህላዊ መድሃኒት ህክምና ሙያ እተዳደራለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር:: ሙያውን ያስተማሩኝ የሰይኮ ገዳም መነኩሴ «ይህን መድሃኒት ወስደህ ከአዲስ አበባ ወዲያ አገር አለ:: ድሬደዋ ወስደህ ልትጠቀምበት ትችላለህ:: ብዙ ብር ልታገኝበት ትችላለህ» አሉኝ:: በማዳበሪያ መያዣ ሰፍተን እንደ ሻንጣ በዚያ የተቀመመ መድሃኒት ይዤ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ:: /ካሴት ቁጥር 8፣ ግንቦት 3/2000 ዓ.ም/

እኒህ ሃኪም በቄስ ት/ቤት ትምህርታቸውን ገፍተው የመሪጌታነት ማዕረግ አግኝተዋል:: በነባሩ የቤተክህነት የትምህርት ዘርፍ በቅኔ፣ በአቋቋምና በድጓ ብዙ እንደተማሩ ገልፀውልኛል:: ነገር ግን በተማሩት ሙያ አንድም ቦታ አልሠሩም:: ከአዲስ አበባ ከ700 ኪሎ ሜትር በላይ ከሚርቅ ጐንደር፣ ሊቦ አውራጃ፣ እብናት ወረዳ፣ ሰይኮ ገዳም ነው የመጡት:: በምሣሌነት እሳቸውን ጠቀስኩ እንጂ ያነጋገርኳቸውም ሆኑ ምልከታ ያደረኩባቸው ሁሉ የመጡት ከክፍለ ሃገር ነው:: ከጅማ አቡበከር አህመድ፣ ከወሎ ሃጂ ኑሩ አደም፣ ከሰሜን ሸዋ ተክሌ ሃብተ ገብርኤል እና ማሞ ሐይሌ፣ ከጐጃም እርገጤ ከበደና ደጀኔ ብሩ ይጠቀሳሉ::

በዚህ ማሣያ መሠረት የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎች እንደገለፁት የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች ወደ ከተማ የመሰባሰባቸው ሚስጢር ከኑሮ ማሻሻል ጋር የተያያዘ ነው:: የተከራዩትም ሆነ የሚኖሩበት ቪላ ቤት የሚያረጋግጠውም ይህኑ ነው::

### 4.2. የባህላዊ ህክምና መድሃኒቶች መገኛና አሰባሰብ

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች ለህክምና አገልግሎት የሚያውሏቸውን መድሃኒቶች ከተለያዩ የገጠር አካባቢዎች እንደሚያስመጡ በቃለ መጠይቁ ወቅት ተናግረዋል:: «መድሃኒቶችን ከጐጃም፣ ከጐንደር፣ ከወሎ፣ ከአርባ ምንጭ፣ ከባሌ፣ከሃረር፣ ከአፋር፣ ከወለጋ፣ ከአሶሳ ከዚያ ድረስ ነው፣ የምናስመጣው:: ደንበኞች አሉ፣ የድርጅቱ ሃኪሞችም ይሄዳሉ::» ይህን ምስክርነት የሰጡት ሃኪም እርገጤ ከበደ ናቸው::/ ካሴት ቁጥር 2፣ ሚያዝያ 10/2000ዓ.ም/

በግቢያቸው የመድሃኒት ዕፅዋትን ማልማት የጀመሩት ሃኪም ማሞ ኃይሌም ከገጠር መድሃኒት አስመጣለሁ ብለዋል:: ለቃለ መጠይቅ በሄድኩበት ወቅት ለጊዜው በቂ መድሃኒት አለኝ በሚል ምክንያት በግቢያቸው የሚገኙትን ዕፅዋት መንጥረዋቸው ነበር::

«ይሄው የመነጠርኩት ከደጄ አለ:: ከየትም አምጡት ስል ያመጣሉ፣ ከአፍሪካ አገር ሁሉ:: ሰው ይላካል:: እኔም እስጣቸዋለሁ:: እነሱም ያመጣሉ:: ከጐጃም፣ ከመራቤቴ፣ ከጅማ፣ ከአለም ከተማ፣ ከሰም አገሬ ነው የማዘው ሁሉ ማንም ያመጣል:: ከአንኮበር፣ ከጨርጨር፣ ዋናው አርባጉጉ ነው::» /ካቤት ቁጥር 3፣ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም./

የህክምና ጥበቡን የት እንደተማሩት ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ሃኪም ማሞ በሰጡት መልስ፣ ከላይ በጠቀሷቸው ቦታዎች በመዘዋወር ቤተክርስቲያን ከሚያገለግሉ መነኮሳትና በተለይ

አርባ ጉጉ ከሼሆች መማራቸውን ገልፀውልኛል:: በተመሣሣይ ሁኔታ የመድሃኒት መገኛ ቦታዎችን የተናገሩት ሃኪም ተክሌ ኃብተገብርኤል እንሚከተለው ጠቅሰዋል::

> እኔ የምጠቀመው በገበሬ ማህበር ነው:: እዚህ ማግኘት አልችልም:: አገር ቤት እሄዳለሁ:: እዚያ እበረሃ ያሉት ሰዎች ጋር እሄዳለሁ:: እነዚያን የገበሬ ማህበሮች እንዲህ እንዲህ ያሉትን ዕፅዋት ታውቃላችሁ ወይ? አዎ፣ የት ነው የሚበቅሉት? እዚህ፣ እዚህ ቦታ:: እነዚያን አሣይቼ ይሄን እንዲህ አርጋችሁ አምጡልኝ ገንዘብ እሰጣችኋለሁ ብዬ እፅዋቶቹም እንዳይጎዱ ሰዎቹም ሲያመጡ ሌላ መሆኑን ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጨ ናሙና ነው ይዘው የሚመጡት እንዳይበሰብሱ ይሄን፣ ይሄን አድርጋችሁ ብዬ ገበሬዎቹን እያሰለጠንኩ፣ እያስተማርኩ፣ ከጐጃም፣ ከጐንደር፣ ከእንሳሮ፣ ከጅሩ፣ ከሜታ አቦ፣ ከአንኮበር ከየቦታው በገበሬ ማህበር ነው የማመጣው፣ እነሱም ያመጡልኛል::/ ካሴት ቁጥር 1፣ ሚያዝያ 9/2000 ዓ.ም./

ያነጋገርኳቸው ሰባት ሃኪሞች ለመድሃኒት የሚውሉትን እፅዋት፣ እንስሳትና ማዕድናት ከየክፍላተ አገሮቹ ገጠር እንደሚያስመጡ የተናገሩት የቦታ ምንጫቸውን ሳይቀር በመጥቀስ ነው:: ከሃኪም ማሞ ቀጥሎ የመድሃኒት ዕፅዋት ዘርን ሰብስቦ በተወሰነ ቦታ የማልማት እቅድና ጅምር ያላቸው ሃኪም ሃጂ ኑሩ አደም ናቸው:: እንደተናገሩት ለመድሃኒት የሚውሉ የዕፅዋትን ዘር አዘጋጅተው ቦታ ከመንግስት ለመቀበል በዝግጅት ላይ ናቸው::

በአጠቃላይ ለህክምና የሚውሉት መድሃኒቶች የሚሰበሰቡት የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች ከመጡበት ከተለያዩ ክፍላተ ሃገር ገጠር ነው:: ይህም የሃኪሞቹንና የመድሃኒቶቹን መሠረታዊ ቅርርብና ከጥንት ተያይዞ መምጣት ያመለክታል::

የባህላዊ ህክምና መድሃኒት አሰባሰብ፣ ባህላዊ ገጽታውን ይበልጥ የሚያሳይ ሂደት አለው:: መድሃኒቶችን ለመሰብሰብና ለማዘጋጀት የተለየ ሥነ ሥርዓት ይደረጋል:: ምክንያቱ ደግሞ ፍቱን እንዲሆኑ ተፈልጐ ነው የሚል ዝርዝርና ጥቅል መረጃ ከባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች አግኝቻለሁ::

መድሃኒቶች የተለየ የአቆራረጥና የአቆፋፈር ሂደት አላቸው:: ይህ ደግሞ በመፈወስ አቅማቸው ላይ ኃይል ይጨምርላቸዋል የሚል እምነት ያላቸውና በዚሁ የቆየ የአሰባሰብና የዝግጅት ሂደት ከሚጠቀሙት አንዱ ሃኪም ተክሌ ኃብተገብርኤል የሚከተለውን ነግረውኛል::

ሸእርግጥ የሚቆርጠው ሰው እህል ሳይቀምስ ቢሆን ጥሩ ነው። ጠዋት ከሴትም ንጹህ ሆኖ፣ ምግብም ሳይበላ ቢሆን ቆንጆ ነው አዋቂም ከሆነ። ነገር ግን በገበሬ ማኅበር አምጣልኝ የምትለው ከሆነ መቸም የግድ ነውና ያንን ትእዛዝ ልትሰጠው አትችልም። እሱ ያነን አድርጐ ካመጣ አንተ ደግሞ ትንሽ ያገኘሃትን ከዚያ ጋር ቀላቅለህ መድሃኒት አድርግልኝ ብለህ መፀለይ ነው። መድሃኒቱ ላይ እምነት የሚባል ነገር አለ። እኔ ዕፅዋቶችን ሳመጣ ራሴ ምናልባት የማነግሣቸው ሊኖሩ ይችላሉ፤ በራሴ።

አብዛኛውን እፁን አንተ ማንገሥ አለብህ በፀሎት፣ በድሮው ከሆነ ግን ደምም አፍሰህ የምታደርገው ነገር አለ። አንተንም እንዳይጣላህ፣ የሚጣላህ ዕፅዋት አለ። ያንን እንደገሰገስክ ሂደህ ብትቆርጠው ወይም አይንህን ያጠፋሃል ወይም ያሳብድሃል ወይ አንድ ነገር ያደርግሃል። ያ ነገር መድሃኒት ነውና ጠባቂ መልዓክ አለው። መድሃኒቶች ናቸው፣ ዕፅዋቶች ናቸው እንደሰው ይታዘዛሉ። / ካሴት ቁ.1፣ ሚያዝያ 9/2000 ዓ.ም/



*የመድሃኒት መቀመሚያ ፍሬ*

ሃጂ ኑሩ አደም በበኩላቸው ለመድሃኒትነት የሚያገለግሉ እፅዋት በማንምና ያለምንም መሰናዶ ቢሰበሰቡ የመፈወስ ችግር የለባቸውም ብለዋል። ነገር ግን ዕፅዋት የመድሃኒትነት ኃይላቸው የሚጨምርበትና የሚቀንስበት፣ የሚገኙበትና የሚጠፉበት ወቅት እንዳለም ጠቅሰዋል።

በሃምሌ የምንሰበሰባቸወ እፅዋት አሉ። በመስከረም የምንሰበስባቸው ዕፅዋቶች አሉ። በመጋቢትና በየካቲት የምንሰበስባቸው እፅዋቶች አሉ። ሦስት ቦታዎች አሉ።

> እነዚህም በቀዝቃዛ ቦታ በመካከለኛ ቦታ፣ ሐምሌ ውስጥ ቀዝቃዛ ሰዓት ነው፣ ቆየት ስትል በረድ ያለ፣ ቆየት ስትል በጣም የሞቀ ታገኛለህ:: እዚያ ውስጥ የምንቆፍራቸው መድሃኒቶች አሉ:: ሐምሌ ላይ ኃይለኛ የሆነው በበጋ ነው መቆፈር ያለበት:: በጋ ያተነዋል:: ኃይሉ በፀሐይ ሲተን ሰውነት እንዳይጐዳ ያደርገዋል:: ኃይሉ ደካማ የሆነውን እፅዋት ደግሞ ክረምት ነው ቀዝቃዛ ነው ታወጣዋለህ፣ ጥላ ላይ ታደርገዋለህ:: ከዚያ በኋላ ያን ትጠቀማለህ ማለት ነው:: ስለዚህ በተለያየ ሰዓት ነው የሚቆፈረው:: / ካሴት ቁጥር .4፣ ሚያዝያ 12/2000 ዓ.ም/

እነዚህ ሁለት የባህላዊ መድሃኒት ቀማሚዎች የመድሐኒት አሰባሰብና አዘገጃጀት ተሞክሯቸው የተለያየ ነው:: ነገር ግን ሁለቱም ሃኪሞች እውቀቱን ያገኙበት መንገድ የተለመደው ውርስ ነው:: በእርግጥ በእምነት ይለያያሉ:: ሆኖም የልምድ እንጂ የእምነት ጉዳይ አለመሆኑን ከሚከተሉት መረጃዎች እንረዳለን:: የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑት ሃጂ አቡበከር አህመድ እንደ ሃኪም ተክሌ የአሰባሰቡን ሂደት ዘርዝረው አይናገሩ እንጂ ስርዓቱ አስፈላጊ ነው ለመድሃኒት የሚውሉ ዕፅዋትን በፀሎት፣ ከመኻታ እንደተነሱ በባዶ ሆድ፣ መስዋዕት ተደርጐ፣ ... እንዲሁም ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ልጅ ቢቆርጣቸው ወይም ቢቆፍራቸው፣ መቁረጫና መቆፈሪያቸው የተለየ ቢሆን ፍቱን ይሆናሉ፤ ነገር ግን ሌሎች ስለአልደረሱበት በዚህ ወቅት መናገሩ አስፈላጊ አይደለም ሲሉ ተገቢነቱን አረጋግጠዋል:: /ካሴት ቁጥር 6፣ ሚያዝያ 23/2000 ዓ.ም./

ሃኪም እርገጤ ከበደ የመድሃኒት ዓይነቶች ይለያያሉ እንጂ የተለየ ዝግጅት ተደርጐላቸው የሚሰበሰቡ መድሃኒቶች መኖራቸውን ተናግረዋል::

> ያልባለቀ ልጅ የመቁረጥ ነገር አለ:: ያልባለቀ ልጅ ለሴት ያልደረሰ፣ ለወንድ ያልደረሰች ወይም የወር አበባ ያላየች:- ለምሣሌ ጫት፣ ለፀሎት ለዱአ፣ ዕፁ ቅዱሣን ይባላል:: ሄደው፣ ቤት ተለቅልቆ አርቲው፣ አደሱ ምናምን ተብሎ ያልባለቀ ልጅ ሂዶ ቆርጦ አምጥቶ ከሰው ጋር ሳይነጋገር እዚያ ቤት ውስጥ ይገባል:: እስላሞች የሆኑ ይጠሩና ወዳጃ የሚባል ነገር አለ፣ ይባላል:: የታመመ ሰው ካለ ቀጥ ብሎ ይነሣል:: /ካሴት ቁጥር.2፣ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም./

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ትምህርታቸውን ከገዳም ያገኙትና ዛሬም የመድሃኒት ምንጩ ገዳማት ናቸው የሚሉት ሃኪም ፍቅረስብ መኮንን፣ የተለየ ዝግጅት የሚያስፈልጋቸው ለደዌ ማስወገጃ የሚውሉት መድሃኒቶች ሳይሆኑ ለመስተፋቅር፣ ለትምህርት እና ለመሳሰለው የሚገለግሉ ናቸው:: በፀሎት የሚሰበሰቡ ከሆነ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ውጭ ላሉት ላያገለግሉ ይችሉ ነበር:: ነገር ግን ቁም ነገሩ ከዕፅዋቱ ስለሆነ በምንም ሁኔታ ቢሰበሰቡ

ይፈውሳሉ በማለት የሃጂ ኑሩ አደምን ሃሣብ ደግፈዋል:: /ካሴት ቁጥር 8፣ ግንቦት 3/2000 ዓ.ም./

ያነጋገርኳቸው ሁሉም የባህል ሃኪሞች የተስማሙባቸው የጋራ ነጥቦች አሏቸው:: እነሱም የተክሎች የእድገት ደረጃ፣ የሚገኙበት ወቅትና አካባቢ፣ እንዲሁም የመድሃኒትነት ኃይል መቀነስና መጨመር፣ በአሰባሰብ ወቅት ትኩረት የሚደረግባቸው መሠረታዊ ስልቶች የሚሉት ናቸው::

ሃኪም እርገጤ ከበደ መድሃኒቶች በተለያየ ወቅት የሚሰበሰቡበትን ምክንያት ምሣሌ በመስጠት እንዲሁም የዕፅዋት እድሜ አስፈላጊነት ጭምር ያስረዳሉ::

> በተለይ ከጳጉሜ ጀምሮ እስከ ህዳር 30 ቀን ድረስ ነፍስ የለንም:: እኛ እፅዋቶች የሚቆረጡበት maturity date አላቸው:: ያ እፅዋት ስለሆነ ብቻ አይደለም የሚያድነው:: የራሱ የሆነ maturity date አለው:: የሚቆረጥበት ጊዜ አለ:: ለምሣሌ ባህርዛፍ ለፍሉ /flu/ መድሃኒት ነው:: የትኛው ባህርዛፍ ነው? ለጋው ነው:: ከለጋው ካለፈ አይሆንም:: ደረጃውን ጠብቆ ነው:: /ካሴት ቁጥር 2፣ 10/2000 ዓ.ም./

ሃኪም ደጀኔ ብሩም፣ ከእፅዋት የሚዘጋጁ መድሃኒቶች በክረምት ወቅት ቢሰበሰቡ ውጤታማ አይሆኑም የሚል አመለካከት አላቸው:: «በክረምት ውስጥ ልሰብስብ ብትል ጭርቃ ናቸው፣ ያልበሰሉ ናቸው:: መድሃኒቶች ሊሆኑ የሚችሉት ደግሞ የበሰሉ፣ የጠነከሩ ናቸው:: በይበልጥ ከቆላማ ሃገር የሚገኙት በሳልና የጠነከሩ መሆን አለባቸው:: ቢቻል ከጥቅምት በኋላ በዚያን ሰዓት ነው መሰብሰብ ያለበት:: ያልበሰሉት ለመድሃኒትነት አቅም የላቸውም::»/ካሴት ቁጥር 9፣ ግንቦት 25/2000 ዓ.ም./
በመድሃኒት አሰባሰብ ወቅት የተለየ ሥርዓት ቢኖር ይጠቅማል:: ነገር ግን ዝርዝር ውስጥ ብንገባ ሌሎች የተሣሣተ ትርጉም ይሰጡታል:: የሚል ሃሣብ ያላቸው ሃጂ አቡበከር አህመድ ወቅትን ጠብቆ መድሃኒቶች ቢሰበሰቡ ፍቱን መድሃኒት እንደሚሆኑም ያምናሉ::

> በየትኛውም ጊዜ መድሃኒቶቹን ልናገኝ እንችላለን:: ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ አንድ ዛፍ ቅጠሉን በሚያወጣበት ጊዜ ወይም እዚያ ውስጥ አመች ውሃ በራሱ ውስጥ በሚይዝበት ጊዜ ነው መድሃኒትነቱ የሚኖረው:: የመድሃኒት ጥናታችን ይሄ ነገር ለዚህ መድሀኒት ነው ብለን ያወቅነው ሁኔታ ነው የሚወስነው:: አንድ ቅጠል በዚህ ደረጃ ላይ ካለ ለዚህ መድሃኒት ነው፣ ይህን እድሜ ካለፈ የጉንዮሽ ጉዳት ይኖረዋል:: በዚህ እድሜም ሣይደርስ ከሆነ እንዲሁ የጉንዮሽ ጉዳት ይኖረዋል:: / ካሴት ቁጥር 5፣ ሚያዝያ 23/2000 ዓ.ም./

በተለያዩ መንገድ ይግለፁት እንጂ ሁሉም የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ከእፅዋት የሚገኙ መድሃኒቶች ወቅትን ጠብቆ ካልተሰበሰቡ ላይገኙ ወይም በሽተኛውን ከመፈወስ ይልቅ ጉዳት ሊያደርሱበት እንደሚችሉ ይስማማሉ:: መድሃኒቶች እንደ እለት ምግብ ጊዜ ተጠብቆ ካልተሰበሰቡ ሊገኙ እንደማይችሉ ሃኪም ማሞ ኃይሌ የገለፁት አበባን ምሣሌ በመጥቀስ ነው:: « ሽኮኮ ጉመንና ግራዋ በታህሣሥ ጀምሮ ያብባል:: ግራዋ ካረገፈ የት ይገኛል፣ የግራዋ አበባ ተፈላጊ ነው፣ የግራዋ አበባ ማር ገቢርኑቱ ለስኳር ነው:: የግራዋ ማር በአዳስ አበባ ነው የማገኘው::» /ካሴት ቁጥር 3፣ ማ የዝየ 10/2000 ዓ.ም./

አዲስ አበባ ከተማ ህክምናውን የሚሰጡት የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ብዙም ያልተራራቀ የአሰባሰብ ስልት ተጠቅመው መድሃኒቶችን የሚቀምሙት ህክምናውን በሚሰጡበት ቦታ ነው:: ሃኪም ማሞ ኃይሌ በግቢያቸው የተለያዩ ዕፅዋት ያለሙ ቢሆንም ሁሉም የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች ከአዲስ አበባ ውጭ ከተለያዩ ቦታዎች መድሃኒቶችን እንደሚያስመጡ በሰጡት የቃለ መጠይቅ ምላሽ አረጋግጠዋል:: መድሃኒቶች የሚሰበሰቡበት መንገድ በቀረበው ማሣያ መሠረት ባህላዊ አሰባሰቡን በጠበቀ ሁኔታ ነው:: የቤት ቁሳቁስ በመያዝ ለብቻ ወይም እረዳት ይዞ አሉ ከተባሉበት አካባቢ የሚፈለገው የመድሃኒት ክፍል ይሰበስባል:: ከገለፃቸው እንደተረዳሁት መድሃኒቶችን በጥሬው በመሰበስቡ ወቅት ማንም ማገዝ የሚችል ቢሆንም ቅመማውና ለምን መድሃኒት እንደሚውል የመወሰኑ ሥልጣን ግን የሃኪሙ ብቻ ነው:



ሃኪም ተክሌ ኃ/ገብርኤል መድሃኒት ሲሰበስቡ

በአሰባሰቡና በአቀማመሙ ወቅት ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ ባለሙያዎቹ ትኩረት ሰጥተው ይናገራሉ:: የሃኪም እርገጤ ከበደ ማብራሪያ ደግሞ የሚከተለው ነው::

*ዕፅዋት ይመጣሉ:: ዕፅዋቱ ሲመጣ ቅርፊቱ ከሆነ ቅርፊቱ፣ ቅጠሉ ከሆነ ቅጠሉ ሥሩ ከሆነ ሥሩ ለየብቻው ነው፣ መምጣት ያለበት:: ያ ሃኪሙ ነው መሄድ ያለበት፤ በአምጡልኝ፣ በባካችሁ፣ በቢዝነስ አይሄድም:: ይህ የህክምና ሥራ:: ገዝተህ የምትሰራው ሥራ አይደለም:: ድግጣ ከፈለክ ሌሎች ነገሮች ተጨምረው ድግጣ፣ድግጣ ከሸተተህ፣ ነው ብለህ ሌላ ነገር ውስጥ ትገባለህ:: እና እፅዋቶችን ይሄን ቁረጡ፣ ይሄን ቁረጡ ብሎ እዚያው አስቆርጦ ከርሞ 20፣ 30 እና 40 ኩንታል በአይሱዙ ሞልቶ እያንዳንዱ ደርቆ ተጽፎበት ነው የሚመጣው:: /ካሴት ቁጥር 2፣10/2000 ዓ.ም./*

## 4.3 የባህላዊ መድኀኒት አዘገጃጀትና አሰጣጥ

### 4.3.1 አዘገጃጀት

መድሃኒቶች አሉ ከተባሉበት ቦታ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ በየሃኪሞቹ ቤት ይሰበሰባሉ:: ከአባቶችና ከመድሃኒት መጻሕፍት በተገኘ መረጃ መሠረት፣ የቅመማ ሂደቱ በሃኪሙ ቤት፣ በሃኪሙና በቤተሰብ ጭምር ይከናወናል:: አዘገጃጀቱም ከጥንት የመጣነው ስለሚባል የመድሃኒት መጽሐፉ የሚያዘውን መንገድ የተከተለ ነው::

የተሰበሰበው መድሃኒት በእጅ ይወቀጣል፣ ይቀጠቀጣል፣ ይነጠራል፣ ይደፈደፋል፣ ከዚያም እንደየሃኪሙ እውቀት ተቀምመው ወይም ሳይቀላቀሉ በባህላዊ መለኪያ ተለክተው በዱቄት፣ በፈሳሽ በእንክብል፣ በሚቀባ መልክ እየተዘጋጁም ይቀመጣሉ:: በቤት ውስጥ መድሃኒቶች፣ የሚዘጋጁበት ቁሳቁስ በአብዛኛው ባህላዊ ነው:: መቆፈሪያ እንካሴ፣ መጥረቢያ፣ ማጭድ፣ ሙቀጫ፣ ወፍጮ፣ ሰፌድ፣ ወንፊት፣ እንስራ፣ ደምበጃን ይገኙበታል:: ለአብነት ሃኪም ደጀኔ ብሩ የነገሩኝን አቅርቤዋለሁ::

*ሙቀጫ አስፈላጊ ነው መቆፈሪያ ማጭድ ሊሆን ይችላል:: ከማጭድም አይነት አለው:: የነሐስ ማጭድ የሚባል አለ:: የቀንድ ቢላዋ፣ የሚባል አለ:: ከመጥረቢያውም ደግሞ አይነት አለው:: ፋስ መጥረቢያ ባለ ሁለት መንታ መጥረቢያ የሚቆረጥ አለ:: ባለ አንድ ሹል መጥረቢያ የሚቆፈር አለ:: እንደየቃል ኪዳኑ ይለያያል:: /ካሴት ቁጥር 9 ግንቦት 25/ 2000 ዓ.ም./*

ሐኪም ደጀኔ ለምን የተለየ የመቁረጫና የአሰባሰብ ስርዓት ኖረ የሚል ጥያቄ እንስቼላቸው «ለእፅዋት የተሰጠ ቃልኪዳን ነው»በማለት መልሰውልኛል::

ከመድሃኒት አዋቂዎች፣ ከመጻሕፍትና ከልምድ በተገኘው እውቀት መሠረት ደንቡን ተከትሎ መድሃኒት በየባህላዊ ሃኪሙ ቤት ይቀመጣል:: ለአብነት የሃኪም ማሞ ኃይሌን ምስክርነት እንመልከት::

> መድሃኒቱ መዝገቡ እየታየ እንጂ የልቦለድ መድሃኒት አልቀምምም፣ መጣራት አለበት:: ለምሳሌ መቶ ኪሎ እህል አንድ አይነት አይደለም:: ያ መቶ ኪሎ 65 ወይም 70 አይነት ነው:: ለመቶ ኪሎ እህል አንድ ኪሎ ዕፅዋት ነው የሚገባው:: ያ ይፈተሻል፣ ይመረመራል:: ዶሮም ከሞተ፣ አይጡም ከሞተ፣ አይጥ አሁን አሉ:: ዘግቼ ነው እንጂ፣ በዚያ ይፈተሻል ያች ታለተለተች አይሆንም:: አይጧ ትንፋሿን ታለተለተች በኋላ መሞቷ ነው:: ግን አድናታለሁ ማርከሻ አለኝ:: /ካሴት ቁጥር 3፣ ሚያዝያ 10/ 2000 ዓ.ም./



ለመድሃኒት መቀመሚያ የተሰበሰቡ ዕፅዋት

በፈሳሽ መልክ የሚዘጋጀውን መድሃኒት የገለፁት ደግሞ በሚከተለው ሁኔታ ነው::
የኮሶ ዛፍ ፍሬው እርጥቡን የትልቅ ሰንጋ ሳንባ ነው የሚመስለው:: እሱን አምጥተን፣ አንኩረን ነው የምንደፈድፈው:: እንደፎርቴ ያለው ኃይለኛው መሬት ነው የምንቀብረው፣ በደንበኛን መሬት ቆፍረን የአየሩ ሙቀት ያነጥረዋል:: አይሻግትም ስኳር ከነካው ብላሽ ነው:: ማር ብቻ ከሆነች፣ ማር የነካው ነገረ

ኤክስፖየረድ የለውም፣ አይበሰብስም፣ መልኩን አይለውጥም ጣዕሙን አይለውጥም:: እዚያው ስንደፈድፈው ተነጥሮ ወጥቷል፣ ተጣለሰ:: ይኸው እንደ ውስከ ዞን፣ የአንድ ሰው እድሜ ሳይበላሽ ይቆየል:: / ካሴት ቁጥር 3፣ ማየዝየ 10 /2000 ዓ.ም./

በቢልቃጥ የተቀመጠውን አንስተው ቀመሱትና ሞቋል ብለው ወደ ቦታው መለሱት:: ለምን በሽታ መድሃኒት እንደሚውል ጠይቄአቸው ወደ ተደረደሩት መድሃኒቶች እያመለከቱ «ይሄ አሁን የነቀርሳ ነው፣ የኪንታሮት ነው፣ የአሜባ ነው፣ የኮሶም፣ የአስምም ነው:: የጡት፣ የአንገት እብጠት ይሄ ሁሉ ነው» ብለውኛል::

ሃኪም ማሞ ኃይሌ ከ15 ዓመታቸው ጀምሮ የባህላዊ ህክምና አገልግሎት በመስጠት የገነነ ስምና እጅግ ቁጥሩ የበዛ ታካሚ አላቸው (በምልከታየ ወቅት 150 ታካሚዎች ቆጥሬያለው) የመድሃኒት መቀመሚያ መመሪያ 11 መጻሕፍት አሳይተውኛል:: የተቀመሙ መድሃኒቶች ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ተጽፎባቸው ተደርድረዋል:



ለህክምና የተዘጋጁ መድሃኒቶች

ሃኪም ተክሌ ኃብተገብርኤል አብዛኛውን ጊዜ በህልሙ-ሌሊት ተገልጦልኝ መድሃኒት እቀምማለሁ በማለት ከ130 ዕፅዋት መድሃኒትን እንደሚቀምሙ የቃልና የጽሑፍ መረጃ ሰጥተውኛል:: የቅመማ ስልታቸውም ከብዙ ዕፅዋት ለአንድ በሽታ መፈወሻ መድሃኒት በማዘጋጀት ላይ የተመሠረተ ነው::

> ለኪንታሮት የምሰጠው መድሃኒት 10 ዓይነት ዕፅዋት ነው:: ያንን አስር አይነት ዕፅዋት በትንሹ ማንኪያ አለ፣ በትልቁ ማንኪያ አለ፣ በአንዱ ሁለት ባንዱ አንድ በአንዱ ግማሽ እነዚህ በሚቀመሙበት ጊዜ የእፅዋት ዓይነቶች ታይተውና ተለክተው ነው፣ እነዚህ ተዋህደው ነው የኪንታሮት መድሃኒት የሚባሉት:: አንድ እንጨት አይደለም:: መጠናቸውን ሳያውቁ ሌሎች እንዳያበላሹብኝ በሚል እንጂ እኔ ዝርዝሩን ሁሉ ብናገር ደስ ይለኛል:: የአቀማመሙ ጉዳይ አንዱ ለስላሳ ነው፣ አንዱ ኮምጣጣ ነው፣ አንዱ ጣፋጭ ነው፣ አንዱ ኃይለኛ ነው፣ አንዱ ደግሞ ዝልግልግ የሆነ ለሐጭ ነገር ያለው አለ:: አንዳንዱ ደም ያለው ነገር አለ፤ ነጭ ወተት የሚወጣው ነገር አለ:: /ካሴት ቁጥር 1፣ ሚያዝያ 9/2000 ዓ.ም./

የጥናቱ አካል የሆኑ ሃኪሞች መድሃኒቶችን እንቀምማለን ይላሉ፣ የተቀመመ ከሌላ ወስደን በሽተኛ እንፈውሳለን የሚል አንድም አላጋጠመኝም:: ስለዚህ ሁሉም ለሚሰጡት ህክምና እራሣቸው መድሃኒት ሰብሳቢ፣ ቀማሚ፣ መርማሪና መድሃኒት ሰጭ ናቸው:: በጠቅላላው የመድሃኒት መቀመም ችሎታውም ሆነ የማከም ጥበቡን እያንዳንዳቸው ሃኪሞች ያከናውናሉ:: ከባህል የተረከቡትን ባህሉን ጠብቆ በዚያው ልማድ እያከሙ መንዝ የሚታይበት የህክምና ዘርፍ ነው፣ የባህላዊ መድሃኒት ህክምና አሰጣጥ::



በቅባት መልክ የተዘጋጀ መድሃኒት

### 4.3.2 አሰጣጥ

የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያ በሽተኞችን የሚያክመው ጠይቆና የተጐዳውን አካል አይቶ ነው፡፡ የሃኪሙ ልምድ ታክሎበት ህክምናው ይካሄዳል፡፡ በማየትና በመዳሰስ ምርመራው ከተካሄደ በኋላ መድሃኒቱ ይሰጣል፡፡ በመድሃኒት አሰጣጡ ላይ ለምግብነት የሚያገለግሉ እንደ መድሃኒት ማገገሪ ተደርገው ስለሚሰጡ ልማድን ያለቀቀ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው አዘውትሮ የሚጠቀምባቸው እንደ ወተት፣ ማር፣ ቅቤ፣ ቡና፣ የሥጋ መረቅ፣ ሎሚ፣ ውሃ የመሳሰሉት የመድሃኒቱ አካል ሆነው ይታዘዛሉ፡፡ አብዛኛዎቹ ታካሚዎች መድሃኒቱን የሚቀበሉት በፌስታልና በወረቀት በተለያየ መጠን ተጠቅሎ ነው፡፡ ፈሳሽ መድሃኒቶችን በጠርሙስ በውሃ ላስቲክና በብልቃጥ ይይዟቸዋል፡፡

ሃጂ ኑሩ አደም ስለመድሃኒቶች አወሳሰድ በቃለ መጠይቁ ወቅት የሚከተለውን ተናገረዋል፡፡

> የሚጨሰውን ስትወስድ ሰባት ቀን የሚጨስ አለ፣ የምች መድሃኒት፣ ሦስት ቀን የሚወሰድ አለ፡፡ የሚዋጥ ስትወስድ ለሁለት ቀን ብቻ የሚሠራ ዕፅዋት አለ፡፡ ሁለት ቀን ብቻ የሚሰራ ዕፅዋት አለ፡፡ በወተት የሚወሰድበት ምክንያት ኃይሉ እንዲዳከም ነው፡፡ ወተት አፍራሽ ነው፡፡ በማር የሚወሰድበት ምክንያት ደከም ያለ መድሃኒት ተሰጥቶት፣ ማር ሙቀት ሰጭ ስለሆነ ሙቀት ሰጥቶት ወደ ሥራው እንዲመለስ ነው፡፡ በሰውነት ክብደት መጠን ተለይቶ እንዲሁም ለምትወልድና ለማትወልድ አንድ መድሃኒት እኩል መጠን አይሰጥም፡፡ /ካሴት ቁጥር 4፣ሚያዝያ 12/2000 ዓ.ም./

የሚሰጠው ህክምና ከባህል የተቀዳ ቢሆንም ልምዱና ዲሲፕሊኑ ግን የጠበቀ መሆኑን የሚያረጋግጡ መረጃዎች አሉ፡፡ ከአሰባሰብ የሚጀምረው ልዩ ትኩረት፣ በመቀመም ጊዜና በአሰጣጥም ጥንቃቄው እንደተጠበቀ መሆን ይገባል የሚሉት ደግሞ ሃኪም ፍቅረሰብ መኮንን ናቸው፡፡

> የታካሚውን እድሜ የበሽታውንም አይነት ማወቅ ይገባል፡፡ አንድ መድሃኒት ሰጭ በሽታው ተላላፊ ነው ወይስ አይደለም ማለት ይኖርበታል፡፡ መድሃኒት ሰጥቶ መሸኘ ት አይገባም፤ ከሰውየው ጋር ላይሄድ ይችላል፡፡ የጐን ችግር ሊያስከትል ይችላል፡፡ የተፈጨው ፍሬ ወይም የተወቀጠው ቅጠል ተቀምሞ ወይም እንዳለ በማንኪያ ተለክቶ መጽሐፉ እንደሚያዘው ይሰጣል፡፡ ህፃን፣ ወጣት፣ ሽማግሌ. .... እድሜን ወስኖ ይሰጣል፡፡ ወዲያው ተጭሮ የሚሰጠው ቆይቶ ከሚሰጠው ይለያል፡፡ ሲቆይ ጠቀም ማለት አለበት ወዲያው የተዘጋጀው ግን ኃይሉ እንዳለ ነው፡፡ / ካሴት ቁጥር 8፣ ግንቦት 3/2000 ዓ.ም./

የባህላዊ ህክምና መድሃኒትን ሲሰጥ የመመጠን ችግር ያለበት መሆኑን የሚያምኑና ለዚህም ጥንቃቄ ይገባዋል የሚሉት ደግሞ ሃኪም ደጀኔ ብሩ ናቸው::

> የባህል መድሃኒት ለዘመናዊው መድሃኒት ጥንት እንደዛሬው ቴክኖሎጂ ሳይስፋፋ የጥንት ሰዎች በባህል መድሃኒት በቅጠላ ቅጠል በሥራ ሥር በአለት ድንጋይ ነበር:: የባህል መድሃኒት ሃያል ነው ይፈውሳል:: ፈጣን ነው:: ትክክለኛ አዋቂ ትክክለኛ ተጠቃሚ ከተገኘ ትክክለኛ መድሃኒቶች ከተገኙ ይሰራል:: ይፈውሳል ያድናል:: ይሄ የታመነበት ነው:: የባህል መድሃኒት አዋቂዎች ዶዙን አይችሉም ነው የሚባለው፣ ትክክል ነው:: እንደ ዘመናዊው መድሃኒት በሚሊግራም እየተለካና በፋብሪካ የተቀመመ አይደለም:: አንዳንድ መድሃኒት ኃይል ነው:: በሰው ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ:: መድሃኒት አዋቂው ያንን ሃይል ያለውን ለሰው አደጋ እንዳያደርስበት ሃይሉን መቀነስ አለበት:: ኃይል መቀነሻ / ማርከሻ/ አለው:: ሳይድ ኢፌክት በሚሆን ሰዓት ማርከሻ ይሆነዋል:: መመጠን መቻል አለበት ማለት ነው:: /ካሴት ቁጥር 9፣ ግንቦት 25/2000 ዓ.ም./

በአጠቃላይ የህክምና ስልቱ የአንዱ ባህላዊ ሃኪም ከሌላው የሚራራቅ አይደለም:: መጀመሪያ እውቀቱን የጨበጡበት ሥልት እንዳለ ሆኖ በግል ችሎታና በልምድ ታካሚን ለማርካት የሚደረግ ጥረት ግን አለ:: የመድሃኒት አሰጣጡ ከሰውየው ተደራቢ በሽታ መኖርና አለመኖር ጋር ተረጋግጦ፣ መድሃኒቱ መሰጠት እንዳለበት ሃጂ አቡበከር አህመድ የሚሉት ለዚህ ማረጋገጫ ነው::

> አንተ የጨጓራ በሽተኛ ነኝ ብትል፣ አንዱ የጨጓራ በሽተኛ ነኝ ቢል፣ የሁለታችሁም የጨጓራ በሽታችሁ ደረጃ አንድ አይነት እንኳ ቢሆን ለሁለታችሁም የምሰጠው የተለያዩ መድሃኒቶች ሊሆኑ ይችላሉ:: ምክንያቱም አንተ ያን መድሃኒት የት ሆነህ ትወስደዋለህ፣ ያኛው ደግሞ እዚያ አንተ አካባቢ ሆኖ አይወስድም:: አንተ ሦስት ዓይነት በሽታዎች አሉህ፣ እርሱ ሁለት አይነት በሽታዎች አሉት ለሁለቱም የመድሃኒት አይነት ይለያያል:: ወይ አወሳሰዱ ሊለያይ ይችላል:: ወይ ብዙ ነገሮች ሊለያዩ ይችላሉ:: / ካሴት ቁጥር 6፣ ሚያዝያ 23/2000 ዓ.ም./

ከነዚህ የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች የህክምና መድሃኒት አሰጣጥ መገንዘብ የሚቻለው በአገኙት የእውቀት ዘርፍና ልምድ መሠረት የሚያክሙ መሆናቸውን ነው:: ባህላዊነቱንም የምናረጋግጠው፣ የህክምና አሰጣጡ ከነበረው ሳያፈነግጥ ወይም ሃኪሙ ይሁነኝ ብሎ

ከያዘው መንገድ ሳይወጣ ህክምናው የሚሰጥ መሆኑን ነው። ታካሚዎችም በነበረው የቆየ የህክምና አሰጣጥ መሰረት በእምነት ይገለገላሉ።

ተቀምመው በማዳበሪያ፣ በጠርሙስና በልዩ ልዩ መያዣ ዕቃዎች ከተቀመጡ መድሃኒቶች በሽተኛ ሲመጣ እየተቆነጠረና እየተቀነሰ ይሰጣል። ሃጂ አቡበከር አህመድ ደግሞ በሽተኛ ካነጋገሩ በኋላ እንደ በሽታው ዓይነት ቀምመው እንደሚሰጡ ነግረውኛል።

## 4.4 የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች አዘውትረው የሚፈውሷቸው የበሽታ አይነቶች

ለጥናት በተመረጡ የባህላዊ ህክምና መስጫ ቦታዎች ሁሉ ያገኘኋቸው ታካሚዎች በአብዛኛው ከአስሩ ሰባቱ፣ በሚያቆስል በሽታ ታመው እርዳታ የሚፈልጉ ናቸው። ሃኪሞቹ፣ ከህክምና በፊትና በኋላ ፎቶ ግራፍ አንስተው ለመረጃ የያዟቸው ታካሚዎች ሰውነታቸው የቆሰለባቸው ናቸው።



አካላቸው ላይ ቁስል ያለባቸው ታካሚዎች

ከሁሉም ሃኪሞች በተደጋጋሚ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ታካሚ የሚመጣው ከሰውነት መቁሰል ጋር በተያየዘ መሆኑን ሰባቱም ሃኪሞች በሰጡት የቃለ መጠይቅ መልስ አረጋግጠዋል። ታካሚ የሚሰቃይበት የመጀመሪያው የሚያቆስል በሽታ ኪንታሮት ሲሆን፣ ነቀርሳ ሁለተኛውን ደረጃ ይይዛል። ወቅት እየጠበቀ አልማዝ ባለጭራም ፋታ እንደማይሰጣቸው ገልፀውልኛል።

ሃኪም ተክሌ ኃብተገብርኤል የቁስል በሽታ ያለባቸው ታካሚዎች ወደ ባህላዊ ሃኪም የሚያመዝኑ መሆናቸውን ጠቁመው፣ አዘውትረው የሚያክሟቸውን በሽታዎች እንደሚከተለው ገልጸዋል::

> ዋናው ኪንታሮት ነው፣ አምስት ዓይነት ኪንታሮት ቢኖርም ቀጥሎ ነቀርሳ ነው:: የአጥንት ነቀርሳ አለ:: የደም ካንሰር አለ:: አጥንት እየተሰበረ ይወጣል፣ ይድናል:: ሰውነቱ የተቆጣጠረ፣ ደሞቹ የተቆጣጠሩ ሁሉ ይድናሉ:: ችፌ፣ አልማዝ ባለጭራ፣ ማናቸውም እባጭ የወፍ እባጭ፣ እኔ ጋ የሌለ የለም:: መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር አካባቢ አልማዝ ባለጭራ ነበር የበዛው:: ህፃናቶች ሁሉ ነበረ ለህክምና ሁሉ አስቸግሮን የነበረው እሱ ነው:: / ካሴት ቁጥር 1፣ ሚያዝያ 9/2000 ዓ.ም/

አካላዊ ቁስለት ደርሶባቸው ከዘመናዊ ህክምና ፈውስ አጥተው ወደ ህክምና መስጫቸው ከሚመጡት መካከል አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት የአልማዝ ባለጭራ፣ የኪንታሮትና የነቀርሳ በሽተኞች እንደሆኑ፣ ሃኪም ፍቅረሰብ መኮንን/ ካሴት ቁጥር 8፣ ግንቦት 3/2000 ዓ.ም./ እና ሃኪም ሃጂ ኑሩ አደም /ካሴት ቁጥር 5፣ ሚያዝያ 12/2000 ዓ.ም./ በሰጡት ቃለ ምልልስ አረጋግጠዋል:: በመቀጠልም እንደ ስንፈተ ወሲብና የውስጥ ደዌ ያለባቸውን በሽተኞች በሁለተኛ ደረጃ ያስቀምጧቸዋል:: በምልከታየ እንዳየሁትና ከሃኪሞቹ ባገኘሁት መረጃ መሠረት በአማካይ በቀን ከ10-50 ቁጥር ያላቸው በሽተኞች ህክምና ያገኛሉ:: ከእነዚህ መካከል የሚበዙት በቁስል በሽታ የሚሰቃዬ ሆነው፣ ዘመናዊ ህክምና ሞክረው ሣይሳካላቸው የቀሩ መሆናቸውን ሃኪሞቹና ታካሚዎቹ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ገልፀውልኛል:: በጋንግሪን በሽታ እግራቸው እንዲቆረጥ የታዘዙ ታካሚዎች ከሆስፒታል ወጥተው በሽታውን እንደዳኑ ሃኪም ፍቅረሰብ መኮንን ነግረውኛል:: /ካሴት ቁጥር 8፣ ግንቦት 3/2000ዓ.ም./

ሃኪም ደጀኔ ብሩ ሌሎች ያልቻሉትን በሽታ የሚፈውሱበትን መድሃኒት ሱባኤ ገብተው ማግኘታቸውን ተናግረዋል::

> በዓለም ላይ መዳን ያልቻሉ በሽታዎች መድሃኒቶቻቸው ከእኔ ጋር አሉ:: አንዱ ሱባዔ ማለት፣ ነገሮች ግልፅ እንዲሆኑልህ ነው:: ለምሣሌ የአፍ ጠረን የአፍንጫ ጠረን፣ አስም በዓለም ላይ ማስታገሻ እንጂ ማዳኛ የለውም:: እኔ ማዳኛ ነው ያለኝ:: ሳይነስ ከውስጡ ነቅሎ ድራሹን የሚያጠፋ ማዳኛ ነው ያለኝ:: እንደዚሁም:: ለሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅርቤ ዘመድ በማጣት ዝም ብለውኛል:: ዘመድ ያላቸው ተሰጥቷቸዋል:: አራት አይነት ነበር፣ የችፌ፣ የአስም የሳይነስና የነቀርሳ መድሃኒትን ነበር ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ያቀረብኩት፣ ማለፉን አልፏል ግን ፖተንት

አልተሰጠኝም:: በዘመናዊ ህክምና ሊድኑ የማይችሉ በባህልም ህክምና መድሃኒት የሌላቸው እኔጋ አሉ::/ካሴት ቁጥር 9፣ግንቦት 25/2000 ዓ.ም./

ሃኪም ሃጂ አቡበከር አህመድ አብዛኛው ታካሚያቸው በዘመናዊ የህክምና ተቋማት ሞክረው ያልዳኑ መሆናቸውን በመግለፅ ከላይ የተባለውን ያጠናክራሉ::

> በአሁኑ ጊዜ ከመቶ 90% የመጀመሪያ የህክምና ደረጃ እያጋጠመን አይደለም:: መጀመሪያ አንድ ሰው ሲታመም ወደ ክሊኒክ ይሄዳል:: ያልቻሉትን ነው 90% ያህል እያከምን ያለነው:: እነሱ ካልቻሉ ይሄ ሰው የት ይሂድ? ህብረተሰቡ እራሱ ይጠይቃል:: አንዱ ከዚህ የባህል ህክምና ሄጀ ድኛለሁ ብሎ መረጃ ይሰጠዋል:: ይሄ እንግዲህ የበሽተኛው ምርጫ ነው:: /ካሴት ቁጥር 4፣ ሚያዝያ 23/2000 ዓ.ም./

በራንክ ክሊነክ ያገኘሁዋቸውና የቆዳ ስፔሻሊስት የሆኑት ዶ/ር ሩት ሊካሳ አዘውትረው የሚገጥሟቸው ታካሚዎች በባህላዊ መድሃኒት ህክምና ጉዳት የደረሰባቸው መሆናቸውን ገልፀዋል::

> እኛ ጋ የባህላዊ መድሃኒት ወስደው የተቸገሩ ነው የሚገጥመን ስለዚህ ባያዝድ የሆነ አስተያየት ሊሆን ስለሚችል በጥናት መልክ መታየት ይኖርበታል:: ባህላዊው ምን ዓይነት ጥቅም ላይ ውሎ ውጤት አመጣ የሚለው መታየት ይኖርበታል:: እኔ ብዙ ችግር ነው የማየው አይረዳምም ለማለት አልችልም አላውቀውም:: ምን ዓይነት ነገር እንደሚጠቀሙ ማለቴ ነው:: ታካሚው በሽታዬን እያወጣልኝ ነው ሊል ይችላል:: የመረዳት ነገር ነው:: ግን ለበለጠ ጠባሳ የሚዳረጉበት ሁኔታ ስለማኖር አስቸጋሪ ነገር ነው:: ባህላዊው ህክምና መታየት ይኖርበታል:: ይሄ ቅይጥ የሆነው ነገር እንደ ባህላዊ ሊቆጠርም አይገባውም፣ ህጋዊም አይመስለኝም:: መድሃኒቱን ከባህላዊ ጋር ከቀላቀሉት ትክክለኛ ባህላዊ አይደለም:: ሌላው ግን እውነተኛው ባህላዊ የተባለው መታየት አለበት:: ለምን በሽታ ይሄን ሰጡት የተባለውንም እኮ እኛ አናውቀውም:: አንድ ሰው በዚህ ነገር ላይ የሚሠራ ካለ መድሃኒቱን ከመጠቀማቸው በፊት መታየት አለበት:: ለምን ጉዳይ ይሄን ነገር ሰጥተው ይሄን ውጤት አመጣ የሚባለው መጠናት ይኖርበታል:: እርግጠኛ ለመሆን:: /ካሴት ቁጥር 10፣ ግንቦት 28/2000 ዓ.ም./

በምልከታዬ ወቅት፣ የኪንታሮት መድሃኒት ተደርጉለት በመዳን ላይ ያሉ ጎልማሳ እና በባዮሎጂ ቢኤ ያለውና በመምህርነት ሥራ ተሠማርቶ የሚገኝ፣ ሁለቱም ታካሚዎች፣

ከሚታከሙበት አልጋ አግኝቻቸው ያረጋገጡልኝ ዘመናዊ ህክምና ሊያሽላቸው አለመቻሉን ነው::

## 4.5 መንፈሳዊ ህክምና እምነት በባህላዊ ህክምና ዘርፍ

መንፈሳዊ ህክምና በባህላዊ ሃኪሞች የሚዘወተር የህክምና ዘርፍ ነው:: ከአነጋገኳቸው ሰባት የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች መካከል መንፈሳዊ ህክምና የቆየና መፍትሄ ሰጭ እንደሆነ አረጋግጠውልኛል::

ከጥንት ጀምሮ ህብረተሰቡ ይፈወስበት የነበረውን፣ የመንፈሳዊ ህክምና ስርዓት የመድሃኒት መጽሐፉ በሚያዘው መሠረት የመንፈሳዊ ህክምና ዘዴ ተጠቅመው በሽተኞችን እንዳዳኑ እንጂ አዲስ ነገር እንዳልፈጠሩም ይናገራሉ:: በሌላ በኩል ዘመናዊ ህክምና ስለአልደረሰበት ህክምናው አያድንም ማለት ተገቢ አይደለም ባይ ናቸው:: መንፈሳዊ የህክምና ዘርፍን ከሚቀበሉት አንዱ ሃኪም እርገጤ ከበደ ናቸው::

> ለምሣሌ የሚጥል በሽታ፣ የአእምሮ በሽታ፣ የመንፈስ በሽታ አለ:: ክርስቶስን ምንድን ነው ያለው? አንተ ልታጠፋን መጣህን ነው ያለው:: እርኩስ መንፈሱን አወጣው፣ ወደ ሪያዎች ገባ (ማርቆስ 5፣10-13):: ይህ መንፈሳዊ ህክምና ነው:: ፀበል ተረጭቶ ያድናል:: ካቶሊክ፣ ኦርቶዶክስ እንደዚህ ነው:: እስላም ጫት ቅመው፣ ዱአ አድርገው አላህ ብለው ያድናሉ:: ዘመናዊ ህክምና ይህን ከባዕድ አምልኮ ወይም ከመጥፎ ነገር ጋር ፈርጀውት ሊቀበሉት አልቻሉም:: በእኛ ግን በባህላዊ ህክምና ፀበሉን፣ ፀሎቱን፣ ቅዱሣት መጸሕፍቱን ሁሉን አብሮ ነው ማወቅ መቻል ያለበት:: / ካሴት ቁጥር 2፣ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም./

ሃኪም ሃጂ አቡበከር አህመድም የሃኪም እርገጤን ሃሣብ ይደግፋሉ:: ለጊዜው በእኛ ሃገር ዘርዝሮ ለማስረዳት የሚያስቸግር ነገር ቢኖርም መንፈሳዊ ህክምና፣ ዘመናዊ ህክምናም ሣይመጣ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ የህክምና ዘርፍ መሆኑን ገልፀውልኛል:: ሲያጠቃልሉም፣ ዘመናዊ የህክምና ዘርፍ በተስፋፋበት አሜሪካ መንፈሳዊ ህክምና ይሠራል እኔም ከዚያ አገር ሆኜ ብጠየቅ ሁሉን እገልፅ ነበር ብለውኛል:: /ካሴት ቁጥር 6፣ ሚያዝያ 23/ 2000 ዓ.ም./

ባህላዊ የህክምና ጥበብ ባለሙያዎቹ ከያዙት እምነት ጋር አገናኝተው መንፈሳዊ ህክምናውን የሚሰጡ አሉ:: ሃኪም ተክሌ ኃብተገብርኤል የሃይማኖት መፃሕፍትን እየደገሙ የመንፈሳዊ ህክምና ፈውስ ይሰጡ እነደነበር ተናግረዋል::

ድርሳነ ሚካኤል እየደገምኩ አጠምቅ ነበር:: በአንፆኪያ፣ ገንዛ፣ ማጀቴ፣ ካራቆሬ፣ አጣዬ አገር ድረስ እየሄድኩ አጠምቅ ነበር:: የሚያስጮሃቸው ሰዎች ሁሉ እዚህ ቦታ ያዝኩት እያለ እየለፈለፈ ይለቅ ነበር:: አዲስ አበባ ከመጣሁ በ55 ዓ.ም ጀምሮ ያ መንዜው ድርሳን አጥማቂው እየተባልኩ ነው የታወኩት:: እመጫቶች አራስ ቤት የተለከፉ ቆበር የሚያስደፍቃቸው፣ የሚጥላቸው እነዚያን ሁሉ እያጠመኩ ነበር:: ከክ/ሃገር ሁሉ እየመጣ ካራቆሬ ድረስ የወሰዱኝ ያበደ ሰው ነበር:: እሱ ያድነዋል ብለው ነው እዚያ ሄጄ አድኘዋለሁ:: /ካሴት ቁጥር 1፣ ሚያዝያ 9/2000ዓ.ም./

መንፈሳዊ ህክምናን በተመለከተ የቆዳ ስፔሻሊስት ዶ/ር ሩት ሲካሳ እንዲሁም ከጥቁር አንበሳ የሥነ ልቡና ስፔሻሊስት ዶ/ር አታላይ ዓለም የሰጡኝ ሙያዊ አመለካከት በቅደም ተከተል የሚከተለው ነው::

መንፈሳዊ ህክምና እኔ ጠቀሜታ አለው ነው የምለው:: ብዙ የጤና ባለሙያዎች ያምናሉ:: የእያንዳንዱ ሰው እምነት የተለያየ ቢሆንም:: በእርግጥ አዕእሮአችን አካላችን፣ ሁለንተናችንን የሚቆጣጠር እንደ መሆኑ በመንፈሳዊ ነገር ይረዳል:: ሆኖም ግን በሽታ የሆኑ ነገሮች ከሆኑ ደግሞ ህክምና የግድ ያስፈልጋቸዋል:: ሁለቱን አንድ ላይ አስታርቆ መሄድ ደግሞ ይቻላል:: ነገር ግን ለሁሉም ሰው አንድ አይነት መፍትሄ መስጠት አይቻልም::እንደ የግለሰቡ ይለያያል አሠራሩ:: እኛ የምናምነውን ነገር ሌላው ላይ ተፅዕኖ ልናደርግ መብት የለንም:: ያ ደግሞ ሙያዊ (Ethical) አይደለም:: ግን ሐሳብ መስጠት እንችላለን:: መንፈሳዊና ዘመናዊ ህክምና አብሮ አይሄድም የሚል እምነት የለኝም:: እንደዚያም አይደለም አብረው ይሄዳሉ:: /ካሴት ቁጥር 10፣ ግንቦት 28/2000 ዓ.ም./

ስለ መንፈሳዊ ህክምና በእኛ ሙያ በተለይ በጣም ትኩረት እየተሰጠው ያለ ጉዳይ ነው:: ሰው መንፈሳዊ ነው፣ ሥጋዊም ነው፣ ስሜታዊም ነው:: ስለዚህ በነኝህ ሁሉ አካባቢዎች እርዳታ ያስፈልገዋል:: ከዚህ የተነሣ በተለይ በምዕራቡ ዓለም Chapliain የሚባል፣ በፀሎትና በምክር የሚደግፍ ሰው ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው አለ:: ስለዚህ ይደግፋቸዋል፣ ይረዳቸዋል:: መንፈሳዊው ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ጉዳይ የነርሱ ዋጋ የሚሰጡበት ነገር ስለሆነ በዚያም አካባቢ ከህመማቸው ጋር ተገናኝቶ አሁን ብሞት የት እሄዳለሁ የሚለው ጥያቄ እኮ የሁሉ ሰው ጥያቄ ነው:: እሱንም አስመልክቶ የሚረዳቸው መንፈሳዊ የሆነ ሰው በየሆስፒታሉች ተቀጥሮ የሚሠራበት ሁኔታ ነው ያለው:: ስለዚህ ድጋፍ ነው፣ ይረዳል ተብሎ ይታመናል:: /ካሴት ቁጥር 10፣ ግንቦት 29/2000ዓ.ም./

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች መንፈሳዊ ህክምናውን እንደሚሰጡና እንደሚያድኑ ይግለፁ እንጂ ዘመናዊ የህክምና ተቋም እውቅና እንደማይሰጠው ከጤና ጥበቃ መሃመድ ዘይኑ እንደሚከተለው ገልፆታል:: «መንፈሳዊ ያልከው አስቸጋሪ ነው ለመለካት አይቻልም ለምሣሌ አድናለሁ ይላል፣ እንዴት ታድናለህ ብለህ ስትጠይቀው መለካት አይቻልም:: ኪሊቲውንም፣ ሴፍቲውንም፣ አድናለሁ ብሎ ቢገድል ተጠያቂው ማን ነው? በዚህ በዚህ አድናለሁ ብሎ አቅርቦ የተለካ ነገር የለም:: ከዚህ አንፃር ነው ጤና ጥበቃ መንፈሳዊውን ክፍል እውቅና ያልሰጠው::» /ካሴት ቁጥር 5፣ ሚያዝያ 22/2000 ዓ.ም/

ከጤና ጥበቃና ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ በተገኘው መረጃ መሠረት መንፈሳዊ ህክምና በዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ዘንድ እውቅና አልተሰጠውም:: የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች በሽታው አለ፣ ፈውሱም አለ ይላሉ:: ህክምናው ባህላዊ መንገድን በተከተለ ስልት የሚሰጥ እንደሆነም ከሰጡት መረጃ መገንዘብ ይቻላል:: ታካሚዎች ደግሞ መፍትሔ እናገኝበታለን ወደሚሉት ባለሙያ መሄዳቸው አልቀረም:: ስለሆነም ህብረተሰቡ ለዘመናት እንዴት ተጠቀመበት፣ ምን ተጨባጭ ውጤት አግኝቶ ስንል፣ ለዘመናት የቆየውና በመደጋገም ከህብረተሰብ ጆሮና ልብ የገባ አስሮ የያዘ የኑሮ መላ መሆኑን እናስተውላለን:: ህብረተሰቡ የተቀበለውና ደጋግሞ የሚጠቀምበት ከሆነ ደግሞ ፎክሎር የምንለው ማኅበራዊ ግኝት ተገለፀ ማለት ነው::

ተጠኝ የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች እንደገለፁት ድግግሞሽ/ ሁሉም የህክምና ጥበቡ ከጥንት የመጣ ነው ብለዋል/ ሲውል ሲያድር ተቀባይነቱ የማይቀር መሆኑ ነው:: የተቀመሙ መድሃኒቶችን ተጠቅሞ ማዳኑ ብዙም ላያጠያይቅ ይችላል:: ነገር ግን መንፈሣዊ ህክምናው ከህብረተሰቡ የኑሮ አውታር ውስጥ የገባ የማዳን ሥልት እንጂ የሚለካ ነገር የለውም:: ሰው ሥጋዊ ብቻ ሣይሆን መንፈሳዊ በመሆኑ ከሥጋዊ ህክምና ጋር መንፈሳዊ ህክምና ጥቅም እንጂ ጉዳት እንደሌለው በዘመናዊ ህክምና ሥራ ላይ የተሰማሩ ዶክተሮችም ቢሆኑ ይመክራሉ:: በዚህ የህክምና ዘርፍ የተሰማሩ የባህላዊ ህክምና ባለሙያዎች ከእምነት ተቋማት መምጣታቸው ደግሞ ለተቀባይነቱ የጐላ አስተዋጽኦ አበርክቷል ማለት ይቻላል::

### 4.5.1 እምነት በባህላዊ ሃኪሞችና ታካሚዎች ላይ

Faith Healing- A term used to express a belief that in the curing of disease the faith of the sufferer (or of others) is a contributory factor. This faith puts its trust in the immediate action of a super- normal being, acting with or without means. In the stricteset sense, therfore, faith healing may be said to exclude the use of visible means of healing; but in the wider sense, in the sense, that is to say, in which faith healing occurs as a histirical phenomenon it admits such means as one factor in the process of healing. The principal species are named mental

healing, magntic healing, spiritualistic healing and spiritual healing. /Encyclopedia of religion and ethhics Vol.5, 697-698/

የእምነት ፈውስ ጽንስ ሃሳቡ ከማመን ጋር የተያያዘ ሲሆን የታማሚው/የተጠቂው/ እምነት ከበሽታው ለመዳን /ለመፈወስ/ አስተዋጽኦ አለው:: እምነቱ ከተለምዶ ውጭና በላይ በሆነ መንገድ ፈጣን ለውጥ እንዲያስከትል ከተለምዶ ውጭና ከላይ በሆነ ኃይል ላይ መደገፍ አለበት እንጂ የሚታይ ወይም ተጨባጭ የሆነ የፈውስ መንገዶችን አይጠቀምም:: ነገር ግን ውስጣዊ በሆነ እንደ ታሪካዊ ክስተት ይገለፃል:: የእምነት ፈውስ ዓይነቶች ብዙ ናቸው፤ አእምሯዊ ፈውስ፣ መግነጢሳዊ ፈውስ፣ መንፈሳዊ ፈውስና የመሳሰሉትም እንደመጠሪያ ያገለግላሉ::

«አረቦች እምነት ግማሽ መድሃኒት፣ ግማሽ ፈውስ ነው ይላሉ::» /ኑሩ፣ ካሴት ቁጥር 4፣ ሚያዚያ 12/2000 ዓ.ም./

እምነት የተቀበልነው ብቻ ሳይሆን የምንኖርበት መሆኑን የባህላዊ መድሃኒት ህክምና አሰጣጥ በተጨባጭ ያስረዳል:: የዚህን ምክንያት ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ዕዝራ ሙሉነህ አብራርተውታል:: «የኢትዮጵያ የባህል ህክምና ሲባል ምንጩ እምነት ነው:: ወይ የክርስትና እምነት ወይ የእስልምና እምነት ተከታዮች ናቸው:: አንደኛው በእምነት መንፈሣዊ በሆኑ ነገሮች ሳይካትሪ የሆኑ ነገሮችን Solve እናደርጋለን ስለሚሉ በዚያ መልኩ ይሄዳል::»
/ ካሴት ቁጥር 8፣ ሚያዝያ 28/2000 ዓ.ም/

የዘመናዊ ህክምና ባለሙያው የገለፁትን በባህላዊ መድሃኒት ህክምና የተሰማሩት ባለሙያዎችም ያረጋግጡታል:: እምነት በባህላዊ መድሃኒት ህክምና ከፍተኛውን ቦታ ሊይዝ ይገባዋል ከሚሉት መካከል ሃኪም ተክሌ ኃብተገብርኤል አንዱ ናቸው:: በእሳቸው አመለካከት የባህላዊ ህክምና አሰጣጥ ያለ እምነት ቦታ የለውም::

ወደ እኔ ሲመጡ የምላቸው በእግዚአብሔር እመኑ እኔ አይደለሁም የማድን ነው የምላቸው፣ ምክንያቱም ሃኪሙም ጋ እግዚአብሔር ሲኖር ነው ሰውየው መዳን የሚችለው:: ፀበል ማለት ምን ማለት ነው? ፀበል ውሃ ነው:: ስትጠመቅበት እግዚአብሔር ሆይ አድነኝ ብለህ፣ እውነቱን ከሆነ በአይን የማይታየው በእጅ የማይዳሰሰው እርኩስ መንፈስ ጮኾ ይወጣል:: ይችም ዕፅዋት ናት፣ የፈጠራት እግዚአብሔር ነውና መድሃኒት እንዲያደርግላችሁ እግዚአብሔር ሆይ በዚህ ላይ ሆነህ አድነኝ ብላችሁ ለምኑ፣ እመኑ እኔ ሰው ነኝ ብዬ እነግራቸዋለሁ:: እኔ ደግሞ የዘወትር ፀሎቴ ፈጣሪዬን እለምናለሁ:: በሽተኞችን ሁሉ ፈውስልኝ፣ ስሙ የእኔ

ቢሆንም አንተን አምነው እኔ አንተን አምኘ ነውና የምሰጠው፣ መድሃኒት አድርግልኝ ብዬ ቆሜ ተነስቼ እለምናለሁ:: የሚቻለኝንም ሁሉ ለእግዚአብሔር መስዋዕት አደርጋለሁ:: /ካሴት ቁጥር 1፣ ሚያዝያ 9/2000 ዓ.ም/

በሙያው ከቆዩ ከእኒህ ሃኪም የምንረዳው፣ እምነት የባህላዊ ህክምና አንዱ ዘርፍ መሆኑን ነው:: ከዚህ በተጨማሪ «መድሃኒት እግዚአብሔር የሰጠን ፀጋ ነው:: ሰይጣን ነው ለችግር የዳረገው:: በፈጣሪ ስም እነዚያን መድሃኒቶች ቢጠቀም መልካም ነው፤ ይፈውሳል:: እኔ የመጣሁበት የእምነት ቦታ ነው:: ዛሬም አማኝ ነኝ» / ካሴት ቁጥር 8፣ ግንቦት 3/2000 ዓ.ም/ ይላሉ ሃኪም ፍቅረሰብ መኮንን::

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ታካሚዎችም የፈውሳቸው ምንጭ እምነት እንደሆነ ተናግረዋል:: ከሃጂ ኑሩ አደም ህክምና ሲከታተሉ ያገኘኋቸው የ66 ዓመት እድሜ ያላቸውና ወንድ ታካሚ የተናገሩት ለዚህ ተጠቃሽ ይሆናል:: «መድሃኒት ሰበብ ነው የሚያዝልን ያው ዋናው ፈጣሪ ነው የሚያድነው:: የሚያሳምመውም ፈጣሪ ነው:: ግን ሌላው ሰበብ ነው የሚሆነው ምክንያት ነው የሚሆነው በእርሱ ተመስሎ ያው ፈጣሪ ነው የሚያድነው::» /የካሴት ቁጥር 4፣ ሚያዝያ 12/2000 ዓ.ም./

የማዳን ስልጣኑ የእግዚአብሔር ነው:: ሃኪም ምክንያት ነው:: የሚል እምነት ያላቸው ሌላ ታካሚ ያገኘሁት ከሃኪም ማሞ ኃይሌ የህክምና መስጫ ቦታ ነው:: እኒህ የ40 ዓመት ሴት ታካሚ ፈውስ ከአምላክ ውጭ የለም የሚሉና ለምክንያት ግን በተደጋጋሚ ወደ ባህላዊ መድሃኒት የህክምና ባለሙያ እንደሚሄዱ ነግረውኛል:: /ካሴት ቁጥር 3፣ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም./

ከባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች የተለየ አመለካከት ያላቸው ሃጂ ኑሩ አደም እምነት «የአደኙ ሣይሆን የዳኙ ነው» የሚል አስተያየት ሰጥተዋል::

በዚያም ተባለ በዚህ እምነት በባህላዊ መድሃኒት ህክምና ላይ ተጽዕኖው ከፍተኛ መሆኑን ከቀረቡት መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል:: አካሚና ታካሚም እምነትን አስቀድመው ፈውስን በጋራ ይጠብቃሉ ማለትም ይቻላል::

## 4.6 የባህላዊ ሃኪሞች እየሰጡት ያለው አገልግሎት

በአዲስ አበባ ያሉ የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች ቁጥር በውል አይታወቅም:: የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ በአንድ ወቅት ጥሪ አድርጎ 140 ተመዝግበው እንደነበር በቃለ መጠይቁ ወቅት ገልፃልኛል::

በምልከታየ ወቅትም ሆነ ያነጋገርኳቸው ሃኪሞች እንዳረጋገጡልኝ በአማካይ በቀን አንድ የባህላዊ ሃኪም ከ 10 እስከ 50 ሰዎች ያክማል:: በተጠቀሰው ቁጥር መሠረት:- የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች በቀን 1400-7000 ታካሚ ያስተናግዳሉ ለማለት ይችላል:: / የባህላዊ ሃኪም ከ300 እንዳማያንስ ሃኪም ተክሌ ገልፀውልኛል/:: ይህን ያህል ፈውስ ፈላጊ ሰው የባህላዊ ሃኪሞችን ደጅ የሚረግጠው አስር የመንግስት ሆስፒታሎች፣ ሃያ አምስት የግል ሆስፒታሎች፣ 355 ከፍተኛና መካከለኛ ክሊኒኮች ባሉበት የሃገሪቱ ዋና ከተማ ነው::

### 4.6.1 ታካሚዎች ለባህላዊ ህክምና ያላቸው አስተያየት

በባህላዊ መድሃኒት የህክምና መስጫ ቦታዎች ያገኘኋቸውና ያነጋገርኳቸው ታካሚዎች የኦርቶዶክስ፣ የእስልምና እና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ናቸው:: ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ የሆኑት ሦስት የኦርቶዶክስ፣ ሁለት የሙስሊምና ሁለት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ናቸው:: ይህም የባህላዊ መድሃኒት ህክምና በማንኛውም እምነት ተከታይ ተቀባይነት እንዳለው ያመለክታል::

ከሃኪም ማሞ ኃይሌ ለመታከም መጥተው ያነጋገርኳቸው ሴት፣ ባህላዊ የህክምና ጥበብ መፍትሄ ሰጭ መሆኑን ያምናሉ::

> ብዙ ጊዜ የተጠቀምኩት በባህላዊ ነው:: ሃኪም ማሞ ጥሩ አባት ናቸው:: እኔ በእድሜዬ የመጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ሃኪም ብላቸው ደስ ይለኛል:: በሙያቸውም፣ በርህራሄያቸውም ድሃ ነው ሃብታም ነው ሳይሉ ድሃም ሳይከፋፈል የሚታከምበትና የሚረዳበት አለ:: በሙያቸው ደግሞ ከማንም በላይና የታሪክ ሰው ናቸው:: ቢያንስ ከ20 ዓመት በላይ አውቃቸዋለሁ:: /ካሴት ቁጥር 3፣ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም/

እኒህ ታካሚ ሰውነታቸው በአንድ ወቅት መንቀቀስ አቁሞ አልጋ ላይ ውለው ነበር:: ሃኪም ማሞ ኃይሌ ባደረጉላቸው ህክምና መዳናቸውን ገልፀውልኛል:: ያነጋገርኳቸው ለሌላ በሽታ ህክምና መጥተው ነው:: እንደ ሃኪም ማሞ ኃይሌ ረጅም ዓመት የባህላዊ ህክምና አገልግሎት ሲሰጡ ከኖሩት ሃኪም ተክሌ ሃብተገብርኤል ለመታከም መጥተው ያገኘኋቸው

ሴት ለቃለ መጠይቁ በሰጡት መልስ ለተወሰኑ በሽታዎች የባህለዊ ህክምና ባለሙያዎች ይሻላሉ ብለዋል።

> እንዲህ እንደካንሰር እንደ ነቀርሳ ያሉ ነገሮች፣ ይሄ የራሴ እምነት ነው፣ የራሴ ፍላጐት ነው፣ ጡቴን ታምሜ ስሄድ ሃኪሞች ለምርመራ ቆንጥረው ሊወስዱ ይችላሉ። እኔ ይህን አልደግፍም፤ አልስማማበትም። እኔ በሃገር ባህል መድሃኒት እታከማለሁ፣ ታክሜአለሁም፣ ድኛለሁም። ጡቴን ታምሜ ታክሜ ድኛለሁ። እዚሁ ቤት፣ አቶ ተክሌ ቤት፣ የእህቴንም ልጅ አምጥቼ ከክፍለ ሃገር እሷም ድና አሁን እንዲያውም ውጭ ነች ደቡብ አፍሪካ። /ካሴት ቁጥር 1፣ ሚያዝም 9/2000 ዓ.ም/ ሲሉ ምስክርነታቸውን ስጥተዋል።

ከሃጂ ኑሩ አደም በኪንታሮት በሽታ በመታከም ላይ አግኝቻቸው ያነጋገርኳቸው የገጠር ሰው የሰጡኝ መልስ የባህላዊ ህክምና የመጨረሻ አማራጭ ነው የሚለውን አስተሳሰብ የሚያረጋግጥ ነው። ታካሚው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይና የ66 ዓመት ዕድሜ ባለቤት ናቸው።

> *ለዘመናዊ ህክምና ሠላሳ ስድስት ከብት ነው የጨረስኩት። ለኪንታሮት በሽታ ዘመናዊ ህክምና ነው የተከታተልኩት። መድሃኒት ነው የሚዋጥ መድሃኒት ነው። እንደዚህ እንደዚህ ነገር ነው የሚሰጠኝ። ምንም መፍትሄ አላገኘሁም። በፊት ወደ ውስጥ ነበር። ወደ ውጭ አሁን ነው እንትን ብሎ እየደማ ነው ያስቸገረኝ፣ ምንም መፍትሄ አላገኘሁም። ሰላሣ ስድስት ከብት ነው የጨረስኩት። / ካሴት ቁጥር 4፣ ሚያዝያ 12/2000 ዓ.ም/*

እኒህ ታካሚ አልጋ ይዘው ህክምና እየተከታተሉ ቃለ መጠይቅ ባደረኩላቸው ጊዜ ከሁለትና ከሶስት ቀን በኋላ የኪንታሮት በሽታው እንደሚወጣላቸው ነግረውኛል። በዚሁ ጊዜ ለኪንታሮት በሽታ ህክምና ተደርጐላቸው የተሻላቸውን ጐልማሣ ቁስሉን አይቻለሁ።

በባዮሎጂ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለውና በማስተማር ሙያ የተሰማራው ወጣት ከሃጂ ኑሩ አደም ለኪንታሮት በሽታ ሕክምና ላይ አግኝቸው፣ ህክምናውን ሲከታተል እንደቆየና አሁን ግን በመዳን ላይ መሆኑን ገልጾልኛል።

በባህላዊ ህክምና ፈውስ ያገኙ ታካሚዎች የጽሑፍ መረጃ ከነአድራሻቸው ያሰፈሩበት ሁኔታም አለ። ከስድስት ታካሚዎች የጽሁፍ መረጃ መካከል የሁለቱ የሚከተለው ነው።

በመጀመሪያ የማክበር ሰላምታዬን እያቀረብኩ፣ ከዚህ በታች ስለሃኪም ፍቅረሰብ ያለኝንና የተደረገልኝን አስተያየት ስስጥ በደስታና በኩራት ነው:: ከአሁን በፊት ከ6 ወር በላይ እጄን ያሳክከኝ እና በጣም እየቆሰለ ሰው ሰላም ለማለት የማፍርበት ደረጃ ደርሼ ነበር:: በኋላ መጽሔት ሳነብ፣ የእሳቸውን አድራሻ እና ማስታወቂያ በማየቴ ወደዚህ ቦታ መጥቼ የ6 ወር ስቃይ በ7 ቀን ለመገላገል ችያለሁ:: ለዚህ አጋጣሚ ሃኪም ፍቅረሰብን ከልቤ አመሰግናለሁ:: አሁን ያለምንም መሳቀቅ ሰው ሰላም እላለሁ:: ስለሃኪም ፍቅረሰብ የሚያናግረኝ ካለ አድራሽዬ ባህርዳር ቀበሌ 10 ስልክ 0918760723

ተመስገን ገላው/ ፊርማ አለው/

3/10/98

በመጀመሪያ የማክበር ሰላምታዬን እያቀረብኩ ወ/ሪት ለተብርሃን በርሄ የተባልኩ ስሆን መግለፅ የምፈልገውም ነገር እንደሚከተለው ነው:: ይኸውም ከአሁን በፊት በሆድ ህመም ለተወሰነ ወራት ወይም አመታት በጣም ስታመም ቆይቼ የተለያዩ ሆስፒታል ብሄድም ምንም በበሽታዬ ላይ ለውጥ ላገኝበት ባለመቻሌ ሐኪም ፍቅረሰብ ባህላዊ ህክምና አገልግሎት ሆስፒታል መጥቼ ህክምና ወስጄ እና በህክምናው መሠረትም የሚከለከሉትን ነገሮች ሳልነካ በተባልኩት መሠረት መድሃኒቴን ወስጄ በአሁኑ ከበሽታው ነፃ ስለሆንኩ እንደእኔ በዚህ ህመም በሽታ ለምትሰቃዩ እህቶቼም ወንድሞቼ ይሄንን አስተያየት አንብባችሁና ምንም ሳትጠራጠሩ ብትጠቀሙ መፍትሄ እንደሚሆን ነው::

አድራሻዬንም ለምትፈልጉ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12/11 ስልክ ቁጥር 011 4 662844

ለተብርሃን በርሄ
የማይነበብ ፊርማ አለው::

በተፃፈው አድራሻ መሠረት ደውዬ ታካሚውን በማነጋገር የተፃፈው እውነት መሆኑን አረጋግጫለሁ:: ከየሃኪሞቹ ለመረጃነት ተዘጋጅተው ያየኋቸው የታካሚዎችን ፎቶ ግራፎች ባህላዊ የህክምና ዘርፍ በሰፊው እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ ያመለክታሉ::

በአጠቃላይ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በጽሁፍና በፎቶ ግራፍ ያገኘኋቸው መረጃዎች ባህላዊ ህክምና ሰፊ አገልግሎት እየሰጠ፤ ታካሚም ያለማቋረጥ እየጐረፈበት መሆኑን ለመረዳት አስችሎኛል:: የተሰጠው የታካሚዎች ምስክርነትም፣ ሃኪሞቹ እንፈውሳለን የሚሉትን የበሽታ ዝርዝር ሙሉ በሙሉ ማረጋገጥ ባይቻልም፣ ከተገኘው መረጃ በመነሳት

በባህላዊ መድሃኒት ህክምና ዘርፍ ሃኪምና ታካሚ ዛሬም እንደጥንቱ ግንኙነታቸው እንደጠበቀ ነው ማለት ይቻላል::

## ማጠቃለያ

ዘመናዊ ህክምና በተሻለ ሁኔታ በሚገኝበት በአዲስ አበባ ከተማ፣ የባህላዊ መድሃኒት የህክምና አገልግሎት በስፋት በመስጠት ላይ ይገኛል:: የህክምና አገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆኑት ደግሞ የገጠርና የከተማ ነዋሪዎች፣ ዘመናዊ ትምህርት የተማሩና ያልተማሩ ናቸው:: የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ በተለያየ የእድሜ ክልል የሚገኙ ሴትና ወንድ ፈውስ ፈላጊዎች የህክምናው ተጠቃሚ ናቸው:: የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎቹም ከክርስትናና ከእስልምና እምነት ተቋማት የወጡና የህክምና ጥበቡንም ከወጡበት ሃይማኖታዊ ተቋም አገኘነው ያሉ ናቸው:: የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎችና ታካሚዎች የህክምናው ፈውስ መነሻና መድረሻ እምነት መሆኑም ተመልክቷል::

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ከትውልድ ትውልድ በቅብብል ዛሬ ላይ የደረሰው፣ ህብረተሰቡ እንደ ዋና የጤና ችግር ማቃለያ እየተጠቀመበት ነው:: በመሆኑም በህብረተሰቡ ሥነ ልቡና ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቷል፡ ህክምናውን የሚሰጡት ከሃይማኖት ተቋማት የወጡና የተከበሩ ሰዎች መሆናቸው ደግሞ ህክምናውን የታመነ እንዲሆን ረድቶታል::

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች መድሃኒቱን የሚቀምሙት በአገራችን ከሚገኙ የተፈጥሮ ሃብቶች ነው:: ይህ በተፈጥሮ ሃብታችን ያለ ከፍተኛ ወጪ መጠቀምን ያሳያል:: በተለይ ለህብተሰቡ በቅርበትና በፍጥነት አገልግሎት ስለሚሰጡ ባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎችን ተመራጭም ያደርጋቸዋል:: የአገልግሎቱ ክፍያ ከዘመናዊ ህክምና ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ መሆኑ ደግሞ ተፈላጊነቱን ከፍ አድርጎታል:: ይህ ሁሉ ተግባር በአገር በቀል እውቀትና በአገር በቀል ሃብት የሚሰጥ በመሆኑ ከተጠቃሚ ቁጥር አንጻር ሲታይ አስተዋፅኦው ቀላል አይደለም:: ስሆነም የአገር ሃብትን በአገር ልጅ መጠቀም አስችሏል ማለት ይቻላል::

የባህላዊ መድሃኒት ሃኪሞች ህክምናውን የሚሰጡት መድሃኒቶችን ከተለያዩ የገጠር አካባቢዎች በማስመጣት ነው:: መድሃኒቶቹ በተለየ ሥርዓት የሚሰበሰቡበት ሁኔታም አለ:: ለመድሃኒቶች የተገባ ቃል ኪዳን ነው በሚባለው፣ በፀሎት፣በልዩ መቁረጫና መቆፈሪያ፣ ሰዓትና ወቅት ተጠብቆ «የፈውስ ኃይላቸው እንዲጨምር» ይሰበሰባሉ:: መድሃኒትነቱ እንጂ ስርዓቱ አይጠቅምም የሚሉ ባለሙያዎች ከመካከላቸው አሉ::

መድሃኒቶች የሚገኙበት ወቅት፣ ቦታ፣ ለመድሃኒት የሚደርሱበት እድሜ እና የአገልግሎት ዘመን ታውቆ መሰብሰብና ጥቅም ላይ መዋል እንዳለባቸው በቃለ መጠይቁ የተካተቱ

ባለሙያዎች የተስማሙባቸው ነጥቦች ናቸው። ከዕፅዋት የሚዘጋጁ መድሃኒቶች ከተሰበሰቡ በኋላ፣ ሣይደርቁ ወይም ከደረቁ በኋላ ይወቀጣሉ፣ ይፈጫሉ፣ ይነጠራሉ ወይም ይደፈደፋሉ። እንደየሃኪሙ የእውቀት መነሻና የህክምና መመሪያ መጽሐፉ እንደሚያዘው ተመጥነውና ተቀምመው ለበሽተኛ ይሰጣሉ።

መረጃዎች እንዳስረዱት የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች አዘውትረው የሚፈውሷቸው በሽታዎች ከሰውነት መቁሰል ጋር የተያያዙ ኪንታሮት፣ ነቀርሳ አልማዝ ባለጭራ፣ ችፌ፣ የቆላ ቁስል የመሳሰሉትን ነው። የጠረን ችግር፣ የውስጥ ደዌ፣ ከነርቭ ጋር የተያያዙና መንፈሳዊ ህክምናን ተከታይ ያደርጓቸዋል። ታካሚዎችም በዘመናዊ ህክምና መፍትሄ ያጡለትን በሽታ በባህላዊ መድሃኒት ህክምና ፈውስ እንዳገኙለት በቃለ መጠይቅና በጽሑፍ አረጋግጠዋል።

ከዘመናዊ ህክምና ባለሙያ የቆዳና የሥነ ልቡና ስፔሻሊስት ዶክተሮች፣ ሰው አካላዊ፣ መንፈሳዊና ስሜታዊ ስለሆነ በእነዚህ ሁሉ ህክምና ያስፈልገዋል ሲሉ፣ ጤና ጥበቃና የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ደግሞ መንፈሳዊ ህክምና ሊለካ ስለማይችል እውቅና እንደሌለው ገልፀዋል።

በሌላ በኩል የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎች ዘርፉ ገቢ የሚያስገኝ ክፍት የሥራ መስክ ስለሆነ አክማለሁ ብሎ የበሽታ ስም የዘረዘረ ሁሉ እውነተኛ ባለሙያ አይደለምና ችሎታ ያለውና የሌለው በሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ይለይ ሲሉ አሳስበዋል። የዘመናዊ ህክምና ባለሙያዎችም በበኩላቸው መድሃኒት በውል ታውቆ መሰጠት ይኖርበታል። አሁን ባለበት ሁኔታ ግን የተደባለቀ ስለሆነ ስርዓት ማስያዝ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የባህላዊ መድሃኒት ህክምና በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካቶ እንዲስፋፋ ቢደረግ አገራችን በዚህ ዘርፍ የውጭ ምንዛሬ ልታገኝበት ትችላለች። የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ባለሙያዎችም «መድሃኒት ከተነገረ ይረክሳል የሚለውን የጥንት እምነት ትተው ያላቸውን እውቀት ቢያካፍሉ እርስ በርሳቸውም ተቀራርበው ለሙያው ማደግ የበኩላቸውን ጥረት ቢደርጉ ጥቅሙ የወል ይሆናል።

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ይህን ችግር ለማስወገድ የባህላዊ መድሃኒት ሃኪምንና የህክምና አሰጣጡን በተመለከተ ረቂቅ አዋጅ አውጥቶ የሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲያፀድቅለት ልኳል። ከዚህ የጤና አገልግሎት ዘርፍ የተባለው ደንብና መመሪያ ፀድቆ ሥራ ላይ ቢውልና ለባለሙያዎቹም ክትትልና ቁጥጥር ቢደርግላቸው በሌሎች አገር የሚሰማው እድገት በእኛም አገር ተግባራዊ ይሆናል።

# የዋቢ ጽሑፎች ዝርዝር


በቀለች ቶላ :: *ህክምና በቤታችን* :: አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፣ 1999 ::

አለማየሁ ዘሪሁን :: « የኑዌር ማህበረሰብ የባህል መድሃኒት እውቀት አመለካከት፣ አዘገጃጀትና አሰጣጥ::» ኤም ኤ ቴሲስ፣ የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ-ትምህርት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1999 ::

አለም እሸቱ :- *መሠረታዊ የምርምር ዘገባ አጻጻፍ* :: አዲስ አበባ፣ ቅድስት ማርያም ኮሌጅ የሊቨራ አርትስ ፋክልቲ ህትመት፣ 1992 ::

አብደላ መሐመድ ዓሊ :: *ተአምራዊ ፈውስ* :: አዲስ አበባ፣ ነጃሽ ኢስላሚክ አሳታሚ ድርጅት ፣ 1996 ::

አዲስ አበባ ጤና ቢሮ የተገኙ ጹሑፎች :: በጤና አገልግሎት ማ/ማ/መምሪያ የፋርማሲ እና የባህል መድሃኒት ቡድን ከሃገረሰብ ህክምና አዋቂዎች ጋር የአደረጋቸው ውይይት ፣ 1996 ፣(ያልታተመ) ::

የመነጋገሪያ መድረክ :: «የባህል መድሃኒት ከዘመናዊው ጋር ጎን ለጎን የሚሄድበት አሰራር መቀየስ ይኖርበታል::» *ጦቢያ* :: አዲስ አበባ፣ አጥቢያ ኮከብ ህትመትና የማስታወቂያ ሥራ ኃ.የተ.ግ.ማ፣ ህዳር፣ 1994 ::

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር :: *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና፣ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት* :: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣United Bible Societies ; 1992 ::

ጤና ጥበቃ የተገኙ ጽሑፎች:: የባህላዊ ህክምና አስተዳደር ቁጥጥር ደንብ :: ቁጥር 2000 (ያልታተመ)

ፈቃደ አዘዘ:: የመስክ *ሥራ* የሥነ-ቃል አሰባሰብ፣ አከለሳሰፍ፣ አተናተን እና አሰናነድ ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ለ«ባህልና የባህል አመራር ለልማት፣ ሀገር አቀፍ ኮንፈረንስ» የቀረበ ጹሑፍ ሚያዝያ 3-5፣ 1999፣ (ያልታተመ ጥራዝ) ::

______::*የሥነ ቃል መምሪያ* :: አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1991::

# የካሴቶች መዘርዝር

| | | |
|---|---|---|
| መሐመድ ዘይኑ :- | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 5፣2000 |
| ማሞ ኃይሌ :- | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 3፣2000 |
| ሩት ሊካሳ:- | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 10፣2000 |
| ተክሌ ኃብተገብርኤል | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 1፣2000 |
| ኑሩ አደም | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 4፣2000 |
| አቡበከር አህመድ | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 6፣2000 |
| አታላይ ዓለም | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 10፣2000 |
| እርገጤ ከበደ | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 2፣2000 |
| እዝራ ሙሉነህ | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 7፣2000 |
| ደጀኔ ብሩ | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 9፣2000 |
| ፍቅረሰብ መኮንን | ኦዲዮ ቴፕ ካሴት :- | ቁጥር 8፣2000 |

Abraraw Tesfaye. "Traditional Medicine in an Urban Center, Belief and Practices (The case of Dessie Twon, N, Ethiopia)." MA Thesis Department of Social Anthropology, Addis Ababa University, 1993.

Alan Miller, Richared. *The magical and Ritual use of, HERBS.* 1993.

Alemayehu Moges. "Traditional Ethiopian Medicine, Institute of Ethiopian Studies." Eight International Conferences of Ethiopian Studies, Addis Ababa University, 1984.

Assefa Balcha. "Traditional Medicine in Wollo Nature and History." MA Thesis Department of History, Addis Ababa University, 1992.

Fekadu Fullas. *Ethiopian Traditional Medicine: Common Medicinal Plants in Perspective.* Sioux city, lowa: St' Luke's Regional Medical Center, 2001.

Gordon L, Chavunduk. *Traditional Medicine in Modern Zimbabwe*. University of Zimbabwe Publications, 1994.

Grell, Ole Peter and Andrew. (ed), *Medicine and the reformation.* Cunningham, London and New York, 1993.

Haggard, Howard w. The Doctor in History. New York, Yole University. 1992.

*Encyclopedia of Religion and Ethics* . Volume, 5. ___________.

Hecht, Elisabeth-Dorthe. "Traditional Medicine and Magic among the Amhara of Ethiopia." Paper Prepared for the Conference of Ethiopian Feudalism, Addis Ababa, 1976.

Ministry of Health. "Current Status and Future Plans of Traditional Medicine in Ethiopian." Addis Ababa ;1989; (un published).

Mirgissa Kaba. "Indigenous Medical Beliefs and Practices Among the Illubabor Oromo." MA thesis Department of Social Anthropology, Addis Ababa University, 1983.

Pankhurt, Richard. *"The Historical Examination of Traditional Ethiopian Medicine and Surgery."* the Ethiopia Medical Journal. Addis Ababa, 1965 .3, n.4.

___________. *"The Beginning of Modern Medicine in Ethiopian."* Ethiopian Observer, 1965.V -9, n-2.

___________. *"The History and Traditional Treatment of Small Pox in Ethiopian."* 1963.

Peer, Philip M. and Kwesi Yankkah. (eds), *African Folklore: An Encyclopedia*. Published in Greet Britain, by Routledge, 2004.

Roundy, Robert. *Hazards of Communicable Diseases Transmission Resulting from Cultural Behavior in Ethiopian Rural Highland Dwelling Population: A Cultural Geographic Study*. Published PHD Dissertation alion, University of California, 1976.

Wilbrlt, Watson. (ed), *Black Folk Medicine*: The Therapeutic Significance of Faith and Trust. New Brunswiek, New Jersey, 1988.

Young Allan. *Medicial Beliefs and Practices of Begemeder Amhara.* Published PhD Dissertation, Philadelphia, University of Pennsyvania, 1970.

___________ .*The Practical logic of Amhara Traditional Medicine.* In Africa Therapeutic Systems, Los Angeles Cross Roads, press, 1979.

___________ *.Magic as a "Quasi-Profession." The Organization of Magic and Magical Healing among Amhara.* An International Journal of Cultural and Social Anthropology, V. XIV, n.3, 1975.


Zerihun Doda. "Culture, Belief and Mental Illness Among the Zay." MA Thesis Department of Social Anthropology, Addis Ababa University 2001.

"http://en.winkipedia org/wiki/folk medicine"

ሐኪም ሃጂ ኑሩ አደም



ሐኪም እርገጤ ከበደ



ሐኪም ተክሌ ኃ/ገብርኤል



ሐኪም ማሞ ኃይሌ



ሐኪም ፍቅረሰብ መኮንን



ሐኪም ሐጂ አቡበከር ሐህመድ



ሐኪም ደጀኔ ብሩ



አባሪ 1

## የመረጃ አቀባይ ሃኪሞች ዝርዝር ሁኔታ

| | ስም | እድሜ | ሃይማኖት | የትምህርት ደረጃ | የቤተሰብ ሁኔታ | ሙያውን የተማሩት | የአገልግሎ ዘመን | የሚሰጡት ህክምና | የህክምና መስጫ ቦታ | መተዳደሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሃኪም 1 | ማሞ ኃይሌ | 91 | ኦርቶዶክስ | ባህላዊ ትምህርት በተለያዩ ዘርፎች | ቤተሰብ የመሰረቱ | ከገዳማት፣ መነኩሴ፣ ከሼሆች፣ ከመጻሕፍት | 76 ዓመት | ለማንኛውም በሽታ | ሣሪስ፣ ዮሴፍ ቤተክርስቲያ አጠገብ | የባህላዊ መድሃኒት ህክምና በመስጠት |
| ሃኪም 2 | ተክሌ ኃብተገብርኤል | 70 | ኦርቶዶክስ | በባህላዊ ትምህርት | ቤተሰብ የመሰረቱ | ከአያታቸው፣ በህልመ-ሌሊትና ከመጻሕፍት | ከ50 ዓመት በላይ | ለማንኛውም በሽታ | ቀጨኔ መድኒዓለም 8 ቁጥር ማዞሪያ | የባህላዊ መድሃት ህክምና በመስጠት |
| ሃኪም 3 | እርገጤ ከበደ | 62 | ኦርቶዶክስ | በባህላዊ የወንጌል መምህር በዘመናዊ ዲፕሎማ | ቤተሰብ የመሰረቱ | ከአጎታቸው፣ ከገዳማት መነኩሴዎች ግብፅ፣ ቻይና፣ህንድ | ከ30 ዓመት በላይ | ለማንኛውም በሽታ | መሿለኪያ ድልድይ ገበያ | የባህላዊ መድሃኒት ህክምና በመስጠት |
| ሃኪም 4 | ፍቅረሰብ መኮንን | 25 | ኦርቶዶክስ | በባህላዊው እስከ መሪጌትነት ማዕረግ | ትዳር ያልመሰረቱ | ከገዳማት መነኩሴ፣ ከመጻሕፍት | 9 ዓመት | ለማንኛውም በሽታ | አክሱም ሆቴል አጠገብ | የባህላዊ መድሃኒት ህክምና በመስጠት |

## አባሪ 2

# የባህላዊ መድሃኒት ባሙያዎች የሚያክሟቸው የበሽታ አይነቶች

| ሃኪም ማሞ ኃይሌ | ሃኪምተክሌ ኃብተገብርኤል | ሃኪም እርገጤ ከበደ | ሃኪም ሃጂ ኑር አድም | ሃኪም አቡበከረክ አህመድ | ሃኪም ፍቅረሰብ መኮንን | ሃኪም አክሊሉ ብርሃኑ | ሃኪም ደጀኔ ብሩ | ሃኪም ሃጂ ሳኒ አሊ | ሃኪም ተውህቦ ምሕረት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| - ኪንታሮት<br>- አልማዝ ባለጭራ<br>- ስኳር<br>- የደም ግፊት<br>- ለተቅማጥ<br>- ለጨብጥ<br>- ለፈንጣጣ በሽታ<br>- ለወባ በሽታ<br>- ለካንሰር<br>- ለችፌ<br>- ለቆዳ ቁስል<br>- ለጎርምጥ<br>- ለነቀርሳ<br>- ለጆር ቁስል<br>- የመሽናት ችግር ላለበት<br>- ለወፍ | - ለኪንታሮት<br>የ5 ዓይነት<br>- የ4 ዓይነት ነቀርሳ<br>- ወንዴና ሴቴ አጥንትና የደም ካንሰር<br>- የአባላዘር በሽታ<br>- ለ4 ዓይነት ችፌ ለፈንገስ<br>- አልማዝ ባለጭራ<br>- ለማኛውም እባጭና ቁስል<br>- ለጨንጉራ አልሰር | - ለፀጉር መርገፍ የቆዳ ኪንታሮት<br>- ጭርት<br>- የቆዳ ማሳከክ<br>- ላሽ<br>- ፎረፎር<br>- ማዲያት<br>- የሰውነት ላብ ማሳከክ<br>- ቋቁቻ<br>- ቆርቆር<br>- ችፌ<br>- ለምቆ<br>- የብብት ጠረን<br>- ለራህ<br>- አልማዝ | - ለኪንታሮት<br>- ለካንሰት<br>- ለተላላፊ በሽታ<br>- ለሆድ በሽታ<br>- ለዓይነ ጥላ<br>- ለስንፈተ ወሲብ<br>- ለጉበት በሽታ<br>- ለሳንባ ነቀርሳ<br>- ለቲቢ<br>- ለማገኛ ውም ቁስል<br>- ለአልማዝ ባለጭራ<br>- ለችፌ<br>- ለፎረፎር<br>- ለጨብጥ | - ኪንታሮት<br>- የወገብ ህመም<br>- ጭንቀት<br>- ላብ<br>- የሆድ መንፋት<br>- መጮህ<br>- የወሲብ ድክመት<br>- ለጭንቀት<br>- ለድግምት<br>- ለአይነጥላ<br>- ለሚጥል በሽታ<br>- ለራስ ምታት<br>- ለአልማዝ ባለጭራ<br>- ለቁስል<br>- ለቋቁቻ | - ለኪንታሮት<br>- ለአልማዝ ባለጭራ<br>- ለጋንግሪን<br>- ለካንሰር ነቀርሳ<br>- ለስንፈተ ወሲብ<br>- ለሚጥል<br>- ለጭንቀት<br>- ለአፍ ጠረን<br>- ለጉበት በሽታ<br>- ለሚያሳብድ<br>- ለሆድ ውስጥ በሽታ<br>- ለጉበት<br>- ለጨንጉራ<br>- በአካል ላይ | - ለኪንታሮት<br>- ለፊስቱላ<br>- ለችፌ<br>- ለቆዳ በሽታ<br>- ለልክፍት<br>- ለቋቁቻ<br>- ለጭርት<br>- ለኩላሊት ኢንፌክሽን<br>- ለማህፀን ኢንፌክሽን<br>- ለአንጎል ነቀርሳ<br>- አለባላዘር<br>- ለጡት ህመም<br>- ለአልማዝ ባለጭራ<br>- ለእጢ<br>- ለጆሮ ህመም | - ለደም ብዛት<br>- ለአልማዝ ባለጭራ<br>- ለአፍ ጠረን<br>- የአፍንጫ ጠረን<br>- ለጨብጥ<br>- ለልክፍት<br>- ለእጅ ሰብ<br>- ለአልጋ ላይ ለሚሸና<br>- ለጨንጉራ<br>- ለሚርት<br>- ለአይነ ጥላ<br>- ለራስ ምታት<br>- ለወባ እስቴን | - ለኪንታሮት<br>- ጆሮ ህመም<br>- ሆድ ህመም<br>- ስኳር መድኃኒት<br>- ኩላሊት<br>- እባጭ<br>- ቋቁቻ<br>- ነስር<br>- አእምሮ በሽታ<br>- ቆዳ በሽታ<br>- ለዓይን በሽታ<br>- ለእራስ ምታት<br>- ለብርድ በሽታ<br>- ለእንቅርት በሽታ | - ለመፍትሔ ሥራይ<br>- ለኪንታሮት<br>- ለነቀርሳ<br>- ለድክመት ወሲብ<br>- ለውሻ ልክፍት<br>- ለጉበት /ወፍዙር/<br>- ለጨብጥ<br>- ለራስ ሕመም<br>- ለአእምሮ መረበሽ<br>- ለጆሮ ህመም<br>- ለልብ ሕመም<br>- ለስኳር በሽታ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በሽታ<br>- ለሣል<br>- ለጨንገራ<br>- ለሆድ ትላትል<br>- ለአሜባ<br>- ለቋቁቻ<br>- ለልክፍት<br>- ለመጋኛ<br>- ለውነቱ ለማይታዘዝ ለት<br>- ለኮሶ<br>- ለነርቭ<br>- ለእከክ<br>- ለአባላዘር በሽታ<br>- ለማንኛ ውም እባጭ<br>- ለአስም<br>- ለነስር<br>- ለማኛውም ኢንፌክሽን<br>- ለሶሰሪያሲስ<br>- ለእጀሰብ<br>- ለራስ | - ለአሜባና ለተቅማጥ<br>- ለሆድ ድርቀት ለጨንገራ አሲድ<br>- ለወፍና ለጉበት በሽታ<br>- ለቋቁቻና ለጭርት<br>- ለትፋኮማ በሽታ<br>- ለሚጥልና ለሚያንቀ ጠቅጥ<br>- ለልክፍት<br>- ለሳልና ለሳንባ ነቀርሳ<br>- ለደም ግፊት<br>- ለሾተላይ<br>- ለትውከትና ለሚያቅለሸ ልሽ<br>- ለመጋኛ | ባለጭራ<br>- ብጉንጅ<br>- የውጪ ዕጢ<br>- ውጋት<br>- ቁርጥማት<br>- ነቀርሳ<br>- ዝሆኔ<br>- ጥፍረ መጥምጥ<br>- የቆላ ቁስል<br>- ጨብጥ<br>- ኪንታሮት<br>- ፌስቱላ<br>- እባጭ<br>- የማያቋርጥ የማህፀን ፈሳሽ<br>- ካንሰር<br>- የአካል መድከም<br>- የመሽናት ችግር<br>- የወር አበባ መብዛት<br>- የኩላሊት በሽታ | - ለራስ ህመመም<br>- ለብርድ በሽታ<br>- ለሸባነት<br>- ለቁርጥማት<br>- ለዝሆኔ<br>- ለደም ብዛት<br>- ለነስር<br>- ለአስም<br>- ለጆሮ በሽታ<br>- ለዓይን በሽታ<br>- ለጭርት<br>- ለለምፅ<br>- ለሆድ ትላትል<br>- ለንቅርት ማጥፊያ<br>- ለሚያሳክክ በሽታ<br>- ለልክፍት<br>- ለቦርጭ መቀነሻ<br>- ለሰውነት | - ለጭርት<br>- ለብጉር<br>- ለችፌ<br>- ለማዲያት<br>- ለለምጽ<br>- ለላሽ<br>- ለቆረቆር<br>- ለፎረፎር<br>- ለሪህ<br>- ለእብጠት<br>- ለፊስቱላ<br>- ለካንሰር<br>- ለነርብ<br>- ለብርድ<br>- ለቁርጥማት<br>- ለሚሸመቀቅ<br>- ለኪላሊት በሽታ<br>- ለፊኛ ኢንፍክሽን<br>- ለሽንት መሸናት ችግር<br>- ለሃሞት<br>- ለልብ በሽታ<br>- ለጉበት በሽታ | ለሚወጣ ማንኛውም ቁስል | - ለጃርዲያ<br>- ለእጀ ሰብ<br>- ለማንኛ ውም ቁስል<br>- ለሆድ ትላትል<br>- ለአፍንጫ ጠረን<br>- ለሚጥል በሽታ<br>- ለአሜባ<br>- ለቁርጥማት<br>- ለሳ ህመም<br>- ለጨንገራ<br>- ለራስ ምታት<br>- ለወሲብ ችግር<br>- ለተቅማጥ<br>- ለአእምሮ ጭንቀት<br>- ለነቀርሳ<br>- ለምላስና ለጉሮሮ<br>- ለሚቆስል | - ለወሲብ ድክመት<br>- ለለምጽ<br>- ለኪንታሮት ለነቀርሳ<br>- ለወፍ<br>- ለጉበት<br>- ለችፌ<br>- በደረቁና እየቆሰለ ለሚያሳክክ<br>- ለጆሮ መምገል<br>- ለቋቁቻ<br>- ለሆድ ውስጥ ደዌ<br>- ለአስም<br>- ለሪህ | - ለእሪህ በሽታ<br>- ደም ማነስ<br>- ጨንገራ<br>- ልብ ድካም<br>- ጨብጥ<br>- ጥርስ ህመም<br>- ፎረፎር<br>- የሰውነት ጠረን<br>- የአፍ ውስጥ ጠረን<br>- ለቁንጭር<br>- ንቅሳት<br>- ካንሰት<br>- የሆድ ትላትል<br>- ለማንኛ ውም ቁስል<br>- የደም ብዛት<br>- ለምጽ<br>- ለችፌ<br>- ጭርት<br>- አስም | - ለድንገተኛ ሕመም<br>- ለሆድ ህመም<br>- ለኩላሊት ህመም<br>- ለጨንገራ ህመም<br>- ለውሃ ወለድ በሽታ<br>- ለአስም በሽታ<br>- ለገርጋሪ<br>- ለዓይነ ጥላ<br>- ለሰው ውለት<br>- ለጥርስ ህመም<br>- ለምች አደር<br>- ለሚጥል በሽታ<br>- ሽንት ለሚዘጋወ<br>- ለመጋኛ /ጋዕዝ/ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምታት<br>- ለስንፈተ ወሲብ<br>- ለሆድ ውስጥ ደዌ<br>- ለእጢ<br>- ለቁርጥማት<br>- ለአካል ላይ ለሚወጣ ቁስል | - ለጥርስ ለቆዳ ቁስል<br>- ጆሮ ለሚመግል<br>- ለሰምጥ በሽታ በሚቀባ<br>- ለአስም ለሳይነስ<br>- ለነስር<br>- በቆዳ ላይ ለሚወጣ ሶሪአሲስ | - ተቅማጥ<br>- የወፍ በሽታ<br>- የሆድ ነቀርሳ<br>- የጉበት በሽታ<br>- ምግብ ለማይበላስ ት<br>- የማያቋርጥ ተቅማጥ<br>- ጃርዲያ<br>- ጨጓራ<br>- የውሃ ትል<br>- ስኳር<br>- አሜባ<br>- ቁርጠት<br>- የጥርስና የድድ በሽታ<br>- የማያቋርጥ ሳል<br>- የጆሮ መምገል<br>- የአፍ ጠረን | መጨመር<br>- ለሳይነስ | - ለጨጓራ በሽታ<br>- ለጃርዲያ<br>- ለአሜባ<br>- ለትላትል<br>- ለቁጠርት<br>- ለተቅማጥ<br>- ለጠረን<br>- ለጆሮ<br>- ለዓይን<br>- ለጥርስ<br>- ለምላስ መያዝ<br>- ለአስም<br>- ለሳይነስ<br>- ለሳንባ ነቀርሳ<br>- ለደም ግፊት | | | | - ኢንፌክሽን<br>- ሽረሪት ቁስል<br>- የውሻ ልክፍት<br>- የወሲብ ችግር<br>- ለእከክ<br>- የቁርጥማት<br>- የድንገተኛ<br>- የተላላፊ በሽታ<br>- የማዲያት<br>- የምች<br>- የሳል ህመም<br>- የጡት ካንሰር<br>- የአሜባ<br>- የእጀ ሰብ<br>- የአልማዝ ባለጭራ<br>- የቶንሲል<br>- ለሚጥል | - ለቋቁቻ /ደረመን/<br>- ለአመንምን በሽታ /ህመም ፈፀንት/<br>- ትምህርት ለማይገባው /ግላልብ/<br>- ለሽረፊ ሕመም ወይም ለአልማዝ ባለጭራ<br>- ለሳንባ ወይም ትቢ<br>- ለቁርጥት<br>- ለእ ህመም<br>- ለሾተላይ /ውርዝል/<br>- ለአሜባ<br>- ለጃርዲያ<br>- ለሕልመ ለሊት /ቅትቃጤ/ |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | - የአፍንጫ አስም<br>- የደም ግፊት<br>- ለአስም<br>- ለእንቅርት<br>- ብሮንካይት<br>- ብርድ<br>- የመንፈስ ጭንቀት<br>- ለሚጥል በሽታ<br>- ለመፍትሄ ስራይ<br>- ሌሊት ለሚባንን<br>- ለአይነ ጥላ | | | | | | | |

*ኪንታሮት ፊንጢጣ ላይ ዙሪያውን የሚወጣ አለ፣ እንደመዥገር የመውጣት ባህሪ ያለው አለ፣ የሚገለባበጥም አለ ::

አባሪ 3

## መረጃ አቀባይ ታካሚዎች

| መለያ ቁጥር | እድሜ | ሃይማኖት | የቤተሰብ ሁኔታ | አድራሻ | የት/ት ደረጃ | ፆታ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ታካሚ 1 | 41 | ኦርቶዶክስ | ቤተሰብ የመሠረቱ | ገጠር ወሎ | 3ኛ | ወንድ |
| ታካሚ 2 | 51 | ኦርቶዶክስ | ቤተሰብ የመሠረቱ | አዲስ አበባ | 10ኛ | ሴት |
| ታካሚ 3 | 66 | ፕሮቴስታንት | ቤተሰብ የመሠረቱ | ገጠር ግንደበረት | ያልተማሩ | ወንድ |
| ታካሚ 4 | 28 | ሙስሊም | ትዳር ያልያዙ | አርሲ ጮሌ ከተማ | ቢ.ኤ በባዮሎጂ | ወንድ |
| ታካሚ 5 | 55 | ሙስሊም | ቤተሰብ የመሠረቱ | ኦጋዴን ጎሬ | ያልተማሩ | ወንድ |
| ታካሚ 6 | 50 | ፕሮቴስታንት | ቤተሰብ የመሠረቱ | አዲስ አበባ | 12 ክፍል | ሴት |
| ታካሚ 7 | 65 | ኦርቶዶክስ | ቤተሰብ የመሠረቱ | ጎጃም | የባህላዊ ት/ት የተማሩ | ወንድ |

አባሪ 4

## ለባህላዊ ሃኪሙ የቀረቡ ጥያቄዎች

## በቅድሚያ ለቃለ-መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ።

I. ግላዊ መረጃ

1. እድሜ ______________________
2. ፆታ ______________________
3. ሐይማኖት ______________________
4. የትምህርት ደረጃ ______________________
5. መተዳደሪያ ______________________
6. የቤተሰብ ሁኔታ ______________________

II. በሽታዎችና የሚሰጧቸው ህክምናዎች

1. ወደዚህ ሙያ እንዴት ገቡ? ______________________
   ሙያውን ከማን ተማሩት?
2. ከየትኛው የህክምና ቡድን ይመደባሉ?
   ሀ. በፀሎት ከሚያድኑ? ______________________
   ለ. በፀበል ምሪት ከሚያድኑ? ______________________
   ሐ. ቅዱሳን መጻሕፍትን ገልጠው ከሚያድኑ? ______________________
   መ. መድሃኒትን አዘጋጅተው ከሚሰጡ? ______________________
   ሠ. ከወጌሻ? ______________________
   ከላይ ከተጠቀሱት በሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ ይጥቀሷቸው።
   1. ______________________ 2. ______________________ 3. ______________________
3. በዚህ የህክምና ሙያ ለስንት ዓመት ቆይተዋል? ______________________
4. በዋናነት የሚፈውሷቸውን 5 በሽታዎች ይጥቀሱ ?
   1. ______________ 2. ______________ 3. ______________
   4. ______________ 5. ______________
5. በአማካይ በቀን ምን ያህል በሽተኞች ያክማሉ ?
   ህክምናውን መቼ ይሰጣሉ ?
6. ወደ እርስዎ የህክምና ማዕከል የሚመጡት በአብዛኛው በምን በሽታ የተያዙ ናቸው ?
   1. ______________ 2. ______________ 3. ______________
   4. ______________ 5. ______________

7. በተለየ ሁኔታ የሚያድኑት በሽታ ካለ ይጥቀሱ ?

1. ________________ 2. ________________ 3. ________________

8. ለህክምና የሚጠቀሙበትን መድሃኒት ከየት ያገኙታል ?

9. ለታካሚዎች ያዘጋጁትን መድሃኒት የሚሰጡት

ሀ. ብቻውን ይፈውሳል ብለው ነው ? ________________

ለ. ከእምነት ጋር አያይዘው ነው ? ________________

10. መድሃኒቶቹ የሚዘጋጁበት ጊዜ (ሰዓት) መቼ ነው ? ለምን ?

የሚሰበስቡበት ወቅት አለ ? ________________

ምክንያቱን ቢጠቅሱ ? ________________

11. የመድሃኒት አዘገጃጀት

ሀ. በተለየ ሰው ነው ? ________________ ለምን ?________________

ለ. የተለየ መሣሪያ አለ ? ________________ ለምን ? ________________

ሐ. የተለየ ሰዓት እና ቀን አለ ? ____________ ምክንያቱ ቢጠቀስ ? ________

መ. በእምነት /እንደየሃይማኖቱ/ ስም ይዘጋጃል ? ________________

ምክንያቱን ይጥቀሱ ? ________________

ሠ. መድኒቶቹ እንዴት ይዘጋጃሉ ? ደረጃዎቹን ይዘርዝሩ ? ________________

12. መድሃኒቱን በሽተኞች እንዲወስዱ የሚያዙበት

ሀ. የተለየ ቀንና ሰዓት አለ ? ________________

ለ. መድሃኒቱን ብቻ ይሰጣሉ ? ________________

ሐ. መድሃኒቱን የሚያግዙ ተጨማሪ የአወሳሰድ ስርዓት ያዛሉ ? ________________

________________

መ. በእምነት ስም ይሰጣሉ ? ________________

13. ከሌሎች ባህላዊ ሃኪሞች ጋር ተቀራርበው ይሰራሉ ? ________________

ሀ. ከሰሩ ምክንያቱን ይግለፁ ? ________________

ለ. ካልሰሩ ምክንያቱን ይግለፁ ? ________________

14. ከዘመናዊ የህክምና ባለሙያዎች ጋር ተቀራርበው ይሰራሉ ? ________________

ሀ. ከሰሩ ምክንያቱን ይግለጹ ? ________________

ለ. ካልሰሩ ምንክንያቱን ይግለጹ ? ________________

## ለባህላዊ ህክምና ታካሚዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

## ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ

I. ግላዊ መረጃ

1. እድሜ ________________

2. ፆታ ______________

3. ሐይማኖት ______________

4. የትምህርት ደረጃ ______________

5. መኖሪያ ________________

ሀ. በገጠር ______________ ለ. በከተማ ______________

6. የቤተሰብ ሁኔታ

ሀ. ያገባ ______ ለ. ያላገባ ______ ሐ. ስንት ቤተሰብ አለዎት? ______

II. በሽታዎችና ህክምናቸው

1. በአካባቢያችሁ ህብረተሰቡን የሚያጠቁ ዋና ዋና በሽታዎች መካከል 5ቱን ይጥቀሱ ?

1. ______________ 2. ______________ 3. ______________

4. ______________ 5. ______________

2. የበሽታዎች መንስኤ ይሆናሉ የምትሏቸውን ይዘርዝሩ?

1. ______________ 2. ______________ 3. ______________

4. ______________ 5. ______________

3. ስትታመሙ በቤታችሁ የምታደርጉ ህክምና ካለ ይግለፁ? ______________

4. ስትታመሙ በቅድሚያ የምትሄዱት

ሀ. ወደ ባህላዊ ሃኪም? ______________ ለምን ? ______________

ለ. ወደ ዘመናዊ ህክምና ተቋም?______________ ለምን ? ______________

5. እርስዎና ቤተሰብዎ አዘውትረው የሚታከሙት

ሀ. በባህላዊ ሃኪም ? ______________ ለምን ? ______________

ለ. በዘመናዊ ህክምና ? ______________ ለምን ? ______________

ሐ. በሁለቱም ይገለገላሉ ? ______________ ለምን ? ______________

6. የአካባቢያችሁ ሰዎች በሽታዎችን በምን በምን ይከላከላሉ ?

______________________________________________

7. ለህክምና አነስተኛ ክፍያ የሚጠይቀው

ሀ. የባህላዊ ህክምና ______________ ለ. የዘመናዊ ህክምና ______________

8. አስተማማኝ ህክምና የሚገኘው
   ሀ. በባህላዊ ህክምና ______________ ምክንያቱ ቢጠቀስ ______________
   ለ. በዘመናዊ ህክምና ______________ ምንክያቱ ቢጠቀስ ______________
9. በባህላዊ ህክምና ይበልጥ የሚታከሙ
   ሀ. በመድሃኒት አዋቂ ሃኪም ______________ ምክንያት ______________
   ለ. በፀበል ? ______________ ምክንያት ______________
   ሐ. በፀሎት ? ______________ ምክንያት ______________
10. የምትወስዱጽ መድሃኒት
   ሀ. መድሃኒቱን ብቻ ያድነኛል ብላችሁ ነው ?______________
   ለ. ከእምነታችሁ ጋር በማያያዝ ነው ? ______________
11. የባህላዊ ሃኪሞቹ
   ሀ. መድሃኒቱን ብቻ ይሰጣሉ ? ______________
   ለ. ከእምነት ጋር አያይዘው ይሰጣሉ ? ______________
12. አወሳሰድ
   ሀ. መድኒቱን ብቻ ትወስዳላችሁ ?______________
   ለ. ተጨማሪ ክንዋኔና የአወሳሰድ ክንዋኔ አለው ?______________
   ሐ. መድሃኒቱን የምትወስዱበት የተለየ ቀንና ሰዓት አለ ? ይጥቀሱ ?
   ______________
13. ሃኪሙ ስለት እንድትሳሉ ያዟችኋል?
14. ሃኪሙ የተለያዩ እንስሳት እንድትሰው ያዟችኋል?
15. መድሃኒቱን የምትወስዱበት የተለየ እቃ ካለ ይጥቀሱ?
16. መድሃኒቱን እየወሰዳችሁ የምትከለከሉት ካለ ይጥቀሱ?
   **1.** ______________ **2.** ______________ **3.** ______________
   **4.** ______________ **5.** ______________
17. ወደዚህ ባህላዊ ህክምና እንድትመጡ ማን ነገራችሁ ? ______________
   ወደዚህ እንድትመጡ የተነገረበትን ምክንያት ቢገልፁ ? ______________

ለመጀመሪያ የመጽሐፍ ሠላምታዬን እንዳቀረብሁ [illegible] እኔ ሀሳቤ
[illegible] የተደረገብኝን እስተያየት [illegible] ነው።
[illegible]
[illegible] እ 6ወር [illegible]
[illegible]
[illegible] ሀሳቤ [illegible] እመሰግናለሁ
[illegible] ሀሳቤ [illegible]
[illegible] ኣለሁ። [illegible] ሀሳቤ [illegible]
[illegible] 10

ስ.ቁ ቁጥሬ 0918760723 ነው

እመሰግናለሁ።

[illegible]

3/10/98

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible] 011.21.66.28.424

[illegible]